# እነእምሰቱ –''መከረኞች !'':

(የገድላቸው ድርሳናዊ ሐተታ፣በአጭሩ እንደቀረበ)

( ኃይሉ – ገሞራው )



ዶክቶር እጓለ ገብረ ዮንስ
1924 – 1983
(መምህረ ፊልስፍና)



አቤ ጉበኛ
1925 – 1972
(መምህረ ድረሰት)



እሸቱ በቀለ (ሻምበል)
1960 – 1991
(የዓየር በራሪ አርበኛ)




የሙታኑ – ሕያዋን

ጦማራት !

(ደብዳቤዎች)



ጸጋዬ ገብረ መድኅን
1929 – 19 ?
(መምህረ ትግል)



አሰፋ ማሩ
1930 – 1989
(መመህረ ትግል)

# መታሰቢያቸው ትሁንልኝ !

የዚች ትንሽ እትም፣መጽሐፋዊ መታሰቢያነታ፣በይዘቷ ውስጥ፣ ገድላቸው ለተተረከውና ክቡር ስማቸውም ለተጠቀሱት፣ አምስት ወንድሞቼ ነው። ለእናት ሀገራችንና ለሕዝባዊ ወገናችን፣በጥብቅና ቆመው፣በአደባባይ የተከራከሩና በዚያም ሳቢያ፣ክቡር ሕይወታቸውን በመሥዋዕትነት አቅርበው፣አለዕድሜያቸው ያለፉ በመሆናቸው፣እን ዲህ አይነቱ አምሃዊ ገፀ በረከት የሚያንሳቸው እንጅ፣የሚበዛባቸው አይሆንም።ወደፊት ብርሀት የሆነች ኢትዮጵያ በምትከሠትበት ጊዜ ለክብራቸው ተገቢ የሆነና ተጋድሎአዊ ምግባራቸውንም በሃቅ የሚያ ንፀባርቅ ታሪካዊ ሐውልታቸው እስኪታነፅላቸው ድረስ፣ ይህች እት ም በማስታወሻነት ልታገለግል እንደምትችል፣ ተሰፋዬም እምነቴም መሆኑን በመግለፅ፣ በትሕትና አቀርባለሁ።........................................

*****************(ገ ሞ ራ ው)**********************

# እነአምስቱ –"መከረኞች !"

(የገድላቸው ድርሳናዊ ሐተታ፣በአጭሩ እንደቀረበ)

( ኃይሉ – ገሞራው )




ዶክቶር እጓለ ገብረ ዮሐንስ
1924 – 1983
(መምህረ ፈልስፍና)



አቤ ጉበኛ
1925 – 1972
(መምህረ ድረሰት)



እሸቱ በቀለ (ሻምበል)
1960 – 1991
(የዓየር በራሪ አርበኛ)






ጸጋዬ ገብረ መድኅን
1929 – 19 ?
(መምህረ ትግል)

የሙታኑ – ሕያዋን

ጦማራት !

(ደብዳቤዎች)



አሰፋ ማሩ
1930 – 1989
(መመህረ ትግል)

# ሥርወ መሠረት !

## (እንደ መቅድም)

በዓለማችን ላይ የሚከወን ማንኛውም ኩነት ሁሉ፣እንደአፈጣጠር ባሕርዩና እንደአመጣጥ ጠባዩ፣እንበለ ተልእኮ እንደማይከወን፣በፍፁም አተንክሮ መናገር ይቻላል! ለዚህም ተፈጥሮአዊ ሥርዓታዊ ድርጊት፣ከራሱ ከተፈጥሮ የበለጠና የተሻለ ሌላ ማስረጃ አናገኝም። የዑደተ ደመናት ክሥተትና በሰማያት ማንዣበብ፣አጠቃላይ ኪደቱ፣ጠለ ዝናማትን ለማውረድ ነው።ዝናብ መዝነቡ ደግሞ፣በተራው የብስ ምድርን ለማርጠብና በውጤቱም ለአዝርእትና ለእፀዋት ልምላሜን በመስጠት መከርንና ፍሬያትን በማፍራት፣ለእንሰሳትና ለአራዊት፣በጠቅላላውም በደመ ነፍስ ለሚንቀሳቀሱ ፍጡራን "ተመግቦ ሕይወት" ለማበርከት ነው።

በሰማያት ላይ ተሠትራ፣እንደ እንቁና እንደ ልዩ ፈርጥ እያብረቀረቀች ምግብናዋን ባለማቃረጥ፣ ዋዕዩዋንና ፀዳለ ብርሃንን በየቀኑ በመርጨት የምትኖረው ፀሐያችንም ብትሆን፣ መላው የዓለሙ ፍጡራን፣ ያለእርሳ ሕልውና በዚህ ምድር ላይ መኖር እንደማይሆንላቸውና እንደማይችሉም ጠንቅቃ ስለእምታውቅ ነው። ከየአራቱ መአዝናት ዓየራት ቢነፍሱ፣አፍላጋት ማያታቸውን አዝለው፣በየኸረታቸው ቢንሻሹ......ሁሉም በየተግባራቸው ተሠማርተው፣የየበኩላቸውን ተግባራዊ ግዳጅ ቢያከናውኑ፣የተፈጥሮ ተልእኮአቸው አስገድዶአቸው እንጅ ፣ወደው የሚያደርጉት እንዳያደለ ይታወቃል። ነገረ ምክንያተ ተልእኮ፣ በዚህ አይነቱ መግለጫ ይከተታል።እያንዳንዱን ምድራዊ ኩነት፣በየዘርፉ ጠልቀንና መጥቀን ብንመረምር፣ የየግሉና የየራሱ የሆነ፣ ምክንያታዊ የሕልውና ተልእኮ እንዳለው መረዳት እንችላለን።......እንዲህ እንዲያ እያልኩ በማስስ የምደረድራቸው ሐሳቦች፣ሥነ ጽሑፍም፣ የበኩሉ የሆነ መነሻና መድረሻ ተልእኮ ያለው መሆኑን ለማመሣከር በማሰብ ነው። ጥንታውያን የሙያው አባቶችም፣የደራስያንና የድርሰትን ተልእኮ በማስ

መልከት -"ኩሉ ዘተጽሕፈ - ለተግሣፀ ዚአነ ተጽሕፈ!" በሚለው አጠቃላይ መርሕ አካ ትተው መዝግበውታል።..........................

እያንዳንዱ ግዙፍ አካልና ረቂቅ መንፈስ(ነገር)በዚህ ዓለም ገዝፎ ሲገኝ፣ያለአንዳች ምክንያተ መንሥዔና ተልእኮ እንዳይደለ ከተረዳን፣የሁለንተናን ኩነት እንደጠባዩና እንደባሕርዩ ለማስተናገድ፣ሰዎችን ሊረዳ እንደሚችል መታወቅ አለበት ።

ማንኛውም ሥነ ጽሑፋዊ መድበል ሁሉ፣የየራሱ የሆነ መነሻ ዓላማና መደረሻ ግብ አለው።እንደጋማ ከበት ተምሳሊትነት ያለው ይመስላል። "ጉዳ" (ቀንድ የለሾች) ከሆኑቱ በስተቀር፣የጋማ ከብቶች ሁሉ በስተፊታቸው ቀንድ፣ በስተሻላቸው ደግሞ ጭራ(ጅራት) እንዳላቸው ይታወቃል።እንዴው ሙያዬ ብሎ ያጠናለን ባይኖርም፣የበስተፊቱም ሆነ የበ ስተሻላው ተቀፅላ አካል (አላል)፣በመከላከያነት የሚያገለግሉ ደጀኖች እንደሆኑ መገመት የሚያስቸግር አይመስለኝም። ያ አይነቱ የእንስሳቱ ፍጥርጥራቸው፣ያለ "ተልእኮአዊ ግብ" እንዳይደለ መገመት አያቅትም።የሚፈሩት ነገር ከበስተፊታቸው ይኖቹው አፍጦ በቀረባ ቸው ቁጥር፣ ወዲያው ቀንዳቸውን አስተካክለው ለመተምተም ሲሞክሩ፣ ያ ሹል ቀንዳ ቸው የተፈጥሮ ሥራውን መወጣቱ እንደሆነ ስናገናዝብ ፣ ቀንድ ሁሉ መቅድማዊ የተፈ ጥሮ ተልእኮ እንዳለው ይታወቀናል።

የትኛውም ብዕር ዘመት ደራሲ፣ለሚያቀርበው ጽሑፋዊ የድ ርሰት ሥራውና ለሚጠምቀው የወይን ጠጅ ጠበሉ ሁሉ፣ይቅጠንም ይወፍር፣ይጣፍጥ ይጎ ምዝዝ እንጅ፣ሥነ ጽሑፋዊ "ተልእኮ" እና ልዩም የሆነ "አስተምህሮ" አለው። የተፃፈና የተመዘገበ ሁሉ፣እንዲሁ በከንቱ አልተጻፈም፣አልተመዘገበብም።..........

በዚህ እትም ውስጥ ሠፍረው የሚገኙ፣"ገድላውያን ታሪኮች" ሁሉ እንደ አይነታቸው መለያየት ሁሉ፣የአገኛኘታቸው መሠረትና ምንጭ ለየቅል ቢሆንም፣ በአንድ ባሕርያቸው ግን ፍፁም የሆነ መሰልነት አላቸው።ያም አንድ ወጥ የሆነው አስተባባሪ ባሕ ርያቸው "ሁሉም ግለሰቦች ሰው ሠራሽ (Unnatural) በሆነ አማማት፣ ከዚህ ዓለም ፣ ገና የመጡበትን ምድራዊ ሕይወት ሳይጠግቡ፣በመካከለኛው የለጋ ለምለም ዕድሜያቸውላይ

ተቀጭተው ያለፉ መሆናቸው ነው።ግድ ሆኖባቸው እንጅ፣በዚያ የምቦቃቅላ ድሜያቸው ላይ ማለፍ፣ ፍላጎት ያላቸው እንዳልነበሩ፣ለማንም ግልፅ ይመስለኛል።

እነዚህ የቅርብ ወንድሞቹ የነበሩት ወገኖቼ፣ ተመሳሳይ በሆነ "ኢተፈጥሮ አዊ ሞት" (Unnatural Death) በግዳጅ ያለፉ በመሆናቸው፣እነሱ በሞት በማለፋቸው የተ ጎዱ መሆናቸው እየታወቀ፣እኔ በሕይወት ያለሁቱን ሕያው ሰው፣አለአግባብ የመሞታቸው ፀፀት፣ እጅግ እያንገበገበ አቃጥሎ ይጠብሰኛል። አምስቱም "ሰማዕታት" አለድሜያቸው በመራራ ሞት ተቀጭተው ለማለፍ የበቁት፣ለግለ ራሳቸው ጥቅማዊ ግብ ሲኳትኑና ሲንሰ ፈሰፉ ሳይሆን፣ተጀምሮ እስኪጨረስ ይጥሩ የነበረው፣"ዕቡያንና ዕኩያንን ሥንገው በመቃ ወም"፣ ለሕዝባውያን ወገናቸውና ለቅድስት ታሪካዊት እናት ሀገራቸው "አማናዊና አዎን ታዊ ደኅንነት" በማስገኘት ጉዳይ ላይ፣ጠዋት ማታ ተጋፍጠው፣ያላዋዛ ተጋድሎ ያደርጉ ስለነበር ብቻ ነው።

"......ኢትዮጵያን ያለ ወዮለት !!"ብለው ያስጠነቀቁ የነበሩት፣የአንጋፋው ትውልድ ዕውቅ ደራሲ"አሸብር ገብረ ሕይወት"፣ምክራዊ አባባላቸው ትክክል እንደነበረ የሚመሠክረው፣የነዚህ እንደወለላ ማር ዕውቀታዊ ጣዕም የነበራቸው"እንበለ ኢትዮጵያ" ሲሉ፣በዕቡያን አረማውያን ተንባላት ፋሽስቶች ተቀጥቅጠው ማለፋቸው ነው። ለአያሌ ዘመናት ስትወድቅ ስትነሳ ፣ ካለንበት የጊዜ ዕርከን ላይ መድረስ የቻለች እናት ሀገራችን ኢትዮጵያ፣ ራሳቸውን እንደ ሻማ እያቃጠሉ የነፃነት ብርሃን ሲሰጡ በቻሉ ቆራጥ ልጆቻ ተጋድሎ እንደሆነ፣ ከየታሪኩ መዛግብት ውስጥ፣ ዱባ ዱባ የሆኑ ሐረጋዊ አንቀጾችን እየ መዘዙ ማስረዳት ይቻላል።እልህኞች የሆኑ ጠላቶቻም ቢሆኑ፣ "ካልገዛናት ያም ካልተሣ ካልን ካላጠፋናት !" በሚል የገረረ ድረቀት፣ሲያተራምሳትና ሲያንገላታት ኖረዋል። የማ ይገባቸው "ደነዝ ደናቁርት"ሆነው እንጅ፣ኢትዮጵያ "መጥፋት የማትችል ሕያዊትና ዘለ ዓለማዊት ሀገር" እንደሆነች፣ትንቢት የተነገረላት፣ሱባዔ የተቆጠረላት "ፍፅምት" ሀገር እንደሆነች ማወቅ በቻሉ ነበር። "አማን እብለክሙ፣እስከየኃልፍ ሰማይ ወምድር፣የውጣ እንተ አሐቲ ኅርመታ ፣ ወአሐቲ ቅርፀታ፣ ኢትሐልፍ እምኦሪት ወእምነቢያት እስከ ሶበ ኩሉ የትገበር ወይከውን....."።"ኢትዮጵ" በሚለው መቅድማዊ ስማ ላይ "ያ" የምትለዋን

መድረሻ ሆኖ በመጨመር "የየውጣን"ስመ–ሕግ ማቀናጀቱ፣የኢትዮጵያን ዘለዓለማዊ ሕያ ውነት ለማመሣከር የቀረበ ጉልህ ማስረጃ ነው። (የፈደሎችን አሐዛዊ ስሌት፣ መቀመር የሚችል ሁሉ፣ምንነቱን ፈልፍሎ መረዳት ይችላል!!)።.......የቅድመ ታሪክ መገኛና፣ለሰው ልጅም ምድራዊ ሕይወት ቅድምና ያላት ጥንታዊትና ታሪካዊት ሀገር መሆንን፣ ነጭሌው ሳይቀር ለማስተባበል ሞክሮ ሳይሆንለት ቀርታል። ስለዚህም ነው፣ይህን ሀገራዊና ሕዝባዊ ሃቅ ለማስተማርና፣ተቃዋሚዋንም ለማሳመን ሲሉ፣ምሁራኑ ልጆቻ ሁሉ –"ኢትዮጵያ ያሉ ሁሉ ወዮላቸው!" የሚል ከባድ ንግርት መኖሩን ቢያውቁም፣ፈራ ተባ ሳይሉ፣ሠቃዊ ትጥ ቃቸውን ጠበቅ አድርገው፣ ከገጠማቸው መርግ ጋር ፊት ሊት ሲጋፈጡና ሲጋተሩ ኖረ ዋል። በዚህም መራራ ትግላቸው አንፃር፣የከፈሉት ውድና ክቡር መሥዋዕትነት፣በቀላሉ የሚታይ አይደለም።............

በዚህ እትም ውስጥ፣ከበዙው ባጭሩ ተወጣጥቶ፣ መለስተኛ ገድላዊ ታሪካቸው የሠፈረላቸው ወገኖቻችን፣ስለእናት ሀገራቸው "ሃቃዊ ምንነት" ሲያስተምሩና ያለማወላወልም በአደባባይ ወጥተው ይፋ ሲመሠክሩ፣በዕቡያንና በእኩያን ፋሽስታዊ ግፍ ተፈፅሞባቸው፣መሥዋዕትነት ከፍለው ያለፉ ቆራጥ ወገኖች ናቸው።ለዚህ ገድላዊ ታሪካ ቸው መሠረታዊ መነሻ ያደረግሁት፣ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት፣እነሱ ሕያው በነበሩበት ዘመናት፣ይጽፉልኝ የነበሩትን ደብዳቤዎቻቸውን ነው።

ጨካኙ ሞት፣የሰው ልጆች ወይም ፍጡራን ሁሉ፣የማያልፉት ዕዳ በመሆኑ፣ የሚፈሩት አይደለም። ምናልባት፣ የአስፈሪነት መልክ የሚታይበት ሁኔታ ቢኖር፣ በራሱ ሕጋዊ አመጣጥ ሳይሆን፣ "ሰው ራሽ" ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው። በተለይም ፣ የሰውን ልጅ ክቡርነትና የሕይወትንም ትርጉማዊ ምንነት በማያውቁና ድንቁርና በሚነዳቸው መኃይም ናን ባለጌዎች፣የነፍስ ማጥፋት አረሜናዊ ድርጊት ሲፈፀም፣የሞት ምንነት ይበልጥ አስቀ ያሚና አፀያፊ ትርጉም ይሰጠዋል። ከሁሉም ከሁሉም ደግሞ፣የነሪውን ሰው ኅሊና እጅግ የሚያበግነው፣እነዚህ ንፁሐንን ያጠፉ ነፍሰ ገዳዮች፣ዛሬም እየተዝናኑ በሕይወት ለመኖር መቻላቸው ነው።ሌላው መሰል ፍጡር በሕይወት እንዳይኖር በነፈጉት ዓለም ውስጥ፣እነ ሱ፣ያ ለአንዳች ሥጋት ለመኖር መቻላቸው፣የማችን ወገኖች ቆሽት ያደርቃል። ከዚያም

ጥቃት ሁሉ ይለቅ ይብልጥ የሚቆጠቁጠው፣ስተተነቢው ትወልድ መቀጣጨ ይሆኑ ዘንድ፣ ከፍትህ መድረክ ላይ ቀርበው፣ስፈፀሙት ወንጀል ተገቢ ዋጋቸውን አለማግኘታቸው ነው ተገቢ ፍርዳቸውን ሳያገኙ ቢኖሩ፣ሕይወት ራሱ ትርጉመ ቢስ ይሆናል።ሕልውናም መቅኖ ያጣል።"....ምሕረት አለያም ይቅርታ ወይም እርቀ ሰላም" የሚባሉ ፅንሰ ሐቦች፣በሃይማኖ ቶች አድባራትና በሞራሊስቶች ቤተ ምርምር ውስጥ፣ያራሳቸው የሆነ ልዩ ቦታ ያላቸው መሆኑ ቢታወቅም፣ በበኩሌ "....ሆነ ተብለው በማወቅ ለተደረጉ ወንጀሎች፣ተመጣጣኝ ቅጣቶችን በአፀፋው ሊፈፀምባቸው እንደሚገባ የማምን ሲሆን፣ እንደአሪቱ "ለተመጣጣኝ አካላዊ ጥፋት፣መሰል አካላዊ ቅጣት መደረግ አለበት !" የሚለው ሕጋዊ ውሳኔ የፀና ነው

ይህን ግላዊ ውሳኔዬን በሚመለከት፣ቀደም ሲል ከአሥር ዓመታት በፊት ታትሞ በተሠራጨው – "ቀርጠሃት ጣልልኝ ?"– በሚለው ማኅደረ ግጥሜ ውስጥ "መር ሳትን ነው መርባት" በሚል ረዕስ፣ በሚያመረቃ ይዘት አብራርቸአለሁና ይመልከቱልኝ። ያ አዳፋኝ ግጥሜ፣ በሕምረትና በይቅርታ ፅንሰ ሐሳቦች ላይ፣በማያዳግም አንድምታ የቀ ረበ ቀጥተኛ ምግታር ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፣በዚችው መከረኛይት ሀገራችን ውስጥ፣ አስፈላጊ ባልሆኑ ጥቅንጥቆች ተወጥረን፣እንደ ሀገርና እንደ ሕዝብ ልንሠራቸው የሚገባንን አያሌ ተግባሮ ች፣ለማከናወን ሳንችል ኖረናል። ከነዚህም አንዱ "ነሪዎች ሕያዋን – በሞት ለተጠናቀቁ ሙታን ወገኖች"-(ከተዝካርና ከቁርባን ባሻገር)- ምድራዊ ሥጋቸው ውዳቂ መሆኑ ቢታወ ቅም ቅሉ፣ሕያው ለሆነው መንፈሳቸው(ነፍሳቸው)፣ቃሚ የሆነ የዝክረ ሕይወት ማስታወሻ በተገቢው መልክ ማዘጋጀት አለመቻላችን ነው።በሌላው ዓለም እንዲህ ያለው ሥነ ጽሑ ፋዊ የሙታን ማስታወሻ ቅርስ ፣ "ገድል" በመባል የታወቀ ነው ። አይብዛም አይደግም እንጅ፣ በሀገራችንም ጅምሩ ነበር። "ዘወጠነ ኢይፈጽም!" የሚባለው ወጣሪ ማገቻ ሠንጎ አስቀርቶት እንጅ ! በማስረጃነት፣እንደ ገድለ ተክለ ሃይማኖት(አቡነ)፣ገድለ ዜና ማርቆስ (አቡነ)፣ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ(አቡነ)........ወዘተ. እነዚሁም እንካ ተጽፈው የሚገኙት በክላሲካሉ የግዕዝ ቃንቃችን እንጅ፣በዘመናዩ አማርኛ አይኙም።አብዛኛዎቹ "ገድለ ሰማ ዕታት" ግን፣ከሌሎች ሀገሮችና ባሕሎች በትርጉም የተመለሱ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ

እንደ ገድለ እስጢፋኖስ፣ገድለ መርቆሬዎስ፣ገድለ ቀውስጦስ፣ገድለ ፊቅጦር.....የመሳሰሉት ይገኙበታል።ከውጭ የመጡና ከባዕዳንም ባሕል የሠረፁ ቢሆኑም፣የሰውን መንፈስ ለማጠንከርና ለማፅናት፣ ከፍተኛ የአስተምህሮ ተመክሮ ሰላላቸው፣ጠቃሚነታቸው አሌ የሚባል አይደለም። እንደዚያ ያለውን የሰው ልጆች ቅርሥ፣ ለመከባከብና ለማዳበር የሚያስችል ተቃማት (Institution) በሌሌበት ገዋ ክፍተት ውስጥ፣ በግለ ሰብ ደረጃም ቢሆን፣መንፈሱ እንዲኖር መታገል፣ከፍተኛ ቁም ነገር ነው።የዚችም እትም አይነተኛ ተልእኮ፣በተቀዳሚ ደረጃ ይኸው ይመስለኛል።እንዲህ ያለው ልዩ አስተዋፅኦም፣ከገድልነቱ ባሻገር፣እጅግ ለተጠማው የዘመናችን መዝገበ ታሪክ፣ከፍተኛ አለኝታነት ይኖረዋል።አንድ ሀገርና ሕዝብ፣ለራሱ ሕይወትና ህልውና መከበር ሲሉ፣ በተጋድሎ የወደቁለቱን ልጆቹን ከማስታወስ የበለጠ፣እንደ ሀገርና እንደ ሕዝብ ሊከውነው የሚገባው ቁም ነገር አይኖርም።እናዲህ ያሉት የቅን ታጋዮች ገድል ተመዝግቦ ቢቀመጥ፣መጭው ታዳጊ ትውልድ የሀገርና የሕዝብ መውደድን ሊማርበት ይችላል።አርአያነቱ ከፍተኛ በመሆኑም፣አዳዲስ አርበኞችን፣ሀገር ወዳዶችን፣ጀግኖችን፣አፍቃርያነ ሕዝብን፣ለባንዲራቸው ታጋዮችን......ወዘተ. በየዘመኑ ዕርከኖች ላይ፣ለማምረትም ያስችላል።

"ዝኒ ከማሁ" እንዳይሆንብኝ እንጅ፣ከላይ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት፣ለነዚህ ገድላውያን ድርሳናት፣ መሠረት እንዲሆኑኝ ያደረግሁት፣ ነዚሁ መዋትያን ወገኖቼ ሲፅፉሉኝ የኖሩትን የየግላቸውን ደብዳቤዎች ነው። "እንዴው የቃንቃ ነገር" ሆኑብኝ እንጅ ደብዳቤዎች(ጦማራት) ያልካቸው፣ በያዛቸው ትምህርት፣ ፍልስፍና፣ የተለያዩ የዕውቀት ዘርፎች.........አንፃር፣ ከታላላቅ አስተምህርአዊ መድበላት የሚመጣጠኑ፣ ማኅደረ ጥበባት ናቸው። በተለያዩ አግጣቻዎች የሚያተኩሩና በተለያዩ የዓመታት ወቅቶችም በየጊዜው ይፅፉልኝ የነበሩ ደብዳቤዎቻቸው፣በሚያሠፍሩአቸው እንደወለላ ማር የሚጥሙ ትምህርታውያን ሐሳቦቻቸው ከፍተኛ ዕሴት ያላቸው ነበሩ። አብዛኛው ሰው እንደሚያደርገው ፣ የደረሰውን ደብዳቤ ካነበበ በሃላ፣ ወይ ቀዶ ይጥለዋል፣አለያም በነድ ያቃጥለዋል ። እኔ ዘንድ እንዲያ ያለ ድርጊት አይሞከረም። እንዲትም ደብዳቤ፣አልጥልም ወይም አላነድም።ዛሬ በስደቱ ዘመን፣ እነዚያ ያስቀመጥካቸው የወዳጆቼ ደብዳቤዎች ባይኖሩኝ ኖሮ፣

ለመሆኑ መን ገዋና ዶሎሎ ይውጠኝ ነበር ? የብቸኝነትና የትዝታ አንዳጅ ስሜት በተነሳ ብኝ ቁጥር፣ እነሱው ላይ ነው፣ ወርጄ የምነጠፍባቸው። በርግጥ ሲያፅናኑኝና ሲያበረታቱኝ የኖሩት እነዚሁ፣መጠን የለሽ፣የዘመድና የወዳጅ ደብዳቤዎች ናቸው። ከብዛታቸው የተነሳ፣ሲራራ ነጋዴ ጌኛና አጋሰስ ጭኖ፣ጎረደማት የሚነዳው ልፍ አዕላፋት ኮተት ይመስላሉ – የጦማሮቹ መጠነ ብዛት።

ለደብዳቤዎቼ በገፍ መኮረፍ፣አንዱና ዋናው ምክንያት፣እኔው ራሴ ሳልሆን የምቀር አይመስለኝም። ምክንያቱም፣ለሚደርሰኝ ደብዳቤ ሁሉ፣ የያዘው መልእክት ትንሽም ትልቅም ይሁን፣በአፋጣኝ መልስ የመስጠት ከፍተኛ ልምድና ዲስፕሊን አለኝ።አሁን አሁን፣በዕድሜውም ይሁን በየጊዜው በሚፈፀምብኝ በደሎች ተፅእኖ የተነሳ እንደሆነ አላውቅም፣ ያንን ለብዙ ዘመናት ሳካብተው የኖርኩትን ደብዳቤዎች የመፃፍ ባሕሌን ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነስኩና እየነደልኩ ለመምጣት ተገድጃለሁ። ሰዎችም ለኔ እንዲፅፉልኝ ከሚያስገድዳቸው ዐረቦኖች (ምክንያተ መንሥዔ) እኔ ተጀምሮ እስኪጨረስ፣የችግሮችና የፈተናዎች ማኅደር በመሆኔና፣በአንፃሩም የሚያውቁኝ ሰዎች ሁሉ "አይዞህ!በርታ!" እያሉ የሚደግፉኝ ሰዎች፣ በብዛት በመታደሌ ነው። አለበለዚያማ፣ ቀደም ባለው ዘመኔ "አዲዮስ!" ብዬ እንደነገሩ እጠናቀቃ ነበር። እነዚህ የወዳጅ ዘመድ ደብዳቤዎች ሁሉ፣ በጥቁሩ ይሕወቴ ውስጥ፣ልዩ ፀዳለ ብርሃን ሲፈነጥቁልኝ የኖሩ፣የማለዳ "ዠምበር" ናቸው። ቀደም ሲል ከሀገሬ ጀምሮ የተጠናወተኝ ፈተናና ችግር፣ እየተከታተለ በማሳደድ፣ ካለሁበት የስደት ሀገር ድረስ ከች ብሎ መጥቶ ፣ወደፊት ምን ማድርግ እንደሚቀረው ባላውቅም፣ በነጭሴው ከፍተኛ የፍርድ አደባባይ አስቀርቦ "በእብድነት" እስማስፈረጅ አድርሶኛል።ድሮውንስ ቢሆን፣ሳልጠፋ የዘመናት ዕርከን "ወይ ቀደም አድርጎ በፊተኛው ዘመን፣ አለያም ዘግየት አድርጎ በሃለኛው ዘመን ላይ፣ መፍጠር ይችልስ አልነበር ? ሳይ ቸግረው፣ እዚህ እኛው አለንበት ትውልድ ላይ ከመሠገኝ በሃላ፣ "ችግር ጠበሰኝ፣ፈተና ቆላኝ!.... ብሎ መጨህና እሪ ማለቱ ምን ፋይዳ አለው ? ምንስ ጠቀሜታ ይኖረዋል ? ሆኖም ጥሎ አይጥልምና፣በየጊዜው ምግበ ሕይወትን በደብዳቤያቸው አማካይነት እያቀረቡ የሚመግቡኝ፣ወዳጅ ዘመዶቼን በማግኘቴ – "እግዜር ሲጣላ ጨርሶ አይደለም። መውጫ

መገቢያውን በር ግጥም አድርጎ ሲከረችም፣ለማፅናኛ የሚሆን፣መስኮቱን ገርበብ አድርጎ ይከፍተዋል!" እንደሚባለው፣ለኔም መፅናኛና መካሻና፣እንዲሆኑኝ አስቦ፣ ደብዳቤ የሚፅፉልኝን ወዳጅ ዘመዶቼን በገፍ አዘጋጅቶልኛል። ምሥጋናም የሚያሰጥ "ትሩፋት" ቢኖር ይኸው ነው።አለያማ – "ከማን አንሼው ጥያቄ" ይነሳል።.....ሌላው ሌላው ቢቀር እንካ፣ እንደማንኛውም ተራ ኢትዮጵያዊ፣በሀገሬ ምድር ላይ፣እንደብጤቴና እንዳቅምኪ፣የተወላገደች ትንሽ ዛኒጋባ ቀልሼ፣እንዳቅሚኪም ትደር ንብረት መሥርቼ፣በመለስተኛ ተድላ ደስታ መኖር የሚያቅተኝ አልነበርኩም። ያ ያ ደግሞ፣እንደማንኛውም ተራና ተርታው የሀገሬ ዜጋ ሁሉ፣ላገኘው የሚገባኝ "የሰብአዊነት መብቴ" ነበር። በነዚያ ምትኩ፣ሳየው "ስተገብረው" የኖርኩት፣"መከረና ችግርን እሹሩሩ!! እያልኩ በማባበል ነው።ይኸ ይኸን ማንሳሳቴ፣ለቁጭቴ መገለጫ ለማድረግ ሳይሆን፣ ከወዳጅ ዘመዶቼ ጋር፣ ደብዳቤ ስፃፃፍ በመኖሬ ያተረፈልኝን ፀጋና በረከት ለመግለፅ ስል ነው። ከዚያም አልፎ ተርፎ፣ የደብዳቤዎቹ በዚያ አይነት ክምችታዊ ይዘት መሠከት፣ በሀገራችን እምብዛም ያልተለመደውን "መጽሐፈ ገድል" በዚህ በምታዩት መልክ፣በበኩሌ ለመፃፍ የመጀመሪውን ዕድል ሊያጎናፅፈኝ ችላል ። በተለይም – "አሮጌ ደብዳቤዎቼን" ሁሉ፣ወይ ቀድጄ አለመጣሌ፣ አለያም አቃጥዬ አመድ አለማድረጌ፣ያለፉ ሙታን ወንድሞቼን "ዝክረ ሕይወት"ከትቦ፣ለመጭው ተረካቢ ትውልድ፣ በታሪክ መዝገብነት ለማስተላለፍ በመቻሌ ፣ መለስተኛ የሆነ ቅዱስ ኩራት ተሰምቶኛል።.....................................................

........................በርግጥ፣በየዘመኑ የታሪካችን ኪደት ላይ እምብዛም ባይዘወተርና ባይለመድም፣እንደ ሥነ ጽሑፍ የድንበሮች መገናኛ ድልድይ በመሆን፣ አልፎ አልፎ ከውጭም ቢሆን ብልጭ ድርግም ሲል ኖራልና፣ ወደ ፊት በዚሁ በሀገራቸውን ውስጥ ተወልዶ መመንደግ ይኖርበታል – "ገድል!"።በበሙሌ፣ እንደ አዲስ ውጥኔ በማድረግ፣እነዚህን "እነአምስቱ – "መከረኞች" ጆባ ብያለሁ።በምንባቡ ይቅናዎ!

□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□ (ገሞራው) □□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□□

# የአድራሻዎች መጠቆሚያ !

("ማውጫ !" – እንደሚሉት ያለ)


| ተ.ቁ. | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 1 ኛ – | ሥርወ መሠረት | 5 |
| 2 ኛ – | የአድራሻዎች መጠቆሚያ | 13 |
| 3 ኛ – | ዶክቶር አጓስ ገብረ ዮሐንስ | 15 |
| 4 ኛ – | ደራሲ አቤ ጉበኛ | 94 |
| 5 ኛ – | ሻምበል አሸቱ በቀለ | 111 |
| 7 ኛ – | መምህር አሰፋ ማሩ | 150 |
| 8 ኛ – | ገጣሚ ጸጋዬ ገብረ መድኅን | 197 |


######&&&&&&&&%%%%%%%%&&&&&&&&######



ጸጋዬ ገብረ መድኅን

1929 — 19 ?

(መምህረ ትግል)

# እርሱ ራሱ በደብዳቤው ሲናገር

# እንዲህ ብሎ ነበር !

6/1/77

”......ለውድ፡ ወንድሜ፡ ጎይቶ፡ ገ/ዮሐንስ፤

እንኳን፡ ለዘመነ፡ ማቴዎስ፡ አደረሰህ፤
●●●●፡ አልፋ፡ አልፋ፡ (አንዳንዴ፡ ማስታወሻ፡ ሊደገኝ፡
ነው፡ መስሎ፡) ከባንተ፡ ደኅንነት፡ ይጸፋልኛል፡፡—
ለመሆኑ፡ እንዴት፡ ነህ፡ ጂሎ፤ ያሏችሁ አቦችንስ፡ ወሬ፡
ታገኛለህ? ሰሞኑ፡ ጨቅዩ፡ አሁን፡ ደክሞ፡ ይሉ፡ ይሆናል፤
የዘመኑን፡ ርዝመት፡ ያስታወሰኝ፡ ደርግ፡ ነው፡ በቀደምለት፡
ይቀሰቀስል፡፡—በዋና፡ ጠላት፡ ደርጊ፡ ደግሞ፡ የሚቀርብለት፡
ደርግ፡ ካልሆነ፡ ኢሕአፓ፡ ነው፡—ነፃ፡ የሆነ፡ ሕዝብ፡
ነጻነት፡ ያለው፡ ድርጅት፡ ጠባቂ፡ ነው፤ ሁሉ፡ ነገር፡ በኔ፡
ቁጥጥር፡ ሥር፡ በኔ፡ የበላይ፡ ጠባቂነት፡ ግቢ፡ ናት፡፡—
ለሕዝብና፡ ለሕዝብ፡ መካከል፡ ለርጅም፡ ጊዜ፡ የሚቆይ፡ ጥላቻ፡
እንዲነግሥ፡ በየጊዜው፡ እያቀረቀሩ፡ ሥርዐ፡ የማይወቅት፡
ሀገር፡ ዚደ፡ ቅርበት፡ እንጥፉልኝ፡ ይላል፡ እንደሚገባው፡
ባንገር፡ ምብጥር፡ እያሉ፡ ሆድ፡ ዕቃዎን፡ በማይወቅት፡
ዘንድ፡ ታናፋሉ፡፡—እዚህ፡ ላይ፡ ያነሣሁት፡ ተቋም፡ ተገባር፡
የማይቀነጥር፡ ነውጌን፡ ለመዘርዘር፡ የምፈልግ፡ ሆኜ፡
ካልሆነ፡ የጠባብ፡ ብሔረተኞችን፡ ሴራ፡ ተዘክሮታችሁ፤
የሕዋርያነት፡ ሥራችሁን፡ እንዲታዘዝ፡ ነው፡፡—
ጉር፡ ደግመው፤
ጸገረ ወልደ ነገሩ ፲፩ወደሌት፡●●●●●● ነበሩ፡ ጽፎ፡—


ያንተው [illegible] ●●●●●”

# የእስረኛው ፀጋዬ ገብረ መድህን

(ደብተራው)



# ያልታሰሩ ነፃ ደብዳቤዎች!




(ገሞራው – ሀገረ ስዊድን)


1990-1998



# የእስረኛው ፀጋዬ ገብረ መድህን

(ደብተራው)

# ያልታሰሩ ነፃ ደብዳቤዎች!




## (ገሞራው – ሀገረ ስዊድን)

### "ናስተማስለኪ!"

"........የሚገለጥበት – አሳብን አሳክቶ ፣
መግጠም ቀርቷል አሉ – በስድ ተተክቶ ።
ምንኛ ቂል ናቸው – በጣሙኑ ጅል ፣
መግጠም ከቀረማ – ሀረግ ይጠፋል ።
እኔ ምን ተዳዬ – ሀረጉ ቢጠፋ ፣
ለተወዳሽና – ላወዳሽ ካልከፋ ፣
በገና መቃኘት – የኔውማ ተሰፋ ።........"
የተራራ መቅረዝ – ይልሻል እውር ፣
ያለቦታው ገብቶ፣በማያውቀው ነገር – ሲሆን ምስክር !
ብርሃን ቢኖር ነወይ ? – የተመሰግሁ ዱር !
ተአጋም መካከል – ተጥቅጥቅ ቆንጥር ።..............ወዘተ.

(ለዩኒቨርሲቲ የግጥም ውድድር፣በ1959 ቀርቦ፣በሁለተኛነት ካሸነፈው የፀጋዬ ግጥም፣ጥቂቶቹ ዘለላዎች)

በአሁኑ ትኩስ ትውልድም ሆነ በአንጋፋው ትውልድ መካከል፣ትምህርተ መንፈስን፣ ከትምህርተ ስጋ ጋር በተዋህዶአዊ ስምረት አጣምረው የሚገኙ ወገኖች፣ቁጥራቸው ብዙም አልነበር። አልፎ አልፎ እንደጎመራ የማሽላ እሸት፣ የፈርጥ ያህል ሰገግ ብለው ከመካከላችን ብቅ ብቅ ሲሉ፣ "ምሉእ በኩለሄ" የሆኑቱ እሊህ ህዳጣን ወገኖች፣ ለብዙሃኑ ወገኖች ግርማ ሞገስ ሆነው ይታዩ እንደነበር የማንዘነጋው ነው።ከነዚያ ህዳጣን ብሩሃን ካዋክብቶች አንዱ - "ዛሬ በትግራይ የበረሃ አዘቅታዊ ጉድጓድ እስር ቤት"- በመሰቃየት ላይ የሚገኘው፣ባለቅኔው ፀጋዬ ገብረ መድህን (ደብተራው) አንዱ እንደነበር፣የግጥሞቹንና የሳልሳዎቹን ዘመናት፣ በዩኒቨርሲቲ አካባቢ ያሳለፈ ምሁር ሁሉ፣ ወለል ብሎ

እንደሚታየው ሊጠራጠርም። ራሱ ከላይ በተጠቀሰው ግጥሙ ውስጥ እንደጠቀሰው።

"...የተራራ መቅረዝ – ይልቁል እውር !

ያለቦታው ገብቶ፣በማያውቀው ነገር – ሲሆን ምስክር ፣

ብርሃን ቢኖር ነወይ ? – የተመሰገሁ ዱር !

ተአጋም መካከል – ተጥቅጥቅ ቆንጥር !........"

አንደኛው የቅኔ ባህርይ፣ከህገ አመክንዮ (ሎጂክ) ጋር መጣወሩ ነው። ፀጋዬ እንደተቀኘው –"አንድ ሰው አይኖቹ ከታወሩ፣እንዴት አድርጎ ነው ስለ ብርሃን ጉዳይ አንስቶ መመሰከር የሚችለው ? እንዴትስ ሆኖሎት ነው ? በተራራ ላይ ስለተተከለ መቅረዝ ምንነት ደፍሮ መናገር የሚችለው ? "– ቅኔኛው ፀጋዬ ከግእዙ ቅኔያዊ ስሪት "ንፅፅር" የሚለውን ስርአታዊ ዘዴ ተጠቅሞ፣ብርሃንን ከፅልመት (ከጭለማ) ጋር ጎን ለጎን በማቅረብ፣ምንነታቸውን ከነውጤታቸው ጋር አሳይቷል።"መኑ ዘደመሮ ለፅልመት ውስተ ብርሃን"እንዲል፣የብርሃን አዝመራና ምርት "ነፃነትና መብት" እንደሆኑና፣በአንፃሩም የተገራሪው ፅልመት(ጭለማ) ውጤት "ባርነትና ጭቆና" እንደሆኑ፣በልዩ ቅኔያዊ የአገላለፅ ስልቱ ገልፆታል።

በርግጥም "ከዘመናት የጦፈ ትግል በሂላ፣ዛሬ ብርሃን ይወጣል እያልን ወደሰማያት ስንጠራራ –"እናት ሀገርን እናድን!" በሚለው የጋራ አላማና ግብ ላይ፣ደፉ ቀና፣ላይ ታች ሲሉ የኖሩ ታጋዮች ሁሉ፣በስተመጨረሻ ላይ፣የጋራ የነበር ጠላታቸው ተገርስሶ ሲወድቅ አንዱ ሌላውን "ሾኬ መትቶና ሞባ ሰርቆ"በጠላትነት በመፈረጅ፣ሌላው አምባ ገነን ሲሰራው የኖረውን ደባና ፍዳ፣ እንደገና መልሶ የትግል አጋሩ በነበረ ወገኑ ላይ ሲፈፅምበት፣ ከማየት የከፋና የባሰ "የብርሃንና የፅልመት ተምሳሊትንት" አይሰማማውም ትሉኝ ይሆን?

አዎን! ዛሬ "ብርሃን ባለመኖሩ" ራሱ ቅኔኛው ፀጋዬ እንዳለው "ራሱ ከትገራይ የበረሃ ዱር ውስጥ ተመሰገ" ቢማቅቅ ፣ ይህን ያህል ረጂም አመታት፣ ባልኖረም ነበር! እሾከነቱ እንደሹል መርፌ መጠቅጠቅ ከሚችለውም የአጋምና የጥቅጥቅ ቆንጥር ውስጥ ተጥሎ ያንን ያህል ዘመን ባልተሰቃየም ነበር። እንዴው ለመነሻው ያህል ወደ ቅኔያኛው የቀድሞ ስራዎቹ ጎራ አልኩ እንጅ ፣ ከፀጋዬ መድበላዊ የቅኔ ስራዎቹ ውስጥ ዘልቄ ብገባማ ኖሮ "እንደ ዘውዱን ብገለብጠውማ ኖሮ....."እያለ ከሚያርቀርበው – ዘውድ ከጎፈር–ጨዋታ ላይ የበረቀ ጉባኤ ቃናዊ ቅኔው ብቻ፣ስንቱን ባናገረኝና ባጠበበኝ ነበር።

የዚህ መጣጥፌ አለማዊ ተልእኮ፣በርእሱ እንደተጠቀሰው፣ወዳጄ ፀጋዬ፣በዚያ
ጥድፊትና ተግባር በገነነበት ዘመን፣ከነበረችው ቅንጭብ ጊዜው እየቆጠበ፣አስቸጋሪና ወ
ጣሪ በሆነው የበረሃ አካባቢ በየጊዜው እየፃፈ ይልክልኝ የነበሩትን ደብዳቤያዊ ሃሳቦቹን፣
መሰረት በማደረግ "ቅኔኛው ፀጋዬ ምን አይነት ወንድም እንደነበረ ለማሳየትና የበጎና የታ
ታሪ ወገኖች የህይወት ፅዋና እጣ ምን ያህል መሪርና ጎምዛዛ እንደሆነ ለማገናዘብ ነው።

አሁንም የሚገኝበት ሁኔታ ግልፅና ብሩህ ስላይደለ፣ የደብዳቤዎቹን ይዘትና
አይነት መምረጥ ይኖርብኛል። (በነገራችሁ ላይ ፣ ከወዳጅ ዘመድ በየዘመኑ - ላለፈው
አንድ ኑብ ምእት አመት - እያገኘሁ ያከማቸሁቸው ደብዳቤዎች ቁጥር፣ ወደ ግማሽ መቶ ሺ
እንደሚደርሱ ብገልፅ ይደንቃችሁ ይሆንን ? – ያውም አብዛኛዎቹ በየፖስታ ቤቱ ነቀዞ
ችና ተባዮች እየተበሉብኝ እንጅ፣ብዛታቸውማ የትየለሌ ነበር....!!!)

እንግዲህ ደብዳቤዎቹን መሰረት በማድረግ ለምፅፋቸው መጣጥፎች ሁሉ፣
ተልእኮው ግልፅ ሊሆን ይገባል።ብዙ ጊዜ አዘውትሬ ከምጠቀምባቸው መርሆአዊ መመሪ
ያዎቼ ውስጥ አንዱ - "እንደበት ላጣ ህዝብ – አፍ ማለት" እንደሆነ፣ብዙሃን መግለጫዎ
ች አስተሳልፌአለሁ።ለደብዳቤዎቹ መፃፍ ዋናው መነሻ "የደብዳቤዎቹ ባለቤቶች – ወይ
በህይወት የሉም (ተጠናቀዋል)አለያም በማያፈናፍን ወጥመድ ተይዘው ፍዳ ፈጠቃቸውን
በመብላት" ላይ የሚገኙ ናቸው።በነዚህ ተከታታይ የደብዳቤ አቅርቦታዊ መጣጥፍ ተራ
ላይ፣ቀዳማይ ቁጥሩን የያዘው፣በገዛ ደጁ ላይ በፋሽስት ነፍጠኞች የተገደለው የወዳጄ–
የታጋይ አሰፋ ማሩ ደብዳቤዎች ሲሆኑ፣አሁን ደግሞ በቁጥር ሁለተኛነት የቀረበው፣የወዳ
ጄ የቅኔኛው፣ ለእናት ሀገሩ ነፃነትና ለብዙሃን ወገኖቹ መብት በታገለ፣ እንደበደለ ወንጀ
ለኛ ተቆጥሮ፣ በዘረኞች የባንዳ ቡድን ብያኔ ፣ እንደአውሬ በበረሃ የጉድጓድ እስር ቤት
ውስጥ በመማቀቅ ስለሚገኘው ወንድም ደብዳቤዎች ይሆናል።በዚህ ረድፋዊ ይዘት(ፓተ
ርን) ልፅፍ ያዘጋጀሁቸው መጣጥፎች ብዙዎች ሲሆኑ፣በቀጣይነትም ቅደም ተከተላቸውን
አስተካክለው፣ደርግ ቀጥቅጦ በሽተኛ በማድረግ የገደለው የፍልስፍና ሊቁ ዶክቶር አጋለ
ደብዳቤዎችና የታዋቂው ብእረኛ – አቤ ጉበኛም ይገኙባቸዋል።)

የመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀዳምያን ደብዳቤዎቹ፣ገና የዱር ቤቱን በማዘጋጀት ላይ
እንዳለ የፃፋቸው ይመስሉኛል፣ የተጠቀመበት መፃፊያ "ደረቅ እርሳስ" በመሆኑ (በመደብ

ብዙ)፣ለህትመት ስላላመቹኝ ላወጣቸው አልቻልኩም።የደብዳቤዎቹ ይዘታዊ እምብርት ስለድር ሰፈሬ ማለትም የሰማእቱ እስጢፋኖስ ደብር አውድ ስለነበረውና በተለይም የኳስ መጫዋቻችን ስለነበረው "የራስ ብሩ ሜዳ"፣ ወደ ደርግ አውድነት መለወጥ ጉዳይ በም ፀት ዘዬ የተረከበት ነው ። ያንን ሰፈራችንን እሱም በተማሪነትና በአስተማሪነት የኖረበት የቅዱስ የቤፍ ትምህርት ቤት አጎራባች በመሆኑ፣ ጥሩ አድርጎ ያውቀዋል።ደብዳቤዎቹ፣ የሰላምታ ቃላቸውን ከደረደሩ በሗላ፣በደብተራዊ የቅኔ አገላለጥ እንዲህ ይላሉ።

"....ያንን የሰማእት ደብር ማርገጃ ሰፈርህን፣ደርግ መንጋ ሰራዊቱን ሰብስቦ በየበአላቱ 'ሲያናፋበት' ይውላል። የሰፈርህ ካህናት ሁሉ ፣ በየበአሉ ወቅት መናፈሻና መተንፈሻ አጥተው እንደተረበሹ ናቸው። ደርግ ዲስኩራዊ ልጋ ጉን፣በሚያስተጋባ ድምፅ ማጉሊያው እያንባረቀ ሲያደነቁራቸው ይውላል...."

ብአረኛ ፀጋዬ ይህን ሃሳብ ሲያነሳ፣ማመላከት የሚፈልገው፣ቀድሞ "መስቀል አደባባይ" በስቷሃላ ላይ ደግሞ "አብዮት አደባባይ" እየተባለ ሲጠራ የነበረውን የሰፈሬን መንጠራወዝ ነው ። ከቶ ቁም ነገር የሚሰራና፣ ለሃገርና ለወገን አንዳች ነገር የሚፈይድ ይመስል፣ህዝቡን በጠራራ ፀሀይ ላይ በግዳጅ አስጥቶ፣የፕሮፖጋንዳ ልጋጉን ሲረጭ ይው ል እንደነበር፣ሩቅ ሀገር ለነበርኩት የሰፈሩ ሰው መተረኩ ነበር። "ሲያናፋበት"የሚለው "አድጋዊ" የቋንቋ መግለጫ እንደሆነ ይጠነቀቋል።በርግጥም "መንደባለያ አመድና አም ቡላ" አይኖር እንደሁ እንጃ እንጅ፣ ያ የቅዱሳን ሰፈሬ፣የአህዮች መራገጫና መንደባለያ ጋጣ ሆኖ እንደነበረ፣ሁኔታውን ዘልቆ የተመለከተ ታዛቢ ሁሉ የሚያስታውሰው ነው።አን ዲት ፍሬና ቁም ነገር በሌለበተ ዲስኩር፣ አስከግማሽ ቀን የሚፈጅ ጊዜ ሲለፋደዱበት፣ ያሳልፉ እንደነበር የሚታወስ ነው ። ለነገሩማ እኛን ከዚያ ተወልደን ካደግንበት አካባቢ አለንጣፍ ምትክና አለተመጣጣኝ ገምት፣አባርረው፣ሰፈሩን በአዳዲስ ህንፃዎች ማንፀባረቅ ይችላሉ ላሏቸው ለነ ሃረጎት አባይ አስረከበን ከሄድን፣ጊዜው ረዘም ብሎ ነበር። የሚያና ፉ እንስሳት ተተኩበት እያለ ፀጋዬ ዳርዳሩን የሚቃኘው፣ያ ያንን አስመልክቶ ነው።በጭ ለማው ዘመን ስንጨናበሰበት ኖረን፣ብርሃን ሲወጣ፣ የሰፈሩ ነባር ነዋሪዎች፣ለቀን ተበታ ትነናል። ያ ጦስ ባስከተለው ጠንቅ፣የተበሳጩት የሰፈሩ አዛውንት አብዛኞዎቹ፣በዚያው ወቅት በብስጭታዊ ሰቀቀን አልቀዋል።'የሚያናፉ' አህያ የሰማ፣ጅብ ሞት፣ጠራርጎ ወስዶ አቸዋል። ካህናት እንደመሆናቸው፣በውስጣቸው "የዜማ፣የቅኔ፣የመፃህፍት..." ሊቃውንት

ስለነበሩበት፣ከበፊሩም ሆነ ከምድሩ የተሰናበቱት ካህናቱ ብዙዎቹውን ሳይሆኑ ፤ ቅጂዎቻቸ ው፣ዜማዎቻቸውና የመፃህፍት አውቀቶቻቸውም፣ጭምር ነበሩ።ፀጋዬን ያ 'ልዩ በንብና' እጅግ ቆጥቁጦትና አንገብግቦት ነው - "የሚያናና ተተካበት!!" እያለ የገለፀው።

አሁን በቀጥታ ወደ ደብዳቤዎቹ ልግባ። ከዚህ በፊት የሟቹ አሰፋ ማሩን ደብዳቤ ዎች ባስተናገድኩበት ስልታዊ አቀራረብ ነው፣የአስረኛውንም የፀጋዬ (ደብተራው)፣ያልታ በሩ ነፃ ጦማራት የማቀርባቸው።ለከፋውም ለደጉም ቢሆን፣የገዛ ራሱን የእጅ ፅሁፍ ከደ ብዳቤዎቹ እያጣቀስኩ፣ቅንጭቦቹን (Extracts) ጸቀርባለሁ።።

« ...ሰውድ፡ ወንድሜ፡ ኀይሉ፡ ገ/የሐንስ፤ 6/1/77
እንኳን፡ ለዘመነ፡ ማቴዎስ፡ አደረሰህ፤
....፡ አልፎ፡ አልፎ፡ (አንዳንድ፡ ማስታወሻ፡ ሲያገኝ፡
ነው፡ መሰል፡) ስላንተ፡ ደህንነት፡ ይፅፍልኛል።—
ለመሆኑ፡ እንዴት፡ ነህ፡ ጂል፤ ያዲስአበቦችንስ፡ ወሬ፡
ታገኛለህ? መምሩ፡ መቼም፡ አሁን፡ ደከም፡ ይሉ፡ ይሆናል፤
የዘመኑን፡ ርዝመት፡ ያስታወሰኝ፡ ደርግ፡ ነው፤በቀደምለት፡ ...»

"....ሰውድ ወንድሜ ሀይሉ ገብረ የሃንስ ፤
እንካን ለዘመነ ማቴዎስ አደረሰህ ፤
....አልፎ አልፎ (አንዳንድ ማስታወሻ ሲያገኝ
ነው መሰል) ስላንተ ደህንነት ይፅፍልኛል።ለመ
ሆኑ እንዴት ነህ ጃል ፤ ያዲስአበቦችስ ወሬ ታገ
ኛለህ ? መምሩ መቼም አሁን ደከም ይሉ ይሆናል፤
የዘመኑን ርዝመት ያስታወሰኝ ደርግ ነው፤በቀደምለት...."
(ጦማር ቁጥር 1 – 6/1/77)

አስረኛው ፀጋዬ - ቀደም ሲል ጀምሮ፣ወላጅ ቤተሰቦቼን በቅርብ ያውቃቸው ስለነበር አረጋዊው አባቴን -"መምሩ መቼም አሁን ደከም ይሉ ይሆናል!"የሚለው ስለማንነታቸው በስርአት የተረዳና ካህናዊ ተልእኮአቸውንም እንደብዙዎቹ ያከብር ስለነበር ነው። ቀደ ም ባለው ዘመን – ያኔ እኔ በየእስርቤቱ ስንገላታና በየፍርድቤቱ ስንከራተት በነበረት ጊዜ ከቤት ድረስ በየጊዜው እየሄደ ፤ ሲያፅናናቸው ከነበሩት ወገኖች ውስጥ አንዱ ስለነበርና "መምሩም በኔ ምክንያት፣ምን ያህል ተሳቀው ስለነበር፣ያንን ያንን ስሜት በማመላከት ነ ው፣በደብዳቤው ላይ "ስለመምሩ ሁኔታ" አስቀድሞ ያሰፈረው። ከፍተኛው ፍርድ ቤት እመላለስ በነበረበት ወቅት ሁሉ፣ካልተለዩት ወገኖች አንዱ እሱ ነበር።ዛሬ እንደዚያ ላለ ከፍተኛ ውለታው፣ወሮታ ለመመለስ በማልችልበት ምድር ጥጋት ላይ ታግሬ በመገኘቴ፣ እጅግ አዝናለሁ። በጨካኙ ደርግ መከሰት ምክንያት፣ 17 አመታት ሙሉ በዱር በገደሉ ሲወጣ ሲወርድ፣ሲወድቅ ሲነሳ፣ጎንበስ ቀና ሲል መኖሩ አንሶት፣እንደገና "መሰል የነፃነት አርማ ይዘናል!!" ብለው በጋርዮሽ አላማና ግብ ተነስተው በነበሩ፣ዛሬ ጨምበላቸው ተገ

ስሙ በሰየሉቸው "ጠባብ የባንዳ ዘረኞች" ናበረሃ ጉድጓዳዊ እስር ቤት ውስጥ ፣ እንደገና እንደወንጀለኛ ፣ ላለፉት ድፍን ሰባት አመታት መታሰሩ ሲታወሰኝ ፣ የምንኖርበት አለም ፀዋግነትና እኩይነት (ማለትም - 'ሺት' - እንደሆነ) በጉልህ የሚያሳየኝ ማጉሊያ መነፅር የሆነ ያህል ይሰማኝል። "መምሩማ – ለአያሌ ሱባኤያት - 'ያንን ልጅ አይኑን አሳየኝ! አያ ሉ አዶናይን ሲወተውቱ ኖረው፣እድል ገጥሞን ሳንተያይ፣ከመድከም አልፈው፣ከአመታት በፊት ተጠናቀዋል። እሳቸውስ፣የእድሜ ባለፀጋ ሆነው፣ወደዘጠና እድሜ ደርሰው ነው፣ያ ለፉት። እንደነገሩም ቢሆን፣ትዳር መስርተው፣ልጆች አምርተው፣ከፍተኛ ምግባረ ሰናይ ሰርተው................የዚህ አለም ስጦታ፣ከለው አለማዊ አቅም በላይ ስላይደለ፣ ወግ ማእርግ አድርሰው ነው ያለፉት።እንደኛ ያለው እንጅ ነውማ አሳዛኙ!! እኔም ብሆን ለሩብ ምእተ አመት፣ የባእዳን ፊት ጠዋት ማታ እየጠበሰኝ፣ በሰው ሀገር ስንከራተት መኖሬ ከቶ ምን ይባላል! ወንድሜ ፀጋዬስ ቢሆን – በገዛ ሀገሩና በገዛ ምድሩ ላይ፣ የወጣትነት እምቦቃቅላ ዘመኑን ሙሉ ፣ እንዴት በዱር ገደሉና በየበርሃው ሲንከራተትና መከራ ስቃዩን ሲበላና፣ አሁን በስተመጨረሻ ላይስ ፣ በአረመኔዎች እጅ ተይዞ በበረሃ ውስጥ በሚገኝ የጉድጓድ እስር ቤት ውስጥ ፍዳውን ይቁጠር !!" ትላላችሁ ? ያ የኛ ትውልድ፣የኢትዮጵያን ህዝብ መከራ መስቀሉን ተሸክሞ ሊታደገው ቢነሳ፣እንደወንጀለኛ ተቆጥሮ ያን ያህል መሰቃየቱ ሌላው ሌላው ቢቀር፣ ራሱ ታሪክ ተጠያቂ አይሆንበትም ትላላችሁን ? ፀጋዬ እንደማንኛ ውም ኢትዮጵያዊ ትዳር መስርቶ፣ልጆች ወልዶ፣ ሀገሪቱ በሚኖራት የኢኮኖሚና የሶሻል ኩነት ውስጥ፣ሰላማዊ ህይወት የመኖር መብት ነበረው። ያ አይነቱ ተራ ህይወት፣ሰብአ ዊ መብቱም ጭምር ነው።ታዲያ ለምን ይሆን ? የማንም ጉንፋናም ተዝናንቶና ተንደላቆ እንደልቡና እንዳሻው በኖረበት አለም ውስጥ፣ እንደፀጋዬና መሰል የጥቁር እድል ተጋሪ የሆኑ ወገኖቹ፣ሽርፍራፊዋን የህይወት ፍርፋራዊ ጣእም እንኳ ሳይቀምሱ፣በደይን ተጨማ ደው ሊኖሩ የቻሉት ? ይህ አይነቱ ጥያቄዬ – በአለሙ ውስጥ አለ ለሚባለው የ"ሞራል፣ የሰብአውያን እሴቶች፣ለፍትህ..."አድባራት፣ዘለአለሜን እሪ እያልኩ ሳቀርበው የምኖረው መሰረታዊና ከባድ ጥያቄዬ ነው!!! በነገራችን ላይ የፀጋዬም ወላጅ እናቱ፣በዚያ በአረዊት ነት ዘመናቸው "ልጄን አሳዩኝ!!" እያሉ እንደተንሰፈሰፉ ነው፣አሁን በቅርቡ እሱ በበረሃ ው የጉድጓድ እስር ቤት እንዳለ የሞቱት።ይህን "መከራና ስቃይ፣ፍዳና ደይን፣ደባና በደ

ለ" ከቶ ምን ይሉታል ? ተጠያቂውስ ማን መሆን አለበት ? እንደ – ታሪክ የመዘገባቸው እንደሰዶምና ገሞራ በእሳት መቃጠል፣ እንደታንና አቤሮን መሬት ውስጥ መስመጥ፣እንደ ህንፃ በቢሉን ተደርብቶ እንክትክቱ መውጣትና....ሌሎችም የመሳሰሉትም ድምሳሴዎች ሁሉ፣ከበስተጀርባቸው አንድ የሆነ "አመክንዮ!"አይኖራቸውም ብሎ መከራከር ከቶ ማን ይችላል ? ዛሬስ በምድረ አየትዮጵያ ውስጥ ቀስ በቀስ እየበረቁ የምናያቸው ክስተቶች፣ የምን ትንግርት ነፀብራቆች ይሆኑን?(ለምን በዚህ ጥያቄ፣ይችኛዋን ክፍል አልከረችምም)

«---- ይኽውልህ፡ ሠፈራችሁ፡ የመንግሥቱ፡ መናገሻ፡
ሆነችልህ፡ "ይደልዎ! ይደልዎ፡" ስትል፡ ስንባተች፡—
የገሞራ፡ መፍለቂያ፡ እንደነበረች፡ ዘንግታው፡ ይሆን?
በል፡ ወደ፡ ፊት፡ በአመ፡ ይመጽእ፡ እንወቅሳታለን፡—— »

".......የኸውልህ ሰፈራችሁ የመንግስቱ መናገሻ ሆንችልህ ።
"ይደልዎ ! ይደልዎ ! " ስትል ሰነበተች ። የገሞራ መፍለ
ቂያ እንደነበረች ዘንግታው ይሆን ? በል ወደ ፊት በአመ
ይመፅእ እንወቅሳታለን ።................................"
(የላኛው ጦማር ቀጣይ ኛቀፅ)

"ጥልቃዊ ምፀትና ሉአላዊ ሰላቅ" ተለይቶት የማያውቀው፣የደብተራው ብሂላዊ አነ ገርና ዘይቤያዊ ስልት - "ሰፈርህ የመንግስቱ ማናገሻ ሆነችልህ!!" በማለት፣በድሮ የእስጢፋኖስ አምባ ሰፈሬን ፣ ከሃረር "ቡቴጋ ቅምቡራ ሲያባርሩ" የኖሩት "ነፍጠኛ ወታደሮች" እንደሚያቀረሹበት አይቶ፣በተለመደ አገላለፅ "የጎንዮሽ" ሲገልፅ ነው ።አዎን! ያች ሰፈሬ ከታወቁት እንደነዜጋመልና ማህበረ ስላሴ ታላላቅ ገዳማት፣በነአርዘሊባኖስና በመሳሰሉት እፀዋትና ተክላት ተደምማ ላያት ሰው፣እጅግ የመሳብ መንገኒቅነት ነበራት ። የሰፈሩም ነዋሪዎች ካህናት፣በገሁሱ ባህርያቸው "አምሳለ ካህናተ ሰማይ" እንደነበሩ፣ ከሀገሩ ርቄ ለረዝም ዘመናት ብኖርም፣ለዘለአለም የማይረሳኝ ነባር ትዝታዬ ነው ።ፀጋዬ "የመንግስቱ መናገሻ ሆናለች" እያለ የሚከሸናት ሰፈሬ፣ መካነ ልደቴ ብቻ ሳትሆን፣በገአዘ ህፃን አእ ምሮዬ ያደገሁባትና የጎለመስኩባት ቤቴም ጭምር ነበረች ። ሰማይና ምድሩ ተሳስሞ ከተ ጋጠመበት አድማስ ባሻገር፣ሌላ ምድርና ሰማይ፣ሌላ ሀገርና በሃውርት የሌለ በማይመስለ ኝ በዚያ የእምቦቃቅላ ዘመኔ፣ ያቺ የእስጢፋኖስ ሰፈሬ እንደ ግላዊ "ዩኒቨርሲም"ነበረች።

ቀደም ሲል ከላይ ባለው አንቀፅ ውስጥ እንደጠቀስኩት፣ፀጋዬም ይማርበት የነበረው፣በስተሟላ ላይ ከተተከለው"የቅዱስ የሴፍ ትምህርት ቤትም"በዚያው ሰፈር የደ በረ በመሆኑ፣እንደዚያ በምፀት የሚፅፈው፣እሱም ራሱ ጭምር፣ ያ መንደር ቅዱስ ሰፈር

ያልነበረውን ያህል፣ የፋሽሽት ማናፊያ መድረክ ሊሆን በመቻሉ፣ ትዝግርቱ ሴጅግ ፍራ ቶችና አንገብጋቢትም ነው። የግዮን ሆቴልን፣የቱሪስት ድርጅትን፣የፊንፊኔ ህንፃን፣የኢስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያንን፣የአፍሪቃ አዳራሽን፣የኢዮቤልዩ ቤተ መንግስትን....አካቦ የሚገኘው የየአመቱ የደመራ ማቃጠያ የነበረው የመስቀል አደባባይ ፣ በስተሿላ ላይ ተለውጦ "የአብዮት አደባባይ" የሚባለው የስንት አይነት ልጋግ መርጨና ይስንት አይነት አንቶ ፈንቶ፣አቲሆ ባቲሆና አርሲ ኩርሲ የቅርሻት ዲስኩር ማስሚያና የምናምንቱ ዝግንትል'ሰላማዊ ሰልፍ' እየተባለ፣ሲተራመስበት መቆየቱን፣ማንም አይዘነጋውም። ያቺ የ "ራስ ብሩ ሜዳ" ትባል የነበረች ሰፍራ፣ታናናሽ የበቀሉባት ችፍርጎቿ ሳይቀሩ ተመንጥረው፣ የእግር ኳስ መጨዋቻችን ነበረች።ፀጋዬ ግን በዚያ ብቻ ሳይወሰናት፣ በሰምና ወርቅ አቀራረባዊ ስልቱ፣ቦታይቱን "የገሞራ መፍለቂያ እንደነበረች ዘንግታው ይሆን ?"ሲል ክረርና ሳብ አድርጎ ገልፆአታል። በርግጥም ሰፈሪቱ ያፈራቻቸው ልጆች ፣አንዳቸውም ቀትረ ቀላልና ነፈዞች እንዳልነበሩ ይታወሰኛልና፣ አባባሉ ትክክል ነበር። እንደነፍቅረ ማርያምን የመሳሰሉ ተርብና እነር ምጡቅ ደራስያን ያፈራች ደብር በመሆኗ፣ላባባሉ ሃቃዊነት አንድና ሁለት የለውም! እንደእድል ሆና ግን፣እዚያው ተድበሰብሰው"አለም የረሳቻቸውን ያህል - ተረስተው ቀርተዋል!!" እንዳለው አይዋ ጂቦን፣ እነዚያም ሊቃውንት የትም ተረስተው ቀርተዋል።

የዚያ ሰፈር ገድልና ስንክሳር በተነሳ ቁጥር፣ ሁልጊዜ ትዝ የሚለኝ "የመላ ሰፈሩ አቅኒዎች ተባርረው፣ እንደነሀረጎት አባይ፣እንደነሰዩም ሀረጎት (በአማቱ ልእልት በኩል)፣ እንደነፊንፊኔው ባላባት (ባላምባራስ)............ሳሉት ሰዎች፣ግላዊና እንጡራ ንብረት ተደርጎ መሰጠቱ ነው።እንደእኛ ያለውማ ባይተዋር ዜጋ፣ከሀገሩ ጭምር ተባረን፣በሰው ሀገር ባል ተወለደ አንጀታችን ስንንከራተት ለሩብ ምእተ አመት ስንሰቃይ ኖረናል !!!!!!! አሁን ማን ይሙት ለዚህ አይነቱ በደላችን ፍትህ የሚሰጥበት "እለተ ፍትህ"(የፍርድ ቀን)አይኖርም ብሎ የሚያምን ስሁትና ጅል ሰው ይኖራል ብላችሁ ታምናላችሁን ? አይመስለኝም !!!!!!!!

ፀጋዬ በዚህ ጦማሩ እንዳለው፣ፍትህማ ካልመጣ "በእመ ይመፅእ" እንወቃቀሳለና !!!!!


...የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከዓመት ፡ ወደ ፡ ዓመት ፡
[illegible] ደርግ ፡ መንግሥት ፡ ጠገበ ፡ [illegible] ፡ የሚገባ ፡
ትምህርት ፡ እያገኘ ፡ ስለመጣ ፡ ልቀስቅሳችሁ ፡ የሚል ፡
እንጂ ፡ ቀስቅሱኝ ፡ የሚል ፡ አይደለም ፡— ደርግ ፡
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]

> "........የኢትዮጵያ ህዝብ ከአመት እስከ አመት
> ስለደርግ መንግስት ጠባይ፣እንጆቱ የሚገባ ትም
> ህርት እያገኘ ስለመጣ፣ልቀስቅሳችሁ የሚል እን
> ጂ፣ቀስቅሱኝ የሚል አይደለም።ደርግ ያስፈራራ
> እየመሰለው፣በሚወስደው የቤት ማቃጠል፣የጎተ
> ራ፣የሰብል ማቃጠል፣ የዘረፋ ፣ቤት የመድፈር፣
> የዱላ የግድያ..እርምጃ፤ ዱር ቁሞ ትግሉን የሚ
> ታዘበውን ሁሉ፣ያለ ውድ ከትግሉ መሃል እየጨ
> መረው ነው።..ይበልጡን የማታገል ስራ፣ ደርግ
> ራሱ እየሰራልን ስለሆነ፣የሚገጥመንን የከድሬ ች
> ግር፣ በአንዳንድ ገፅታ እያቃለለልን ነው ማለት
> ይቻላል ።....................................."
>
> (የቁ.1 ጦማር – ሌላው አንቀፅ)

ይህችኛይቱ የፀጋዬ አንቀፀ ጦማር፣አጭርና ቅልብጭ ያለች ትምሰል እንጅ፣በአዘለ ቻቸው ሃይለ ቃላት አንፃር፣እጅግ ጠጣርና በሳል ሃሰቦችን ያገመረች ናት።ቢያንስ አራት ከፍተኛ ቁምነገሮች አቅፋ ይዛለች።የመጀመሪያው ነቁጥ፣ዛሬ እንከትክቱ የወጣው ደርግ የድቀቱ ምክንያት "ራሱ በራሱ የሚሰራው ድርጊት" እንደነበር መግለፁ ነው። ይህንንም ፀጋዬ "ደርግ ለጥፋቱ 'ልቀስቅሳችሁ የሚል እንጅ፤ቀስቅሱኝ!' በማለት፣በማያሻማ ብሂል ጥሩ አድርጎ ገልፆታል። ሁለተኛው ደግሞ – ደርግ በዘመኑ፣ በንፁሃኑ ባላገር ህዝብ ላይ ይፈፅም የነበረውን አፀያፊ ወንጀሎች ያብራራበት፣አረፍተ ሃሳብ ነው።"የሰብል (ምርት) የጎተራ ማቃጠል፣የቤት መድፈር፣የዘረፋ፣የድብደባ፣ የግድያ........"ወንጀሎችን ጠቅሷል። ሶስተኛው -ዘርአ ፋሽስቶች ራሳቸው በሚፈፅሙት ግፍና በደል፣ደባና ደይን፣ፍዳና ስቃይ ት የተነሳ፣ብዙውን ታጋይ ወገን ያለተጨማሪ የጥሪ ቅስቀሳ፣በገዛ ፈቃዱ ወደ ትግሉ ጎራ እንዲጎርፍ ማድረጉ ነው። "እሳት በሌለበት ጭስ አይጨስም !" ይባል የለ ? የዚያ አንድ ምታና መፈክር ነው።እንዚህን ኩነቶች፣ተራ በተራ ከደረደረ በሂላ፣ ፀጋዬ በአራተኛነት ነጥብ ያሰለፈው ማጠቃለያና መዝጊያ ሃሳብ፣ደርግ ከድንቁርናው አኳያ በፈፀመው ስህተ ት፣ የተቃዋሚዎችን ጎራ ልእልና የሚያሳብጥ ተግባር ራሱ እንደፈጠረው በመግለፅ "የከ ድሬ ጉብሎችን ለማጨት ፣ የነበረባቸውን ችግር አቃሎልናል !!!"ይላል ። "በደልና ደባ ምንጊዜም ሆነ ሁልጊዜ፣አጥፊዋን እመፅ ፀንሳ እንደምትወልድ" የቆየውን ሃቃዊ እውነታ የሚያስተጋባ ሃሳብ፣ ከኑጭብጥ ማስረጃው ፀጋዬ በደብዳቤው ተናግሯል። እንግዲህ እን

ባቢ ሆይ - እንዲህ ያለውን"ተንትኖ አስረጂና፣እውቀትን ፈትፍቶ አጉራሹን ሊቅ ምሁር ነው፣ የውሻ ደናቁርት ወስደው፣ከበረሃ የጉድጓድ አዘቅት እስር ቤት ውስጥ አስገብተው በመቆለፍ፣ላለፉት ሰባት ድፍን አመታት በማሰቃየት ላይ የሚገኙት!ከቶ ምን ይባላል? የሃ ሃገራችን ምሁራን እድል ፈንታ፣ዕዋ ተርታ፣እንዲህ ግፍን እየተጋቱ መኖር ሊሆን ነውን?

በሰለጠነው አለም ውስጥ፤ሊቃውንት የሚለገሱቸው ክብርና ዋጋ፤ ከኛው ጋር ሲነፃፀር የ መንግስተ ሰማይና የጀሃነም አለያም የገነትና የሲኦል ያህል፤ከፍተኛ ልዩነት አለው።ለምን ይሆን? ከሰውም ሰው የሚበልጥበት፤የተፈጥሮ ህጋዊ ስርአት ኖሮ ነውን? አይመስለኝም !!



"......ንቅቻለሁ፤በቅቻለሁ የሚለውን ምሁር ነኝ ባዩን፤ ከዚህ በፊት የወደቁትን ተራማጅ ምሁራን፤የሃሞታቸ ውን አጣቢ እንኳን ቢለግሰው፤ መሰረት ያለው ሰከን ያለ ስራ በህዝብ ውስጥ የሚሰራው አሁን ነበር።ከአ ዲስ አበባና ከሌሎች ከተሞች የሚጎርፈው ሁሉ፤ጠ ንክረን መታገላችንን ያደንቅና፤ታዲያስ ? ሲባል አሜ ሪካንን ሳልሳለም እንዴት አድርጌ ይለናል፤ለምለም ሳር አያንቅፍህ ወደፊት ገንዘብ ቢሆን እያልን በከብ ካብ እንሸኛለን።....እንጀትህንም ደግሞ ይበሉታል። ምን ታደርገዋለህ ?......................."

(የጦማር ቁ.1 ሌላው አንቀፅ)

በዚች ንእስት የአንቀፅ ዝንጣፊ ውስጥ፤ለምድር ለሰማዩ የሚከብድ ታላቅ ጭብጦ ሃሳብ ተንጥፎበታል። ዋናውና አይነተኛው ነቁጥ —"ምሁር ነኝ ባዩን ፤ከዚህ በፊት የወደ ቁትን ተራማጅ ምሁራን፤የሃሞታቸውን አጣቢ እንኳን ቢለግሰው...." የሚለው ነው።እዚህ ሃቅ ላይ ብዙ ማተት ካልተቻለ፤በሌላ ምንም አይነት ነጥብ ላይ ሰፊ ሀተታ ማቀረብ ከቶ አይቻልም።አንድ ያልታተመ መፅሃፌ ላይ "አስመሳይ ምሁራንን" በሚመለከት ያሰፈርኩ ት ግጥም እንዲህ ይላል።

"ኮዝሞቲኩ ምሁር!"

"ፈጥሮለት ይሆናል — ሳምባ መተንፈሻ !
ፈጥሮለት ይሆናል — ልብም ማስታወሻ !
ፈጥሮለት ይሆናል — ያን ጆሮ ለመስሚያ !
ሰርቶለት ይሆናል — ያንን አይን ለማያ !
ፈጥሮለት ይሆናል — ጉረሮ መዋጫ !
ጥብሰና ቅቅሉን — በገፍ መስልቀጫ !
አሽንዳም በሰተታች — ኩሳ ኩስ ማስወጫ !
በርግጥ ሰርቶለታል — ያንን ጥርስ ለመፍጫ!

ሚሽነቻ እንደሆነው – ያንንም እፍነርን ።

በርግጥ ለግሶታል – ያንም እግር መሄጃ !

መንታ እጆችንም – ቀለም መነገጃ !

አእምሮም አለው – እወቀት መላሻ !

ይህንም ያንንም – ቀላውጦ መቅመሻ ።.............

እንደፍጡር ሁሉ – ሁሉም አካል አለው ፣

"ምሁር" የሚባለው – ምንም አልጎደለው ።

የጎደለው ቢኖር – ከመላ አካሉ ፣

በህግ ከታነፀው – ከባላቱ ሁሉ ፣

ጉብት ከረጢት ነው – እጢአማው አመንጭ ፣

ያን መራራ ሀሞት – ለጋሰና ሰጭ ።

ወትሮማ ነበረ – ባህርይ ማወቂያ ፣

ለኢትዮጵያዊ ሁሉ – ወንድነት መለኪያ ።

ዘመናዊ ትውልድ – በተለይ ምሁሩ ፣

ሀሞት እንደሌለው – ታውቋል በሀገሩ ።

በታች ኮስቶ ይውጣ – አለያም ይተፋ ፣

ምስጢር ሆኖብናል – ያ ሀሞት ሲጠፋ !!

ኬሚካል ስሪቱን – በዝርዝር ብናውቀው ፣

እኛው ሰርተን ነበር – ምሁር የምንገተው !!!..........." (1978 – ፔኪንግ)


አዎን ! አይዋ ፀጋዬ ".....የሃሞቱ እጣቢ እንኳን ቢኖረው !...." የሚለው፣ከግጥሙ ቴማ ጋር ገጥሟል። ምሁር የምንለው "ቅጠል" (የቆላም ይሁን የደጋ) በባህርዩ ፈሪ ነው።የለየ ለት ጅርጅራ ! ደግሞ ሲበዛ ጠርጣራም ነው። አንድ ነፍስ ብትኖረው፣ ህልውናዋን ሃይል እንዲለቀበት ዲናሞ የሚሞላትና የሚያንቀሳቅሳት "ከራብ በላይ ነፋስ"በሚል መርሆ ነው! ከሱ ጥቅማዊ ክልል ውጭ፣ይሞታታል እንጅ፣አይፈናፈንም። መፅሀፍ "ወእለ ከርሶሙ – አምላኮሙ!"የሚለው እንደርሱ ያሉትን ነው።ሌሎችን እየረዳ፣ ራሱም እንዳሻው መኖር ሲችል፣ከሱ ውጭም መስራት የሚያስችለው ችሎታውም፣እድሉም፣ሁኔታውም..በብቃት

ሊያሰሙ፣ በአንፃሩም እንዲያ ቢሰራ ምስጋናና ክብር፣ከፍተኛም እሴት እንደሚያስገኝለት
ሲታወቅ..ያለመታደል ሆኖ፣እራሱ እኔነቱ ኮረጆ ውስጥ ታፍኖ እንደተድፈነፈነ ያልፋል።

ብዙሃን የጥናት ተቋማትና የምርምር ሊቃውንት - "ምሁር ነኝ" ባዩን በየኮሮጆው
ውስጥ ተኮፍሶ የሚገኘውን ተመፃዳቂ ክፍልና በአጠቃላይም "ኤሊት" የተባለውን ራሱን
በህዳጣን "ህሩያንነት"ፈርጆ፣ከብዙሃኑ ህዝብ "በሊቃዊ ልዩነት"በማግለል በገል እሱነቱ
ተውጠርጥሮ የቦደነውን ክፍል፣በብዙ ደካሞች ባህርያቱ አንፃር፣ብጥልጥሉን እያወጡ፣
እንዳልሆነ አድርገው "በትርፍነት" ፈርጅተውታል። ይህ ማለት፣እንደማናቸውም የተፈ
ጥሮ ትሩፋት "ከብዙ ውስጥ – ጥቂት መልካም እንደማይጠፉ" ሁሉ፣ከብዙሃኑም የሀገራ
ችን "ምሁራን" ውስጥ፣መጠነ ብዛታቸው ኩንትሽ ፍንጃል የማይሞሉ "ለሁለተኛ ወገን"
የሚብከነከኑ እንደሚገኙ መገመት አስቸጋሪ አይደለም።አለበለዚያማ ምድረ ተራቢ ሁሉ
በየመንደሩና በየመሸታ ቤቱ እያውደለደለ በፌዝ እንደሚተርበው –"ሁሉ ከሆነ ቃልቻ–
ማን ሊሸከም ነው ስልቻ!" – "ሁሉ ከሆነ አዋቂ – ማን ሊሆን ነው ፋቂ!"የሚለውን አይ
ነት ዘዬ በመፍጠር "አስመሳዩን ምሁር ነኝ ባይ"ሲያስተች ሊኖር ነው።በርግጥም ቁጥራ
ቸው አይብዛ እንጅ፣ እንደ መፍትሄ ሰራይ መደሃኒታዊ ቅመም "ፍቱን ፈዋሽነት" ያላቸ
ው "ሀቀኛ ምሁራን" መኖራቸውን ከቶ መካድ አይቻልም። ስለሆነም ትችታችን፣ከነዚያ
መሰሎቹ "ሃቀኞች ምሁራን ከልል ውጭ" የሚገኙትን ለራሳቸው ብቻ ያደሩትን አስመሳ
ዮች ነው። ከነዚህ ውስጥ ፣ አብዛኞዎቻቸው የከፍተኛ ትምህርት ማጠናነቂያ የምስክር
ወረቀቶቻቸውን ሊሰበስቡ የቻሉት "ሌሎች የፃፉላቸውን ሰነዶች በማቅረብ" እንደሆነና
ገለራሳቸውን "በዋግምትም ሆነ በወሽባ አለያም በወናፍ" ወጥረውና ቀስፈው ቢጨምቋ
ቸው፣ ከዳም ይሉ ገፈት፣ምንም አይነት ጠብታ እንደማይወጣቸው፣በተጨባጭ ማስረጃ
የተረጋገጠ ነው። ታዲያ እንደነዚህ ያሉ ደናቁርት ናቸው ፣ በዲግሪ ብራናዊ ጨምበል
ውስጥ ተሞሽረው "ከኛ የበለጠ አዋቂ – ላሳር!" እያሉ በመፎከር፣አገርና ህዝብን፣ከልማ
ትና ከእውቀታዊ እድገት ሲያኮላሹና ሲያመክኑ የኖሩት። ለገል ፍላጎታቸው ለከት የለሽ
ርከታ ብቻ የተሰለፉም በመሆናቸው፣ለሞራል ፅርየት፣ለኤቲክ ልእልና፣ለክብረዲስፐሊን
ለሌሎቹም የመንፈስ ንፅሃትና ለቀሩትም የምግባረ ሰናያት ቤተሰቦች(ለንትህትና፣ለአፍቅር
ቢፅ፣ለአክብሮ ሰብ፣ለልገስና፣ለትእግስት)የአፅቅ ቅንጣት ታህል ደንታ የላቸውም።ከነዚህ
ይልቅ፣በወሲብ መሰና መንቀዝ፣ለንዋይ አሰሳ መስገብገብ፣ለጥሩ መልበስ፣ለሰባ መቁረጥ

ለአሜሪቃ መፈትፈት፣ለጣሙና ለግፈጠ መጋት፣ለአጌጠ ቤት መንጦልጦል...ለለሕንዓልፍ ቀን ከሌት ቢራወጡ ይጥማቸዋል። ታዲያንን – ያ እስረኛ ፀጋዬ "ምናለበት ነበር፣ለሀገር ልአልናና ለወገናቸው ክብር ሲሉ፣ በከፍተኛ መስዋእትነትና በታላቅ ክብር ሲታገሉ የወደ ቁትን ተራማጅ ምሁራን - የሀምታቸውን እጣቢ እንኳን ቢለግሰው.....!" እያለ ሲከትብልኝ የኖረው፣የዘመኑ ምሁር"እንደሰኮቲሽ ባለወናፍ የሙዚቃ መሳሪያ፣በነፋት ቁጥር የሚጮህ ተግብርአዊ ፍጡር" መሆኑን ዘንግቶት ይሆን፣እንዲያ ማለቱ ? – ከዚያስ ይልቅ እነዚያኑ ጥቂቱን ምሁራን "አያንቅፋቸው!" ብሎ ማሰቡና መመኘቱ የተሻለ ነው።ሀገር 'ምንጭሯ' ወጥቶ በፈጣጣ አይናቹ እያየ፣የዘመናችን ምሁር ነኝ ባይ "በወንፊት ውሃ ይቀዳል!!በመረ ብ አውሎነፋስ ያጠምዳል! በመጥረቢያ ጠጉር ይፈልጣል ! እንደሰሜንና ደቡብ ዋልታዎ ች ያሉትን ፓራሌል ምሰመሮች ያገናኝል!....." እረ ምን የማይሰራው ተአብ አለ ? የቀረው እንደ ጥንቱ ቅምጥልና ቀበጥ ባላባት "ጥቁር ወተት - ነጭ ኑግ - በቅሎ....አስወልዱልኝ" ማለት ብቻ ነው የቀረው።ምነው ቢባል፣የሚኖረው በህልምና በቅዠት አለም ውስጥነውና!

በዚህ አንቀፁ መጨረሻ ላይ – ፀጋዬ "አሜሪካ ጣእቴ" እያለ ወደ ምድረ አሜሪካ ስለሚመንነው ወጣት ትውልድም፣ብልጭ አድርጓል።በበኩላቸው በነሱ ዱር አምባ በኩ ል የሚያልፉትን ወጣቶች "አያንቅፋችሁ!" በማለት እየመረቁ መሸኘታቸውንም ይገልፃል። በርግጥ ሌሎች ቢሆኑ ኖሮ "እንደዚያ ያለውን ትኩስና ሶታ ጎበዝ፣በዚያው በተግሉ ጎራ ላይ ሰንገና አይቀይዱ ቀይዶ ፣ ከጦርነቱ ነበልባለ እሳት ውስጥ ፣ እንደቤተልሄም የገረረ ሙጋድ ይማግዱቸው ነበር እንጅ "ለምለም አያንቅፋችሁ!!" ብሎ በመመረቅ አስተናግዶ ና ሰንቆ በሰላም አያሸጋግሩቸውም ነበር ። በዚህም – የበጎ ምግባር ድርጊታዊ መስተዋት ውስጥ "የነፀጋዬን ክቡር ሰብእናዊ ምንነት" ጉልህና ብሩህ አድርጎ ማሳየት ይቻላል።ፈረ ንጅ ሀገር ውስጥ ከፈላቴዉን በየግለዳው ተቀምጦ እየላሰ – "የእነፀጋዬን ክቡርና ህጋዊ ተጋድሎ" እያጥላላ "እንዲህ ናቸው! - እንዲያ ናቸው!"ለሚል ሁሉ፣የነፀጋዬ ያን መሰሉ ርህራሄያዊ ዝንባሌያቸው፣የውስጣዊ ባህርያቸው ሙሉ ነፀብራቅ መሆኑን በተረዳ ነበር። ከወሲብ ተራ ፍልስፍና ገና ያልተላቀቀ ኮርማ መሪ ከሚመራው ሀገር "መዳኛዬ ነው!!" ብሎ ወደ ምድረ ያንኪ መኮብለል፣የሰብእና የመጨረሻው ክስረትና ንቅዘት ክስተት ነው። ለዚህኛው ኢትዮጵያዊ ትውልድ የሰጠውን መቅሰፍትና መአት ፣ በደፈናው – "አይጣል አያድርስ" ይሏል እንጅ፣ ምን ተአምር መፍጠር ይቻላል ???



"......ሰሞኑን በሬድዮ (VOA) እንደምንሰማው፣በኢትዮጵያ ስላለው ሁኔታ ውይይት መካሄዱ፣ስላማዊ ሰልፉ....ወዘተ. እንደገና የሀገር ፍቅር እንዲቀሰቀስና ሃላፊነቱን እንዲያስታውስ ይረዳል።.........

በያላችሁበትም፥እንጋፉ ታጋዮች፥ኢትዮጵያውያን ስደተኞችም ሆኑ በሌላ መልክ ያሉ ኢትዮጵያውያን፣ለሀገራቸው ማሰብ እንዲጀምሩ የተቻላችሁን እንደምትደክሙ አልጠራጠርም። የኢትዮጵያ ወጣት ያለፈው የደርግ ጭፍጨፋ ከህሊናው ሊፋቅ ስላልቻለ ፤ ልብ ገዝቶ ፥ ነፍስ ነስቶ ወደ ትግሉ አፈፍ ለማለት፣ እየዳዳው ነው።- ቁስሉን የሚያደርቅ ፥ ሰንበሩን የሚያደበዝዝ መድሃኒት በናንተ በኩል ፈልጉለት......እኛ ያለንበት አካባቢ ጊዜ ሰጥቶ ለማስታመም አይመችም።..........................................."

(የቀዳማይ ጦማር – አንቀፅ 8)

ኢትዮጵያዊ ወደፈረንጅ ሀገር ሲሄድ፣አካሄዱ የሚገለፅበት ቋንቋዊ ብሂልና ዘይቤ፣ "ባህር ማዶ ተሻገረ"ነው።የዚህም ብሂል ቀጥተኛ ትርጉም"ውሃ ሳይነካው"ተሻገረ ማለት ነው።እንደሚታወቀው፣ሶስት አራተኛው ክፍለ ምድር፣በውሃ የተሸፈነ መሆኑ የተረጋገጠለት ይህ አለም፣እንኳንስ አህጉራትንና በሃውርታትን ቆርጦ የሄደ ይቅርና፣እዚያው እተወለደበት ሀገር ውስጥ እንኳ በወንዝ፣ በሀይቅ፣በኩሬና በባህር የተከበበ መሆኑ ግልፅ ነው። ከእነዚህ ሁሉ ማህደረ ማያት፣በሆነ አጋጣሚ በአንደኛቸው ውሃ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሳይነካና ሳይረጥብ የቀረ አይደለም።ወደ ፈረንጅ ሀገር ሲሄድ ግን "ባህር ተሻግሮ" (ውሃ ሳይነካው) የሄደ በመሆኑ፣ፈረንጅ ሀገር ያለ ሁሉ "ጥምቀተ ማይ" አላጋጠመውም ማለት ነው።ያም በመሆኑ ይመስለኛል በባህርዩ፣በጠባዩ፣በአለታዊ አካሄኑ፣በየቀን ትግባርቱ የሚታይበት ትግባርቱ፣ ከበስተፊተኛ ሀገሩ ባህላዊ ይዘትና ስርአት፣ ራሱን ሙሉ በመቀየር፣ "ልሙጥና ሌጣ" አድርጎ እንዲዘጋጅ ያበቃው። አዎ! ጥንታውያን የሃገራችን መፃህፍት፣ "ምስጢረ ማያት"ን አስመልክተው ብዙ ፅፈዋል። የህይወት መሰረትና ምንጭ በማድረግ ስለ"ነገረ ማይ"ብዙ ተርከዋል።በማያያዝም"በምድራችን የብስና ባህር፣አየራትና ሰማያት ህዋና ፅንፈ አለማት (ጋላክሲ)ላይ፣ሰፍነው የሚገኙ፣መጠነ ብዛታቸው ይህ ነው የማይባል መናፍስት አሉ። የብዛታቸውን ያህልም አይነታቸውም አይተናነስም። በሆነ ስውር ስልጣ

ናቸው፣አካባቢዎቻቸውን የሚቆጣጠር ሃይል አላቸው። ከዚህ ሰራዊት መናፍስት፣ከሌላ ው ፍጡር ይልቅ፣የሰውን ልጆች ለመፈታተን የተፈጠሩ ናቸውም ይባላል።ሌጌዎኑ፣ጋኔሉ ጋንጨራው፣ጥልምያኮሱ፣አዛዝኤሉ፣ሸበሌው፣ሾተሌው፣ዛሩ፣...........የዚሁ ፈታኝ ሰራዊት አባላት ናቸው። ብዙሃኑም "ረቂቃን መናፍስት" ይሁኑ እንጅ፣ ከፊሎቹም "ልቡሳነ ስጋ" ናቸው።ለምሳሌ እንደቤርሙዳ ሶስትዮሽ ክብ አካባቢ፣መንኮራኩርን እየሳበ ከባህርውስጥ አስገብቶ የሚደፍቀው ግዙፍ ጋኔል "ሾተሌ" ተብሎ እንደሚጠራ የሀገራችን መፅሃፍ ይና ገራል። (የደስታ መዝገበ ቃል ሳይቀር፣ በገፅ 1248 ገፁ ላይ – "ሾተሌ" ን – ጠር የባህር ጋኔን ፣ መርከቦችን እየገለበጠ ሰውን የሚያሰጥም) ሌሎች ትላላቅ ስለስነ ፍጥረት ታሪክ የመዘገቡ፣እንደ "ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ"ያሉ የብራና ጥንታውያን መፃህፍትም፣በዘመና ችን አልፎ አልፎ በየሀገሩ ድንገት ብቅ እያሉ የሚታዩ ልቡሳነ ስጋ አጋንንት (ዩ ኤፍ) የነ ዚሁ ዝርያዎች መሆናቸውን አስቀድመው መዝግበውታል ። ( እኔ በኖብል መፃህፍትነት ጠርዤ ለማውጣት እያዘጋጀሁ ያለሁት፣እንደ "ፃድቁ ጋኔን"እንደ "መድሃኒተ ስጋ" ያሉት ባለፑስቶ ቅፅ መፃህፍቶቼ፤ በነዚህ የመናፍስት ሀተታ አውዳዊ ምህዋር ላይ የሚሽከረከሩ ታሪኮች ናቸውና በርእሱ የተጠቀሰውን እውነታ ለማብራራት መፃህፍቱ ወሳኞች ይሆናሉ)

አስረኛው ወንድሜ ፀገየ ወይን፣በጦማሩ ያነሳውን ታላቅ የጊዜያችን ቁምነገር ለማብራራት ስል –"ፀላዬ ሰናያት ከሆኑት የረቂቃን መናፍስት ታሪክ ውስጥ ተነክርኩ እን ጅ፣በርኩሳኑ መናፍስት አንፃር "ቅዱሳን መናፍስትም" የሚገኙ መሆናቸውን ዘንግቼ አይ ደለም።በመናፍስቱና በርኩሳኑ መናፍስት መካከል ስንጥቅጥቅ የተከሰተው፣ገና ጥንት፣የ አስሩ ነገደ መላእክት ተቀዳሚና ፊታውራሪ የነበረው ሊቃነ መላእክት ሳጥናኤል፣ፈጣሪ ውንና አምላኩን አዶናይን ከዶ፣ኪሩቤላዊ ዙፋኑን ለመገልበጥና፣ስልጣኑንም ለመቀዳጀት በመመኘት "ኩዴታ" ከመታ እለት ጀምሮ ነው።መርሆውን "እነ ውእቱ ፈጣሪሆሙ ለእ ሉ ፍጡራን ! "አድርጎ ሲነሳም "ሰውንና አለሙን ጭምር፣ እንደገል ቀጥቅጦ፣እንደሰም አቅልጦ እንዳሻው እየነዳ ለመኖር እንደነበር፣መፃህፍት ሁሉ ተርከዋል።ዲያብሎስ ድል ተመትቶ፣ገሃነም ይውረድ እንጅ፣ዛሬም ቢሆን ርኩሳን ወገኖቹን በመምራት ስልጣኑ ተኩ ራርቶ ይኖራል።ስለሆነም "የቅዱሳን ጠለላና ከለላ ያልተለያት እናት ሀገር ትሻላለች እን

ጅ" ሞራል ተለይቶት በድኑ ስጋውን የሚኖረው የባህር ማዶማ ሰው፣ይይዘ ይለቀው ሲጠ ፋት በመደናበር ላይ ይገኛል። "መዋቲ ነፍሱን – ለጊዜውም ቢሆን ለማዳን ሲል" ወደ ባህር ማዶ የመረሸው ኢትዮጵያዊ፣ወደደም ጠላም፣የሚኖርበት የፈረንጁ አካባቢ ተፅእ ኖ ሰለባ የመሆን ግዴታ ስላለበት፣ ራሱን ከድሮው ኢትዮጵያዊነቱ እየጠረበ ማስተካከል እንዳለበት ተረድቶ፣አውቆም ሆነ ሳያውቅ ተለውጦ ይገኛል። "ውሃ ሳያጠምቀው ከሀገሩ ተሻግሮ የወጣው የፈረንጅ ሀገር ኗሪ ወገናችን"ርክሰት የገጠመው ይመስለኛል።ስለ ሙላ ደ ሀገሩና ስለ ወላጅ ወገኑ ብዙም ማሰብ አይፈልግም። ፀጋዬ እድል ገጥሞት እኛ ኖረን ከሰለችን ምድር ብቅ ብሎ አይቶልን ቢሆን ኖሮ ፣ የወገኖቻችን "ደንታቢስነት" በንዴት ያስጨሰው ነበር። ሌላው ቀርቶ "ምን እንደሚፈልግ ማወቅ አይቻልም!" ። ከበስተኋላው ጥሏት ስለመጣው እናት ሀገሩ "አረንጓዴም ሆነ ቀይ ህልም" የለውም።ስለሀገሩ የሚያስብ አጠገቡ ቢገኝ "እንደለቀቀ ጅል" ይቆጥረዋል።ሀገሩን እንደቀለጠች ሻማ አስመስሎ የሚ ቆጥራት ይመስለኛል። የማትጠፋ መሆኗን አያምንም። የፈረንጅ ነቢያት – " ከታላላቆቹ የሮማና የኢየሩሳሌም ከተሞች ድምሳሴ በሂላ፣አለማችንም ለጥፋቷ ያስፈራታል!" ብለው በዘመናቸው ቢተነብዩም፣ከከተሞቹ ድምሳሴ በሂላም፣አለም እስከዛሬ ሳትጠፋ አለች።ከ ኖስትራዳመስ ትንቢት ይልቅ በስተኋላ ላይ የተነሱ"መተርጉማን ትንቢት"ትንቢቱን በማ ስተካከል ህይወት ሰጥተውታል። ለምሳሌ ከ "ሶስቱ ፀረ ክርስቶስ ክሰተት በሂላ" (ናፖሊ ዮን፣ሂትለርና፣ገና ያልታወቀው ምስራቃዊ ሃይል) – በ1999 ላይ አለማችን ያስጋታል፣የሚ ሉት ትንቢታቸው ነፍስ ዘርቶ ቢሰራ እንኳ፣ኢትዮጵያ "በዘለአለማዊነት ንግርቷ"ከዚያም ዘመን ባሻገር እንደማትጠፋ – ፈረንጅ ሀገር ረስተዋት ላሉት ንቡዛን ወገኖች ማን በነገራ ቸው ? ፀጋዬ–"እኛ እዚህ ያለነው አላመቸንምና፣እባካችሁ ፈረንጅ ሀገር ላሉ ወገኖች ስለ ሀገራቸው ማሰብ እንዲጀምሩ የተቻላችሁን ሁሉ ሞክሩ!!...."እያለ አበክሮ የሚፅፈው፣በር ግጥ ሰሚ ያለ መስሉት ነው። የከሸፈ ጥይት ሆኖ አንጅ ሳይሞክር ቀርቶ አይደለም።......

( ይህን ሁቲተ አንቀፅ ያቀረበኩበት ስልት ፣ ፀጋዬ በሚያውቀው የስድ ንባብ – "ልብሰ ወርቃዊ ቅኔ"– ቅኝት ነው።)

——ይልቁንም በሕዝቡ ተዋልዶ ላይ ያለው ትልቅ ጋሬጣ
የጠባብ ብሔረተኞች እንቅስቃሴ ነው — እንደሚያውቁት
የሚታገሉት ሰብተቻቸውን ለማጠናከር ሳይሆን ለሥልጣን ሽሚያ
የራሳቸውን ሕዝብ የሚሉትን ደርግ አሁን የኢትዮጵያን ሕዝብ
ከሚገዛበት አገዛዝ ባልተለየ መንገድ ለመግዛት ነው ..—
መቀመጫቸውን ባጠናከሩበት አካባቢ በሙሉ የደርግን
አስተዳደር የማይመርጥ ሰው ማግኘት አይቻልም ..—
ከትግራይ አዋሳኝ ያለው የምዕራብ ክፍል የሁለቱ የወልቃይት
የጠገዴ ሕዝብ ምንም እንኳን በአንዳንድ ታሪካዊ ምክንያት
በጎንደር ክፍለ ሀገር [illegible]
ሕዝብ [illegible]
ሕዝብ [illegible]
ሕዝብ [illegible]

እኔ በነፃ አካባቢ ላይ ነኝ ብዬ ፣ የሆነ ያልሆነውን ትችት ሁሉ መዘርዘሩ አይጠበቅብኝም። ሆኖም አንዳንድ አንኳር አንኳር ነጥቦችን ማንሳሳት ይኖርብኛል።ድሮ ፀጋዬ የተነበያቸው የፃፋቸው – የዚያን ጊዜው "ትንቢቶች" እናም ዛሬ ከዘመናት በሃላ፣"ውሻ" ስልጣን ይዞ የፈፀመቻቸውን ድርጊቶች፣እንደቁምሳጥን ላይ መስተዋት ገፅ በገፅ አቀራርበን እሰቲ እና ስተያያቸው። ለትይታው ገፅ በገፅ ከሚቀርቡልን ስአላዊ ድርጊቶች ውስጥ ጥቂቶቹ፤–

ሀ – "የጠባብ ብሄርነት" ምንነት እንድምታዊ ትርጋሜ (ቅድመ "ውሻ"እና ድህረ "ውሻ") ፣

ሁ – የ"ደርግ ሀ" (አምባገነኑ የመኮንኖች መንግስት) እና የ"ደርግ ሁ"(ውሻ) (ወያኔ ሻቢያ ባንዳ ቡድን) ንፅፅራዊ ትርኢቶች ፣

ሂ – የሁለቱም የቀዳማይ ደረጃና የዳግማይ ደረጃ ጠላት አፈረጃጀት ፣

ሃ – ጎሳን እንደውሻ አጥንት አቅርቦ፣ህዝብን ከህዝብ የማናከስና የማናጩት የኢምፔሪያሊስቶችና ኮሎኒሊያሊስቶች ዘዴ መጠቀም ፣

ሄ – በየዋሂታ "አርት" ስም (ዘፈንና ቲአትር) በመጠቀም የራስን እኩይ አላማና ግብ ፣ በህዝብ ጆሮ ውስጥ መጠቅጠቅ ፣

ህ – "ሁሉ ነገር በኔ ቁጥጥር ስር ይሁን ፣እኔ ብቻ ነኝ ፈላጭ ቆራጭ"........ ጠቅላላውን የሀገሪቱን፣ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ፣ ሀብትና ንብረት (መሬት፣ ኢንዱስትሪ፣ ፋብሪካ፤ ባንክ ፣ኩባንያ......) ዛሬ የማን ነው ?

ሆ – ከላይ የተጠቀሱት ብሄራዊ ደባዎች በመፈፀማቸው፣ዛሬ – ፀጋዬ እንዳለው –"በህዝብና በህዝብ መካከል –(አይፈለጥ አይቆረጥ እንጅ)– ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ጥላቻ አልነገሰም!"በማለት ደፍሮ መናገር የሚችል ከቶ ማነው ? ...........ወዘተ.

እንግዲህ እንደነፀጋዬ ያሉትን ነቢያት ወንድሞች፣ በእመቅ የጉድጋድ እስር ቤት ተቀይደው በታሰሩበት ክፍተት ውስጥ ባለንበት ሁኔታ ላይ ነው፣ እኛም ፈረንጁ ምድር ላይ በማውደልደል የምንገኘው!! ሌሎቹስ ይቅሩና፣ከቶ "እነአውነት፣እነፍትህ፣እነሰብአዊ ይሉኝታ፣እነታሪክ፣እነእውቀት፣እነስነ ህሊና፣ እነስነ ልቦና....የቀሩቱም ሁሉ የንፅሃ ባህርያት አባላት፣ከገባንበት አሳደው ገብተው የማይፋረዱን ይመስላችሃልን ? ምን አባዜ አስችት

ሉን ይሁን ፤ጭጭ ምጭጭ ያሰኘን ? ይህን ጥያቄ ለሚመለከተው ሁሉ ከሰነዘርኩ በሗላ ደብተራው ፀጋዬ በሚያውቀው ቅኔያዊ ቋንቋ፤ ሁለት ከዘመናት በፊት ከዝነኛ ባለቅኔዎች የደረሷቸውን ሁለት ቅኔዎች፤ለዚህ ለመጀመሪያው ክፍል መዝጊያ ይሆነኝ ዘንድ አቀርባለሁ – ትንሽቱና አጭሪቱ ቅኔ "ጉባኤ ቃና" የምትባል ስትሆን፤ረዥሙ ደግሞ "መወድስ" ይባላል።ሁለቱም ቅኔዎች በሚያንፀባርቋቸው ይዘት አንፃር – "እኛን – ለፀጋዬ ወገኖቹ ነን" የምንለውን ሁሉ አንድ በአንድ ይመለከታል ። ይህን ሃሳብ ከመሰዘንዘር ባሻገር የምለው ሌላ ቃል የለኝም ። "ለብልህ አይዘረዝሩም – ለአንበሳም አይመትሩም!" ይባል የለ!!!!!

1ኛ – ጉባኤ ቃና ቅኔ (ባለቅኔው መሪጌታ ስመኝ ይባላሉ።)

ኢትእመኑ ህዝብ – ዘወለድክሙ በተድላ ፤

እስመ ለማርያም ድንግል – ዘወለደቶ ቀተላ። (ላላላ ላላ)

2ኛ – መወድስ ቅኔ (ባለቅኔው ቄስ ገበዝ ካሳ ይባላሉ)

አልቦ ዘመድ ጊዜ ተዋርዶ ፤

ወይከውን ባእደ ጊዜ ተዋርዶ ዘመድ ፤

እመሰ ይትሌአል በንብረተ ስጋ ማእድ ፤

ጥቀ ዘመድ ወጥቀ ነገድ ፤

ባእድ ይዘመድ ፤

እምሃበ አልቦ ነገድ ወእምሃበ አልቦ ትውልድ ።

ሶበሂ ተሰአልዎ ለሃዋርያ አይሁድ ፤

ሃደገ ፈጣሪሁ ወቆመ ምስለ ባእድ ፤

ዘመድሰ የሣንስ ወልደ ነጎድጓድ ፤

እስመ ኢተፈልጠ ምስለ እሙ እስከ መቃብረ ዘይወርድ ። (ሃሃሃ ! ሃሃሃ! ላላላ !)

የሁለቱም ቅኔዎች አጠቃላይ ትርጓሜያዊ መንፈስ – በአማርኛው ቋንቋ –

"......ሲታመሙ ታሞ – ሲሞቱ ካልሞቱ ፤

በምን ይታወቃል – ሰው ወዳጅነቱ.....!!" እንደሚለው ቃለ አዝማሪ አይነት ነው።

***************************ሁለተኛው ክፍል ይቀጥላል**********************************


# የእስረኛው ፀጋዬ ገብረ መድህን

(ደብተራው)



## ያልታሰሩ

## ነፃ ደብዳቤዎች!




ክፍል ሁለት

## (ገሞራው – ሀገረ ስዊድን)

## 1990-1998

*****************************

# ከፍል ሁለት

".....ከታጠቁ አይቀር – ሱሪ !

የጥንቱን ነበር – የተፈሪ ።

ግን አይመችም – ለስራ !

አጣብቆ ይዞ – ከቀኝ ከግራ ።........"

(1958 – ዩኒቨርሲቲ)

ከብዙሃን የፀገየ ወይን ቅኔዎቹ ውስጥ፣ ይህ ዝነኛው ነበር። ዝነኛ ያደረገውም ያን መሳይ ይዘት ያለው ቅኔ፣በዚያ ቀሳፊ ዘመን ላይ ለማቅረብ የነበረው ድፍረት ነው ። "ሞአ አንበሳ ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ሃይለ ስላሴ፣ስዩመ እግዚአብሄር፣ንጉሰ ነገስት፣ወእግ ዚአ አጋእዝት ዘኢትዮጵያ" የሚባሉ ሃያልና ገናና ንጉሰ፣ከመለኮት በተሰጠ ሃይል፣ሀገሩን ና ህዝቡን ፣ እንደሰም አቅልጠው፣ እንደገልም ቀጥቅጠው የሚገዙበት በነበረበት በዚያ ወጣሪ ዘመን ላይ፣ ያን መሳይ "ገናናውን ንጉሰ የሚዘረጥጥና ክፍና ዝቅም አድርጎ የሚዘ ንቅ ሃይለ ቃላት ያዘለ ቅኔ በአደባባይ ማቅረቡ ነው።እንዲያ ያለው አነጋገር፣በዚያ ሰንግ ዘመን ላይ ማቅረብ ማለት፣በገዛ ህይወት ላይ መፍረድ ማለት ነው። ፈሪሃ አዶናይ አድሮ ባቸው በአማላጅ ብርታት የቅርታ የሚያደርጉ ከሆነ – " አርባ ጅራፍ (አኮርባጅ) ጀርባ አስከ.ተላ ያስልጣል" – አለያም ንጉሱ ያመረሩ ከሆነ በተሙኒ ሲባጎ ገበያ መሃል ያስጠለ ጥላል።ግና ወቅቱ የለውጥ ዋዜማ ስለነበር፣ቅኔያዊ አሩምታው በተለየ ሁኔታ በማጉረምረ ም ብቻ እንዲታለፍ፣የዝቋላው አቦ የረዱ ይመስለኛል። የቅኔው ይዘታዊ ትርጉም ሲፈታ አቋራጭ ብሂሉ "ተፈሪ አላፈናፍን አለን!" (ነፃነት፣ፍትህ፣ኢኮኖሚያዊ ርትእ፣የመናገር፣ የመፃፍና ተሰባስቦ የመወያየት መብት – ባጠቃላይም የሰብአዊነት ፀጋ የሆነው ዲሞክራሲ ያ የለም!...) ማለት ነው።እንዲያ ያለውን ነጃሲ ቃል ባደባባይ ተናግሮ – በተአምር ሃይል ካልሆነ በስተቀር – እረ ማነው ለስላሲት ነፍሱ በሰላም ወጥታ የምትገባ ? የማይሞከር ድ ርጊት ነበር – በወቅቱ !!! በዘመኑ ያን መሳይ ሃይለ ቃል ተናግረው ፣ አሳር መከራቸውን የበሉ ብዙሃን እንደነበሩ እናውቃለን !!!

የሚገርመው ግን፣ ፀጋዬ ያን ሁሉ የመከራና የፍዳ ፀሲማን አዝማናት አሳልፎ፣ "ፍትህና ርትእ - ነፃነትና መብት" ተከብረው ይሰፍናሉ በሚባልበት በሰተሟለኛ ዘመን ላይ በባንዳው የወያኔ በረሃማ ጉድጓዳዊ እስር ቤት ውስጥ፣ አሳር አበሳውን እየበላ ለአመታት መኖሩ ነው።በዚህ መጣጥፌ የማዘክረው ፀጋዬን በመሆኑ እንጅማ፣ በየእስር ቤቱና በየወህኒ ቤቱ ጉረኖ ውስጥ፣ታጉረው በመማቀቅ ላይ የሚገኙት ንፁሃን ወገኖቼማ ቁጥር የትየለሌ ነው ?

እንደ ቤተ ክርስቲያን ማደጎ ልጅነታችን፣እኔና ፀጋዬ ከብዙሃን መሰል ካህናት ጋር በቅርብ የምናውቀው የጥንታውያን መፃህፍት "አንድምታ"ሀተታ፣በአንድ አስተምህሮአዊ አንቀፁ ላይ ተከታዩን ታሪክ አሰፍሯል። "........

(አንድምታዊው ትረካ፣በብዙሃን መልካዊ ገፁ ሰለሚገለፀው ጣኦት ከንቱነት ነው)

"........' ወበምክንያተ ሰብእ ከንቱ ቦአ ውስተ አለም ከመዝ '።
በከንቱ ብኑ ምክንያት እንዲህ አድርጎ ወደዚህ አለም ገባ
አንድም - በ ብኑ ምክንያት ከንቱ ጣኦት፣እንደዚህ አድርጎ
ወደዚህ አለም ገባ።.......' አምሳለ ዘገብሩ ሎቱ ቀዲሙ ለዘ
ሞተ ሰብእ ይእዜ ከመ አምላክ አክበርዎ !'.......ለሞተ ለብኑ
ቀድሞ የሰሩለት ምሳሌን ዛሬ እንደ አምላክ አድርገው አከበ
ሩረት 'ለ' የቀረው ነው። አንድም – "ለዘገብሩ ሎቱ አምሳለ
ሎቱ ቀዲሙ"ይላል።ለሞተ ለብኑ አምሳል አድርገው የሰሩት
ጣኦትን ፣ ዛሬ እንደገና አምላክ አድርገው አከበሩት።"ይህስ
እንደምን ነው ?" ቢሉ –(ታሪኩ)– ለሰሎሞን 'ሴሩሀ' የሚባል
ልጅ ነበረው ። በህፃንነቱ ተቀሰፈበት ። ከሃዘን ፅናት የተነሳ፣
እህል አልቀምስም፣ውሃ አልጠጣም አለ ። " ዘመዶቹ ከእህል
ተለይቶ ይሞታል!" ብለው፣እንጨት ጠርበው፣ መልክ አውጥ
ተው ፣ ቀለም ቀብተው "ልጅህ እንጅ ብኑ ተነሳ!"አሉት።"ል
ጄ ብኑ ነህ ?" አለው። "አዎን!" አለው። እሱ ከቤት አግብቶ
አቆመው ። እነዚያም "አምላክ ቢሆን ነው እንጅ ፣ አምላክ
ካልሆን ተናገረን ?" ብለው "አሳየን !" አሉት ። "አይሆንም!"
አላቸው። እነዚያም " እኛ በጠፌብነው እንጨት ሊጋደድብኝ

በሚገኘ የጉድጓድ እስር ቤት ውስጥ ሰንገውና ቀፍድደው በማሰር ለአመታት ያሰቃዩት ፡፡ ይህን "ፀፍፀፈ ምእራፍ" ከጠቀስኩ በሗላ፣አሁን በሁለተኛ ክፍል ወደ መደብኳቸው ደብ ዳቤዎቼ አመራለሁ ፡፡..........

«

መጋቢት ፡ 6 ፤ 1978

ለአይዋ ፡ ኃይሉ ፡ ገ/ወልደንስ ፤

እንደምን ፡ አለህ ፡ ጃል?

እኛ ፡ ይኸውልህ ፡ የገዳም ፡ ሰዎች ፡ ሆነን ፡ ገዳሜ ፡ ገዳሜ ፡ ስንል ፡
እንዳንዴ ፡ በቤተ ፡ እናንተ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ዜና ፡ ሳንከታተለው ፡
እንቀራለን ፤ ሆኖም ........ በየጊዜው ፡ ደግነትህን ፡ ይደፍልሃል
እኛ ፡ በጣም ፡ ደህና ፡ ነን ፤ ማኅሌታችንን ፡ ከመቆም ፡ አላቋረጥንም ፡ ...
ዝማሬ ፡ ብስራት ፡ እየመረገድነው ፡ ነው ... ሊጃፍንት ፡ እንቸገራለን፤
ምድሬቱ ፡ ወቸሎ ፡ አልመከነችም ፤ በየጊዜው ፡ ወልዳም ፡ ወልዳም ፡
መርገቷን ፡ ታራግፋለች ፤ ቢያስዘው ፡ ገዳሟ ፡ ናቸው ...
አንተ ፡ ያለህበት ፡ አካባቢ ፡ ለማኅሌት ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ አመቺ ፡
እንዳልሆነ ፡ እንረዳለን ፤ "ወቸስ ፡ ማለትዱና" እንደሚገባው ፡
በትእግስት ፡ የተቻለውን ፡ ሁሉ ፡ መሥራት ፡ ነው ፡ ——— »

ድሮ በየጨምቢው (የዝክርና የተዝከር ድግስ) ላይ፣መጠነኛ ለብታ ተሰምቶን፣ሞቅ ሲለን የምንዘምራት አንዲት የማህሌተ ገንቦ ወረብ ነበረችን ፡፡ መዘመር ብቻም ሳይሆን፣ በቸብቸቦ አስገብተን እንደነክርባታለን ፡፡ "....ወገዳሙኒ – ገዳሙኒ አንትሙ ! ወገዳሙኒ - ገዳሙኒ አንትሙ ! ኧኸ ! ብርሃኑ ለአለም ! ብርሃኑ ለአለም ! አንትሙ ብርሃኑ ለአለም!" የምትል ነበረች ፡፡ለአርድት ቅፅላዊ መጠሪያ የሆነችውን "አይዋ" ን፣ በደብዳቤው አማካ ይነት ይዞ ብቅ ያለው ፀገየ ወይን - "እኛ ይኸውልህ የገዳም ሰዎች ሆነን - ገዳሜ!ገዳሜ! ስንል !....." በሚል ብሂል፣የበረሃ ኑሮውን እንደተጣወረው ይገልፃል ፡፡ታችና ላይ ደፋ ቀና ሲሉ ውለው፣በሰተማምሻው ላይ እንኳ ሁነኛ ማረፊያ መኝታ የማይገኝበት፣ከቁንጫውና ከሙጃሌው ወራሪ ሃይል ግብ ግብ የሚገጥሙበት፣አሰተማማኝ የሆነ የምሳና የእራት በቂ አሰቤዛ የማይገኝበት ፤ እንደልብ – የእጅና የፊት የእግርና የጠቅላላውም አካል (ማራሻ) መታጠቢያ ውሃ የማይገኝበት፣ሲብሰበትም ጨልፈው የሚጠጡት የፍንጃል ውሃ የሚነጥ ፍበትን በረሃማ ቦታ ነው – ፀጋዬ "ገዳሜ! ገዳሜ!"እያለ የሚያሞካሻትና የሚያሸበለብላት! "ቤቱ ካሉት – መቃብርም ይሞቃል" እንደሚሉት ያለ ብሂል ነው ፡፡ለመስዋእትነት የተሰለ ፈን አንድ ሃይል፣ምንም አይነት መራራ ፈተና፣ከትግሉ ሊያግደውና ሊከትረው እንደማይ ችል፣ቁርጣዊ ውሳኔን የሚያንፀባርቅ ነባላዊ የመንፈስ ሃይልና ነዲድ ውስጣዊ ስሜትን፣

የሚገልፅ ቋንቋዊ ቃና ይመስለኛል – የበረሃን ህይወት ተጣውሮ "የገዳም ሰዎች መሆን!"
አዎን፣ጥማትን፣ረሃብን፣እርዛትን፣ከቆላ ደጋ መንከራተትን..."በእንተ ሰብእ፣በእንተ ነፃነት
በእንተ ፍትህ፣በእንተ ርትእ......." ሲሉ ታግሰና ችለው፣በትግል ጎራ ላይ ተሰልፎ መዋደቅ፣
የቆራጥነት ቀጥተኛ ነፀብራቅ ነው።ለአንድ ሳምንት ብቻ ቢሆን ኖሮ መልካም ነበር።ለወ
ራትም አድሜ ቢሆን ኖሮ ባልሰለቸም ነበር። ለአመትም ጊዜ ቢሆን ባልመረረ ነበር።ልብ
በሉልኝ ወገኖች ! ፀገየ ወይን በለምለም እድሜው መግቢያ ላይ ጀምሮ ነው መላ እድሜ
ውን ሙሉ በበረሃ ለአመታት ያሳለፈው።"መፅንኤውን ይስጠው!"ይላሉ አበው፣እንደዚያ
ያለውን ሰብአዊ ትእግስት ሲያገናዝቡ ነው።የፀጋዬ ቆይታ የትእግስታዊ ባህርይ መገለጫ
ብቻ ሳይሆን፣ እሱ ራሱ በደብዳቤው እንደገለፀው......."እኛ በጣም ደህና ነን።ማህሌታችን
ን ከመቆም አላቋረጥንም!!......." ይላል። ተራውን ማህሌት ሳይሆን፣ቅኔያዊ ብሂሉ ነው።

እንደሚታወቀው፣ ፀገየ ወይን "ደብተራ" የሚል ተቀፅላ ስያሜ አለው።እስ
እንዳች ምክንያት የተቀጠለለት ስያሜ አይደለም። እንደካህን ልጅነቱ፣ከህፃንነቱ ጀምሮ
ግእዘ ህፃን ራእዩን የተለመው፣ተወልዶ ባደገበት በባጀበት፣ከታላቁ የዝቋላ(ዝ ቆላ) ገዳም
ነው። አባቱም ታላቅ ካህን ነበሩ።ከነአቡዬ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገድል እንስቶ፣በገዳሙ
የሚሰጠውን የዜማ፣የቅኔና የሊቃውንት መፃህፍት ሲቀፅል ያደገ ነው።ያንንም መንፈሳዊ
ትምህርቱን (ያሬዳዊ ፀዋትወ ዜማ፣እፁባዊ ቅኔውን፣ህሩያዊ መፃህፍቱን) በማጣቀስ ነው -
"ደብተራው!" የሚል ስያሜ የተቀፀለለት። ከካባቢ ከነበሩት የትግል ቃል ኪዳናዊ ጓደኞ
ቹ እንደሰማሁት ከሆነ፣ የፀጋዬ በነበረበት የትግል አካባቢ መሰማራት፣ እስተዋፅኦ ያደረ
ገው "ለጎራው" ብቻ ሳይሆን ፣ ለየደረሰባቸው የጎጃምና የጎንደር ገዳማትና አድባራትም
ጭምር ነበር። ቀደም ሲል ባካበተው የቤተ ክርስቲያን ትምህርቱ በመጠቀም፣በየታላላቅ
በአላቱ ወቅት ሁሉ፣በየአብያተ ክርስቲያናቱ በመገኘት፣ከፍተኛ የደብተርነት አገልግሎት
በመስጠቱ፣ከበረከታና አድናቆት ብቻ ሳይሆን፣በካህናቱ መወደድን አምርቶ ነበር።

በየአውደ በአላቱና በየክብረ ቅዱሳኑ እለታት በየደብሩ እየተገኘ፣በሚደብለት
የክብር የቅኔ ማህሌት መአርጋዊ ቦታ ላይ፣ ከካህናቱ ጋር በመሰየም ፣ በግራጎኑ ጨንቃዊ
ተዋረዱ ላይ ከላሽኒኮቡን አገልድሞ፣ በቀኝ እጁ መቋሚያውን ይዞ፣ በአቋቋሙ ዝማሜ
ሲውረገረግ ለተመለከተው፣ ፍፁም ያሬድን እንደሚመስል፣ብዙ ሰዎች ፅፈውልኛል፣በተ
ለይም ደግሞ ፣ በቀኝ እጁ ፀናፅሉን ይዞ፣መረግ ዱን ፣ ንኡሱንና፣ ፅፍአቱን እንደቅደም

ተከተሉ እያፈራረቀ ሲያስነካው፣ከካህናተ ሰማይ እንደ አንዱ፣ፀጋና ግርማ ሞገስ የረበበ ት ሆኖ እንደሚታይም ገልፀውልኛል። ገና ከዋዜማው ምሽት ላይ ጀምሮ፣ካህናቱን በማስ ተባበርና አስፈላጊውንም በአላዊ ስርአትና ዝግጅት ሰያደርግ ላየው ሰው፣ፀጋዬን እንደገ ዳሙ "አበ ምኔት" አስያም እንደ ደብሩ "አለቃ"አድርጎ ነው የሚቆጥረው።የሚቃኘውን "ዚቅ" ቃኝቶ፣ የእለቱንም በአላዊ "አንገርጋሪ" መርቶ ፣ የሚወረበውን ለዘብ በተቀዳሚ አዚሞ ነው፣የቅኔ ማህሌቱን በአላዊ ስርአት የሚያከናውነው ብለውኛል። እኔም ብሆን ፣ እንደዚያ ያለውን ቤተ ክርስቲያናዊ አገልግሎት፣እንደነበር "ደብተራነቱ"እንደማያቅተው በጭራሽ አልጠራጠርም።ችሎታውም ሆነ ክሂሉ እንዳለው አውቃለሁና።

ያም ብቻ አልነበረም። ፀጋዬ የተሰማራበት የትግል ቦታ፣ለትምህርተ ቤተ ክርስ ተያን (ለቅኔ - እነዋሸራ፣ ለዜማ - እነቤተ ልሄም፣ ለብሉያትና ሃዲሳት - እነደብረ ታቦር) መገኛ ምንጭ የሆኑ መከናት (ደብሮችና ገዳማት) የሚገኙበት በመሆናቸው ፣ ሊቃውንቱ ዘንድ እየሄደ "ይቀፅል" እንደነበረም አረጋግጫለሁ። "በአንዲት ጠጠር ጥንድ ወፍ !..." ይሏልም፣የኸው ነው። ፀገየ ወይን፣እንዲህ እንደዛሬው፣ በኩታራ ወንጀለኛነት ተፈርጆ፣ ከበረሃ አዘቅት ውስጥ ተጥሎ ይማቅቅ እንጅ፣ታሪካዊቷና ጥንታዊቷ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ካፈራቻቸው፣ጥቂት ንኡዳንና ክቡራን ብርቅዬ ልጆቿ ውስጥ አንዱ ነው፤ ቤተ ክህነት ከለገሰችው፣ ከቅኔ ከዜማና ከመፃህፍቱ ትምህርታዊ ችሎታው ባሻገር፣በሞ ራላዊ ህሊናና በኤቲካዊ ልቦና የታነፀ፣እጅግ ትሁት ሰብእና የተላበሰ፣ትሁት ገርና ርህሩህ ሰው ነው።በዚያው አንፃርም፣እወነትንና ሃቅን ተመርኩዞ፣ እጅግ ደፋርና ጎበዝም ነው።

ይህን ይህን መሰል ባህርያቱንና ከትግሉ ጋር አጎራብቶ በድርብነት የሚሰራውን ትግብርቱን ከገለፅኩ በሂላ፣ከላይ ወደ ሰፈረው "የደብዳቤ" ይዘቱ እመለሳለሁ። "......እኛ ማህሌታችንን ከመቆም አላቋረጥንም። ዝግ ብለን እየመረገድነው ነው ! ለፅፍአቱ አንቾ ኩሉም ! ምድሪቱ መቸም አልመከነችም፣በየጊዜው መልካም መልካም መርጌቶች ታፈ ራለች፤ ሲያለዝቡ ጉድ ናቸው !............"እያለ ፀጋዬ የሚገልፀው፣በቅኔያዊ ብሂል ሲሆን፣ አባባሉ እንደደብተራነቱ ከላይ የጠቀስኩትን የቅኔ ማህሌት ያሬዳዊ ስርአት ሳይሆን፣እን ደጎራ ታጋይነቱ፣በሰራዊተ ደርግ ላይ የሚያወርደውን ነጎድጓዳዊ "ቅጣት" ነው።"እንመ ረግዋለን" ሲል ደመቅ ባለ ድምፅ፤ሰፊውን የከበሮ ገፃዊ ክፍል በተራዘመ ቆይታ እየመቱ፣

በሚዜመው አይነት ፣ የደርግን ሰራዊት "እንደመረገዱት" (በሰፊ መዳፍ እንደከደኑበት) ሲገልፅ ነው። (የተከሎ ማዳን ወታደራዊ የማጥቂያ ስልት ሳይሆን ይቀራል?) "ፅፍአት"- የሚባለው፣ከህማማት ቀኖት አንዱ ሲሆን "በጥፊ ማጩል"ን ያመላክታል።ስሪቱ ተፋጣ ኝነት አለው።ከበር "ፅፍአት" በሚመታበት ጊዜ፣ምቱ ፈጣን ነው። ያንን አስመልክቶም ፀጋዬ "ለፅፍአቱ አንቸኩልም" ይላል። ከሆነማ "አድግን" ቀስ ብሎ መዝለጥ እንጅ! በየ ጊዜው የሚነሱትም "መርጌቶች"ደንደሮውንና ሸካራውን ደርግ "ሲያለዝቡ" ስሉጥ መሆ ናቸውን መናገሩም "በሰምና ወርቅ ቅኔያዊ ስልት" የማህሌቱን ስርአት፣ከጎራው ተግባሩ ጋር እያነፃፀረ በሰምረት ሲያቀርበው ነው።ታዲያንን ዛሬ፣ሌላ ደነዝ(ሞርን) ሃይል ተነሳና ያንን የመሰለ ሊቅ፣ከዚያ አይነት እውቀቱ ጋር በረሃ ውስጥ ባለ እስር ቤት ጠፍሮታል። የሚገርመው፣ደርግን በትግሉ ያንበረከከ፣እሱ መሆኑ ሲታወቅ፣በዋዜማ ላይ የመጡ "የድል አጥቢያ አርበኞች" የድሉ ተጠቃሚ በመሆን፣ፈራጅ አሳዋጅ፣ቀራጭ ፈላጭ መሆና ቸው ነው። እርስዎስ ይህን ትንግርት ምን ይሉታል ?

« ... ለመሆኑ ከ[illegible] ጋር ግንኙነት ተ[illegible]?
[illegible]
... [illegible] ነበር ...
[illegible]
[illegible]
[illegible] ... »

"...እርከክ ወእርከ አቡከ ኢትህድግ" (የግል ወዳጅህን ቀርቶ፣የአባት ወዳጅ አትተው)ይላል ጥንታዊው ሰሎሞናዊ ምእዳን።ለየትውልዱ ምክርና ተግሳፅ መሆኑ ነው። ይህም ብሂል፣አበው -"የአባት ወዳጅ - የደንጊያ ገድጋጅ"- እንደሚሉት ያለ ነው። እናት ቤተ ክርስቲያን ኮትኩታና መልምላ ያሳደገችው፣እንደ ፀገየ ወይን ያለ ምሁር፣የትም ይኑ ር የትም፣ምንም አይነት ፈተና ይግጠመው-"አፍቅር ቢፀከ ከመ ነፍስከ" (ጓደኛህን እንደ ነፍስህ ውደድ) የሚለውን መሰረተ ትምህርት መርሳት አይችልም።አንድን ሰው ማፍቀር የቻለ፣ያከብረዋልም ያሰብለታልም ማለት ነው።

በላይኛው የፀጋዬ አንቀፀ ጦማር የምናነበው፣ይህን መንፈስ ነው።ለሁለታችንም የቅርብ ወንድም የሆነ፣በጥበብና በእውቀት አምላኩ ለይቶ የሰራው፣በአዲስ አበባ ይኖር ነበር። ስለዚህ ወንድማችን፣ እኔም ቀደም ባለ ዜና የሰማሁት፣የመልእክ ሞቱ ደርግ ፅዋ

ደርሶት የማለፉን መርዶ ነበር። እጅግ አዝኜ ፀፀቴን ካወጣሁ ቆይቼ ነበር። ፀጋዬም የሚ ለው፣የወንድማችንን መርዶውን ሰምቼ "ሀገረ ህይወትን ያዋርስልኝ ብዬ ደምድሜ ነበር" ነው። "አሁን ግን የሰይጣን ጆሮው ይደፈን ብያለሁ!!" ይላል፣በህይወት መኖሩን በሰተሟላ ላይ አረጋገጦ። እኔ ይህን ነጥብ እዚህ ላይ የማነሳው፣ የፀጋዬን "ስለወንድም መቆጨትና መጨነቅ" አስመልክቼ፣ለሌላው ሰው ያለውን "አሳቤ፣ርህራሄ፣አፍቅሮ ቢፅ፣ልዩ ፍቅራዊ ስሜትና ሰውን የማክበር ዝንባሌውን....."ለማሳየት ነው። አስታውሱ፣ ያለበት የትግል ፍት ጊያ ጎራ፣ሩቅ ሳለ ወዳጁ አስታውሶ ማሰብ ቀርቶ ፣ እዚያው ባለበት አሰቸጋሪ ሰፍራ ላይ እንዳለ፣የደቂቃዎች ፍንካች ነፃ ጊዜ አግኝቶ፣ እለታዊ ጉርሱን እንኳ፣በሰርአት መመገብ የሚችልበት የተረጋጋ ሁኔታ አያገኝም። እሱ ግን ከዚያ ሁሉ ውጥረትና የትግብርት አጣ ብቂኝ ውሰጥ ወጥቶ ፣ በመናሃሪያቱ ከተማ ውስጥ ላሉ ወንድሞቹ ሁሉ የሚያስብ ሃቀኛ ወንድም ነው።እንደዚያ ያሉ የመከራ ቅፅበቶች ውስጥ እያለ፣ ያ አልበቃ ብሎት፣ ከዚያ ፀሊም ኩነት ውስጥ ተሻግሮ፣ስለተቸገሩ ወገኖቹ የሚያስብና ስለአድላቸውም የሚጨነቅ ሰው መሆኑ"ፀጋዬ በባህርዩ ክቡርና አርቆ አሳቢ ሰው"እንደሆነ፣አማናዊና ፍፅምታዊ ማስ ረጃ ነው። አዎን ! እንግዲህ የዛሬዎቹ "ብሩሃን መሪዎቻችሁ ነን !" እያሉ የሚያቅራሩቱ ባንዳ ወንበዴዎች፣እነፀጋዬንንና እሱን የመሳሰሉ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንዝበየጉሮኖው አስረው ነው—"በሂደት እንፈተዋለን!!!" እያሉ ምናምንቴያቸውን የሚያቀረሹብን !!! ከዚህ የበለጠ ግፍና በደል፣ፍዳና ደይን፣ደባና መከራ ይኖርን ?

የዚህ ትውልድ አንጋፋ የሆን ወገኖች —"ኢትዮጵያ ! ህዝቧ ! ነፃነት ! ፍትህ! ርትእ ! ባጠቃላይም ክብረ ህዝብ (ብዙሃን - ዲሞክራሲ)........" እያልን ዘመናችንን ሙሉ እሪ ስንል የኖርነውና፣ግማሾቻችን በእስራት፣ጥቂቶቻችን በስደት፣የቀረነው ደግሞ በተለ ያየ የፈተንና የችግር ውጥረቶች ተሰንገን የማቀቅነው፣ዋናውና መሰረታዊ አላማችን፣ ሀገ ራችንና ወገናችንን "ለመታደግ" ባደረግነው ትግልና ተጋድሎአዊ ገድል ነው። ይህንንም ትግል ከማያወላውል ብሄራዊ ግቡ ለማብቃት የተጠቀምንበት ቀዳማዊ ስልት "ብእራዊ" እንደነበር የሚያውቅ ሁሉ ያውቀዋል። ትግላችን ህጋዊና በሰርአተ አመክንዮም የተደገፈ ነው። መነሻና መድረሻው፣አልፋና አሜጋው ማራኪና አማናዊ ምክንያት አለው (ጀስቲፋ ይድ ኮዝ)። እኔ በዚህ አጭር ፅሁፌ ላይ አካትቼ ማስቀመጥ እችላለሁ።

".....ጥንት ቅድመ ታሪክ፣ አለም እንደተፈጠረ – ገና ሰማይና ምድሩ ተሳስመው
ይኖሩበት ከነበረው ክፍተት ውስጥ፣እምሃበ አልቦ ከች ብለው ደርሰው ሲገዝፉ፣ ለሰው
ልጅ መቅድመ ፍጥረት የሆነው ቀዳማዊ ፍጡር የተገኘው ፣ በምድረ ኢትዮጵያ ነው።
ሰብአዊ ፍጡር ብቻም ሳይሆን፣በህይወት ለማስኖር መደገፊያ የሆኑ የተፈጥሮ ትሩፋቶች
ም(ምግብ፣ልብስ፣መጠለያ)በዚያው ወቅት በአንድነት የተገኙት፣በሀገረ ኢትዮጵያ ውስጥ
ነው(የገብሱንና የስንዴውን፣የጥጡንና የፀጉሩን፤የዋንዛውንና የቀሩትንም ሺ እፀዋት፣ በም
ድረ ኢትዮጵያ በቅድመ ታሪክ መገኘት፣ ዝርዝር ሀተታውን ለስነ ጥናትና ለስነ ምርምር
ሊቃውንት እተወዋለሁ) ያ ሁሉ በእንደዚያ መልኩ ተቀነጃጅቶ ከተጀነጀነና ከተገደገደ
በሂላ፣ከድህረ ታሪክ ልዩ ልዩ ምእራፉዊ እርከኖች ተዋረድ ላይ፣በየዘመኑ የድንጋይ፣የብ
ረት፤የብራና የወረቀት...እየተባለ በሚጠቀሰው የስላማኔ ዘርፎች ላይ፣አድገታዊ ለውጦችን
በማፈራረቅ፣ለኛ ለኢትዮጵያውን ብቻ ሳይሆን፣ለመላው አለም ጭምር፣የኢትዮጵያው ያን
ፀጋና በረከት መፈንጠቅ ብቻ ሳይሆን"ቾምቧ"ተደርጎ እንደተረጨ፣የትላንቱም፣የዛሬውም
ታሪክ በማስረጃ መዝግቧል። ይህ እውነታዊ ታሪክ የነገም ሃቅ ይሆናል። እንግዲህ እንደ
ፀጋዬና እንደኔ ያለው የቀለም ሰራዊት ያደረገው ትግል ቢኖር፣ ይህን ታሪካዊ ሃቅ ለማስ
ከበር ብቻ ነው ። እሪ ብለን የጮህነውም – "የሃገራችኽ ሁለንተና ቅድምና (በኩረ ኩሉ
ኩነታት) አትንኩብን!!" በማለት ነው።ይህ ቅድምናዋ፣የታሪክ፣የስልጣኔ፣የጥበባት፣የባህል
የፊደል፣የመፃህፍት.....ብቻ ሳይሆን፣የሰዉን፣ የእንስሳቱን፣የእፀዋቱን፣የፍሬያቱን(ቡና)፣የአ
ዝርእቱን (ጤፍ ስንዴ) የማእድናቱን......የመሳሰሉትን ሁሉ ያጠቃልላል። ዛሬ፣ትላንት የተ
ፈጠሩ እንደነብራዚልና ኮሎምቢያ ያሉ የሩቅ ታናናሽ ሀገሮች ሳይቀሩ "ቡና የኛ የተፈጥ
ሮ ምርት ነው!"እያሉ፣በአለም ማቅራራት ይዘዋል።ኢትዮጵያ ገና በስተፊተኛ የለመለመና
ያበበ ስልጣኔዋ ወቅት"ከወርቅ፣ከአልማዝና ከከርከዴን በተሰራ የመታጠቢያ ገንዳ"ስትጠ
ቀም በነበረችበት ጊዜ፣ ገና ህልውናቸው ያልተከሰቱ የአውሮፓና የአሜሪካ ሀገሮች፣ትላ
ንትና ተነስተው "የምድሪቱ አንጋፋ አባቶችና መስራቶች ነን!!" ብለው ሲፎልሉና ሲያቅ
ራሩ፣"ለዚያ ክብር ምናችሁ አድርሷችሁ ?.....እታጭበርብሩ!!" እያልን በመጮሃችን ነው
የኸውና ዛሬ በያለንበት፣አሳር ፍዳችንን እያሳዩን ያሉት !!! መከራ እንብላ እንጅ፣የኢትዮ
ጵያን የታሪክና የስላማኔ ብኩርናና ቅድምና፣የፈለጉትን አድርገው ቢንጨረጨሩም፣ ከቶ

መጋራት አይችሉም። ይልቁንስ – የአበጠ የቅኝ ግዛት ህልማቸውን አሟሽሸው "ሰቀቅ!" ያድርጉንና በተሻድሶ ህይወት ራሳችን በራሳችን ብቻ እየተዳደርን እንዳንኖር አይረብሹን!!

«...በተረፈ፡ በግራና፡ በቀኛችን፡ መታጠር፡ ነው፡ የለውም፤
ግንድ፡ ብሎአል፡ የሱዳን፡ ፓሊቲካ፡ ቅጥ፡ እምባሩ፡ መፍታል፤ በሱን፡ በጦስ፡
ዴርግ፡ ይገም፡ ሕዴሪኦን፡ (አጋዴን፡ [illegible]፡ ከፋሌን፡
ጉራጌዎች) እንመሠርታለን፡ እያለ፡ ሰራት፡ ያናፋል፤... እኛ፡ ግን፡
ሁሉ ቱንም፡ እየታዘብን፡ ከሕዝባችን፡ ጋር፡ ስራጅው፡ እየተነፈስን፡
ራጅም፡ ጉዛችንን፡ እንቀጠልን፡ ነው።...
ፈገግ፡ የምትፈልገው፡ እለሁ፡ ስማለት፡ ነው።... እሱ፡
ሲያጠቃው፡ ማፍለን።...
ቸር፡ ይገጠመን፤
ያንተው፤
[illegible]
[illegible] »

ይኸ ጦማራዊ ደብዳቤ ከተከተበ፣በዛሬው ቀን መንታ ሰባኤ አመታት ሞልቶታል። በዚያ ዘመንና(1976) በዛሬው ዘመን(1991) መካከል ያለፈው የዘመን ማእበል ብዙሃን እን ግዳ ነገሮችን፣በየወቅቱ እንደደለል እያስቀመጠ ያከማቸው አንቶ ፈንቶ፣ አቲሆ ባቲሆና አርሲ ኩርሲ (ጥርህርህ) ፣ ብዛቱ ይኸን ያህላል ተብሎ ለመገመት ያስቸግራል። በዚያ ዘመንና በዚህ ዘመን መካከል የተከሰተው ዝግንትል፣ ሁልቆ መሳፍርት የለውም ። ከኛ ውጭ የሚገኙ ጎረቤት ሀገሮች፣እነሱዳን ተተረማምሰዋል። እነሱማሌያ እንደወትሮአቸው "በይነ መንግስታዊ"ቋንቋ ፈጥረው መናገር ከማይችሉበት ገዋ ክፍተት ውስጥ ተነክረዋል። የነሩዋንዳ ብሩንዲን ህዝባዊ እልቂትም ያጤኗል!እዚያው ብሄራዊ ቤታችን ውስጥ፣ጃንዴ በማንገቡ ብቻ፣የሀገሩና የህዝቡ"ፈጣሪ ነኝ"የሚል የወታደሮች ቡድን ተነስቶ፣የምድሩን ጨርሶ ሰማዩን ልቧጥ ብሎ እስኪመረቅን ድረስ፣በህዝብ ነፍስ ላይ ነቀዘ፣ሸና፣ኮሰ።የሚገርመው ደግሞ ሌሎች ሲያወሩ ሰምቶ "ሪፐብሊክ" ሆኛለሁ አለ።እንዲህ ያለውን መዶር ዬት፣ፀጋዬ በላይኛው ደብዳቤው እንደተናገረው "እናፋበት" አለ። እንደ "ዉሼዎቹ ዋር ዴዎች" ማለቱ ነው። በዛሬው ዘመን ላይ "ከልቢ" ናት እያሉ የሚያብጠለጥሏት ሱዳን፣ ለወትሮው "ወያኔ ሻቢያን"በዚታዎ ጭና አዲስ አበባ ያስገባች ወዳጃቸው ነበረች። የዛሬ ውን አያድርገውና - ራሷ "ሻቢያ"መንትያ ወንድሟ "ወያኔን"እንኮኮ ብላ፣በደደቢት በኩ ል አቆራርጣ፣ ከፈረደባት አዲስ አበባ ላይ አምጥታ ያራገፈቻት ነበረች። አያልፍ አይለ ወጥ የለምና፣በዚያና በአሁኑ ጊዜ መካከል፣ያ ሁሉ ሆኖ፣ዛሬ አዲስ ዚቅ እየተቃኘ ነው።

ልክ ፀጋዬ እንደሚለው "...እኛ ግን ሁሉንም እየታዘብን፣ከህዝባችን ጋር በረጅሙ እየተነፈስን፣ረጅም ጉዞአችንን እንደቀጠልን ነው!!!"...ይህ ሀቃዊ አባባሉ ፣ሰሃ እንደማይወጣለት ጤነኛ የሆነ ህሊና ሁሉ ይረዳዋል ብዬ አምናለሁ።


የሚገርመው፣ እኛ በሩቅ ተቀመወጠን እየታዘብን ባለንበት ወቅት፣ ከጣምራ መንትዮች አንዱ፣ በተሳሳተ ዝየራና ቅመራ (ሚስካልኩሌሽን)..."ለ-አልፋዊው 'ሀ' አልሞ የሰነዘረ፣ቢቀር ቢቀር (ቢያንስ ቢያንስ) ወኦዋዊውን 'ሆ' አይስትም በሚል መላ ምት ያቀረበው "የሸራ–ሮ-ባድመ-ዛላ አንበሳ" የካርታ ይሉ የገበጣ ጨዋታ፣በፈጠረው ጠንቅ፤አሃቲና ዋህድ የነበረች ትግርኛ ቋንቋ ሳትቀር ፣ ባልነበረባት አዳና ባህርይ፣ለሁለት ተፈልጣ በመንታነት ልትሰነጠቅ በቃች።ወዲ አፈወርቂ አሰበው የነበሩት 'የፎረሸው ሪፈራንደም' በሀገራቸው አርቲፊሺያል ህልውና ጉዳይ ላይ ጤና እየነሳቸው ስለተቸገሩ –"እንሼራሮንና ባድመን" ወርረን እንደመያዣነት በመጠቀም፣ትልቁን ባህራዊ ድንበራችንን እናስከብር!"... የሚል ሲሆን – ባልጠበቁት ሰላጭ፣ከመንታ ወንድማቸው ጋር ሳይቀር ለመፋለጥ በቁ ። በኢትዮጵያውያን ብሄራዊ አሳቤ አንፃር -"ሸራሮ አለያም ባድመ ወይም ዛላ አንበሳ"ብሎ የሀገራዊ ድንበር ችግርም ሆነ ውጥረት አለያም ጥያቄ የለም። ጥንትም ሆነ ዛሬ አለምአቀፍ እውቅና ያለው ድንበራችን፣ባህረ ኢትዮጵያ (ቀይ ባህር) እና ሱዳን፣ኬኒያ፣ ሶማሊያና ጂቡቲ ዙሪያ ገብ ምድራችን ነው። ፀገየ ወይን በጦማሩ እንደከተበው፣ይህን ህዝባዊና ሀገራዊ እምነታችንን እንደያዝን.."እኛ ሁሉንም እየታዘብን፣ከህዝባችን ጋር በረጅሙ እየተነፍስን ረጅም ጉዞአችንን እንደቀጠልን ነው.....ይህን እምፅፈው 'አለሁ' ለማለት ነው።".. በርግጥ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ገርና ርህሩህ፣ ቅንና ለሀገሩ እንሰፍሰፍ – ሲለውም የለየለት ጀግና ህዝብ ስለሆነ፣ እንደ ፀጋዬ ያለውን ታጋይና አሳቢ ልጁን፣ምን ጊዜም ሊያጣ አይፈልግማና -አንተው "ይህን የምፅፍልህ 'አለሁ' ለማለት ነውና !"እንዳልከው፣እስቲ እባክህን በአዶናይ ስትል (ቢቻል ከእስርህ ተፈተህ) ኑርለት!!!

********************ሶስተኛውና የመጨረሻው ክፍል ይቀጥላል************************
****************************************************************************

# የእስረኛው ፀጋዬ ገብረ መድህን

## (ደብተራው)

# ያልታሰሩ ነፃ ደብዳቤዎች!



## ሶስተኛውና የመጨረሻው
## ማሳረጊያ ክፍል።

## (ገሞራው – ሀገረ ስዊድን)

# 1990-1998

# ክፍል ሶስት

## (የመሰናበቻ ማሳረጊያ)

".........አጃምባ የምትባለዋ ደማቅ ከተማ፣በስተምእራባዊው የስቶክሆልም ከተማ ጫፍ ላይ የምትገኝ የምታዋዋ ከተማ ናት። ብዙ አይነት ቅርፅና መጠን ያላቸው ህንፃዎችን በደረቷ ላይ አቅፋ ስትታይ፣ አቅፋቸው የሞላ ቤት ወይዘሮ እናት ትመስላለች።የታላቁን የስቶክሆልም ከተማ ያህል የህዝብ ብዛትና አፈና አይታይባትም።ከከተማይቱ እምብርት ላይ እንደ ቻይና ደራሮን አፍጠው የሚያዩ የሚመስሉ ህንፃ ፎቆች፣ጉብታው ላይ በመተከላቸው፣ከየትኛውም አቅጣጫ ሆኖ ወጭ ወራጁ ሁሉ ሊያቸው ይችላል። ከበሰተኔ መኖሪያ በኩል ያሉቱ ባለ አሰር ፎቆች የሆኑቱ አምሰት ህንፃዎች፣ቀረብ ብሎ ሳያቸው ፣ ድር ለሰልፍ የሚወጣውን፣ ጠምበለል መሳዩን የክብር ዘበኛ ሰራዊት አይቶ ማየት ነው። የኔ መ ነሻሪያ የሆነችው አነስተኛ ባለሶስት ሸጌ ህንፃ፣ከነዚህ ረጃጅም ህንፃዎች ግርጌ ስርቻ ውስጥ"አለሁ! አለሁ! እዩኝ! እዩኝ!"ትላለች።ሁሉ ነገር እንዳቅምኪ አይደል!

ታዲያንን – አለሙን ስዟዟር ቆይቼ፣ በስተመጨረሻ ላይ መኖሪያ ድንኳኔን ተክዬ የምኖርባት፣ብርቅዬ መከኔ ናት።በቅድማዊ የወትሮ ስሪቷ፣ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ገበሬዎች፣ የእጃ እህል የሚያመርቱባት ለስላሴ ምድር ነበረች። መጠሪያ ስያሜዋን ያገኘችውም ከዚሁ አገልግሎቷ የተነሳ ነበር።ከተማይቱን ሁለት ይሉ ሲሶ ላይ ሰንጥቀው በየጊዜው እየመጡ የሚጎበኙኝ ብዙሃን ወገኖች አሉኝ።

ታዲያያንን – አንድ ቀን ይህን የፀጋዬን ገደል ስጫጭር፣ ከነዚሁ ወዳጆቼ ውስጥ ከዚችው መናኸሪያ ከተፍ አሉ።እህል ውሃ አቅርበን ስንጨዋወት፣ ከመካከላችን አንዱ፣"እስቲ ያንን 'ክፍት አሸንዳ' (ኦፐን ካናል) ክፈትልን' አለኝ።እኔ ብዙ ተሳላችተን ቲቪውን መክፈት ካቆምኩ ቆይቷል፣ ለእንግዶቹ ፍላጎት ስል ለመጀመሪያ ጊዜ እንደገና በዚያን ቀን ከፈትኩ። ቴሌቪዥኑን ለካስ የ'ውሻ' ባንዳ ወኪሎች፣በስቶክሆልም የተከሉት ኖሯል።ከአማርኛ ቋንቋ ጋር፣የከረረ ግብግባዊ ትግል የገጠመው የሚመስል አንድ ሰው ሲንተባተብ ጀመረ። "ሁላችንም – ምናለበት በሚያውቀውና በሚያመቸው በራሱ ቋንቋ በለፋደደ?"

አልንና፣ማየት መስማቱን ቀጠልን።

በዚያን እለት ከአጃምባው አድባሬ የተሰባሰቡ ወንድሞችና እህቶች፣ ከወትሮው ይልቅ እጅግ ሆድ የባሳቸው ሆነው ነበር። የሚናገሩት ሁሉ በቀቢፀ ተስፋ የተለወሰ ሃይለ ቃል ነበር። የሰውን ገፅታዊ አካል እጅግ እያብጠለጠሉ ደጋግመው ከመናገራቸው የተነሳ ቢቸገረኝ "እባካችሁ ከሰውየው ገፃዊ ትችት ይልቅ፣የሚተፋውን የተሸዋረረ አመለካከቱ ንና የተሸመደመደ አስተያየቱን በተገባዕ በትር መጠለዝ የተሻለ ነው!!" በማለት አስተያ የቴን ባቀርብላቸውም "አሻፈረን !" ብለው -"ሸውራራ አመለካከትና ሽምድምድ አስተሳ ሰብ መሰረፅ የሚችለው ከተናጋሪው ስሪታዊ አካልና ተፈጥሮአዊ ቅርፅ ነው ! ማነው ከተ ክለ ሎሚ፣ጣፋጩን የብርቱካን ፍሬ ማምረት የሚችል ? "እያሉ፣ጭቃ ጅራፋቸውን ያወ ርዱበት ገቡ። ከቀደምቱ ኢትዮጵያውያን ነገስታት አፄ ናኦድም ይበሉ አፄ ሚናስ አለያ ም ንጉስ አይዙር – በአካላዊ ቅርፃቸው "ጉጭማ ነት" ይበሉ "መፃጉእነት"አለባቸው ይባ ል ነበር።እንደዚያም ስንኩለ አካልም እንኳ ሆነው የነበራቸው ግርማ ሞገስ "እጅግ መፍ ርሀ መደንገፅነት" ነበረው ይባላል። ይኸ ያሁኑ "በገዛ ፈቃዱ መሪ ነኝ" ያለ ሰው፣ሁለቱ ንም ሲያጣና ይሉኝታና ሃፍረት ያልጣፈበት መገለጢጥ ሆኖ ባደባባይ ሲቀልድ ፣ እንዴት ዝም ብሎ ማየት ይቻላል ? መፅሃፉም የሚለው ፣

".........ኢታሀትት ሎቱ ርእሰከ ወኢታርምም ሎቱ አፋከ፣ ለብእሲ አብድ ወመስተአብድ ፣ አላ ገስፆ ወአመድሉ ገፆ እስመ ነሳኤ ገፅ ወአምኦ........."

(በመንፈስም በአካልም ድውይና"መፃጉእ"የሆነ"ጉጭማ"፣ራሱ አብዶ ሌሎችን በእብደቱ እስኪያሳብድ፣ግስፀው፣ተቸው እንጅ ዝም ብለህ አትለፈው ሲል ነው!) እነዚያ እንግዶቹ፣ስንት ሀገር ቀርጦ መጥቶ፣ርቆው ከሉበት ስፍራ፣ ከፊታቸው ገጭ ብሎ ፣ የሆነ ያልሆነ እንቶ ፈንቶ ነገር እየቀባጠረ ሲለፋደድባቸው ተመልክተው፣እንደዚያ ቢተቹ አይፈረድባቸውም።

እንደ ምድር ያረጀው ጥንታዊው ብሄራዊም ሆነ እለም አቀፋዊ ባህል መሰረት፣በየትም ሀገር በመሪነት ስልጣን ላይ ተቀምጠው በተረ መንግስት ሊይዙ የሚገባቸው ግለ ሰቦች ሁሉ፣ቢ ያንስ ቢያንስ ከተራው ሰው፣በመልካዊ ገፅታውና አቋሙ "የሚያስደነግጥ ግርማ ሞገስ"ያላቸው መሆን እንዳለባቸው ይታመናል።እንደዚህ ያለውን ጥንታዊ እውነታ በማመሳከር ይመስላል እነ ዚያ እንግዶቹ፣በሰውየው ላይ የወረዱበት።

"....መተቸት ነፍስ አካሉን (ሃሳባዊ አመለካከቱን) እንጅ፣ ገላዊ ሰውነቱን (ገፃዊ አካሉን)

አይደለም !"እንዴት ትሰናለህ ? የተሸመደመደ ሃሳብ የሚፈልቀውና የተንሸዋረረ አመለካከትም የሚሰርፀው፣ሙሉነት ከሴለው ጎደሎ ሰው (ጉጭማ ድውይ መፃጉእ) ስለሆነ፣ለምን "አህያውን ትታችሁ - ዳውላውን ተቹ!!" ትሰናለህ ብለው፣ "ምንጩን ትቶ አላሉን !" እንዲሉ የመነሻና የመድረሻ ( Cause & Effect ) ውጤቱን ሳያገናዝቡ መተቸት "እንዴት ትክክል ነው? ትሰ ናለህ ? እበት አይደለም ወይ ትል የሚወልደው ?"......በማለት ጨሁብኝ ።

ከላይ እንደጠቀስኩት፣ በዚያ ቀን ማምሻ ላይ ፣ ያንን ተንኮለኛና መርዘኛ ፊልም ስንከታተል በነበረበት ወቅት፣ እንግዶቼ ባዩት አሰተዛዛቢ ትርኢት፣ የተሰማቸውን ውስጣ ዊ ስሜት በገለፁልኝ ጊዜ ያቀረብኩላቸው አስተያየት ነበር። አልወደዱልኝም። በድምር የተውኩትን የምሽቱን ሁኔታ ፣ እስቲ ትንሽ ላክልበት ።

የፊተኛው ሰውዬ እንደጨረሰ፣ ቀጠለና አንድ በምኑ ም በምኑም፣የቤተ ሰሊሆምን "ጉጭማ" የሚመስል" መፃጉእ ቢጤ"፣ከበስተፊቱ ከተደረደሩለ ት ድምፅ ተቀባይ ማጉሊያዎች እየተንጠራራ፣ እሱም እንዲሁ፣ በአማርኛ እየተንተባተበ ና እየተንተባተበ፣አይኖቹ ተጎልጉለው ከየኮሮጆቻቸው እስኪወጡ ድረስ እየጮኸ ማቅራራ ት ጀመረ። ሁላችንም "ወቸው ጉድ!!??" አልን ።

ለካስ ዲስኩሩን ለሃጩ እስኪዝረበረብ ድረስ ሲረጨው አምሽቶ፣እኛ የደረንስበ ት፣የመጨረሻው ክፍል ላይ ኖሯል ።ሰውየውን ገፃዊ ስሌዳውን አተኩሮ ላየው ሁሉ፣ፍፁ ም እፁ የጠፋበት የቀትር ጋኔን (ጋንጩራ)" ይመስላል። ወጉ አይቅርብኝ ብሎ ይመስላል፣ ከሸንጎበቱ ላይ፣የቆላ አለሌ ጢም መሳይ አብቅሏል። ግንባሩ እንደቀጭን ኮበሌ እርግዝና አሞጥሙጦ የወጣ ነው።ላህያዊ ቅርፁ፣እንደ ድሮው የመርካቶ ደንድር ሽልጦ ክብ አይ ሉት ሙልሙል (አባል) አይነት ሆኖ ቅርፅየለሽ ነው። ሲናገር – እንዲቱን አረፍተ ነገር ከጨረሰ በሗላ፣የራሱን ክር መልሶ እንደሚያጠነጥን ከርካሳ ካሴት፣ የጊዜ ቆይታ (ኢንተ ረቫል) ያደርጋል። ስለዴስኪሪው ሰብአዊ የአካል ምንነት መግለጫ ለመስጠት ያህል፣እን ጅ፤ዋናው የምንነጋገርበት ርእስ ስለምሽቱ ዲስኩር ዲስኩራዊ ይዘት ይሆናል ።

"......የጨዋታውን ህግ ማወቅ ያስፈልጋል!!" ሲል ነበር እኛ ማየት የጀመርነው ። "እኛ ያው የፈረደበት ድንቁርናም ፈረንጅ ሲናገር የቀራረማት ምንትፍ ብሂል መሆኗ ነው ። እኛ

ማየቱ ጠፍጥረን የጋገርነውን የህገ መንግስት ቂጣ፣እንዳለ ከነስግስግ እንክርዳዱና ሰና

ሩ ተቀበሉ"፣ለማለት የሚፈልግ ይመስላል። አዎ ወትሮስ ቢሆን የልጆች ጨዋታ፣ከአመዱ ከመረሬው አፈር፣ከአሸዋው.......ተደባልቆና ተላቁጦ አይደለም እንዴ ቂጣ፣እንጀራ፣ አም ባሻ፣አየተባለ ህፃናት ሲጫወቱበት የሚውሉት ?ወጡንስ ቢሆን፣እነማሚት ሰርተው ለአባ ወራዎቹ ማሙሽ የሚያቀርቡት፣ምኑን ከምን(ኩሉም አይቀር)አደበላልቀው እንደሆነ፣በጥ ንታዊው የነማሙሽና የነማሚት ጨዋታ ህግ የታወቀ አይደለምን ? እኛ ጉጭማ ሰውዬ እ ንዴት ሊያገናኙት ቻሉ ?......የጎረኑትን የዲስኩር ክፍሎች ብቻ መጠቃቀሱ በቂ ይመስለ ኛል። "ጉጭማውን" ከነባንዳ መንጋው ከሚኒልክ አዳራሽ ተግተልትሎ እንዲገባ ያስቻለው ለአመታት አድሜ"መርሆዬ!"እያለ በዱር በገደሉ፣በበረሃና በምድረ በዳው ሲጨፍር ሲያ ቅራራ የነበረበት "አመፅ" መሆኑን፣ ዛሬ ጠፍቶት ይሆን – 'ከናንተ ምንም አይነት አመፅ እንዲካሄድ አንፈልግም! እኛ የምንፈልገውን ስልጣን፣ሀብትና ደስታ አግኝተናልና ከእንግ ዲህ የሚያስፈልገው ሶስት ነገር ብቻ ነው!! ይኸውም 'አንደኛ ሰላም! ሁለተኛ ሰላም! ሶስ ተኛም ሰላም!!"....እያለ ሲንተባተብ፣እነዚያ ወዳጆቹ – መቼም ሲበዛ ታጋሾች ናቸውና፣በ ትእግስት ሲያዳምጡ አመሹ። ትክክለኛ የድንቁርና ነፀብራቅ ነበር። "አመፅ" እኮ የራሱ ውስጣዊ መመሪያ ቋሚ ህግ ያለው የተፈጥሮ ስነ ስርአት ነው። በተለይም በማህበረሰብ አኗኗር ውስጥ እጅግ ጎልቶና ደምቆ በትግበርት የሚታይ ጉልህ ኩነት ነው።ሳይንሱ በቋ ንቋው "ሱፐርሳቹሬትድ" ይለዋል ። ሲበዛበት መጠኑንና አቅሙን ሰቶ የመገንፈል ባህር ያዊና ድርጊታዊ ስሪት ነፀብራቅ ነው።በሁለንተናዊ ትግበርት አፈፃፀም ላይ ማንጠር ይቻ ላል – ይህን ሃቀኝ የማመፅ ህግ።"ጉጭማው" እንዳለው ወይም እሱ እንዳይደረግ ስለተመኘ ው ብቻ ሊገታ የሚችል ተልካሻና ቀላል ስነ ስርአት አይደለም – አመፅ። ከዚህ ቀደም በአለማችን ውስጧ ከዳር እስከዳር የተነሱ ገናናዎችን ሁሉ የፈጠረ አመፅ ነው።በተራውም እነሱንው መልሶ በአፍጢማቸው ለመድፋት ሲነሳ፣ለመከላከል ሞክረው ነበር። አንድም የተሳካላቸው አልነበሩም። በነሙሶሊኒ፣በነሂትለር....መመሳከሩ በቂ ነው። "ሌላውን ሁሉ ማድረግ ይፈቅድላችሃል ! ከአንዲቱ አመፅ በስተቀር!!" አለና አያ"ጉጭማ"። የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ "ከአንዲቱ ነፃ አውጭዋ 'አመፅ' በስተቀር" ሌላ ምንም የሚፈልገው ነገር የለም።በግላዊ አመፁ "ህዝባዊ ህገ መንግስት ደንገገ" በማወጅ፣የዘረኞችን ከፋፋይ ኢህ ጋዊ ቆሻሻ ሰነድ ደምስሶ ያጠፋል።"ለብሄራዊ እርቅ ቅድመ ሁኔታ እያሉ የሚንጫጩት

ን ባለፈርስ አምላኮችንም በአንድነት ደቅቶ ዶጋመድ ያደርጋል። በሶስተኛው ዙር ትግል የተተለመው ፍልሚያ፣ዘረኞች ባንዶችን ከነፈጣሪ ጌቶቻቸው(ኢምፔሪያሊስቶችና ኮሎኒያሊስቶች) ጋር ባንድነት ድባቅ መቶ በየጎልጎታቸው ሳይቀብር አይቆምም። ነገ የሚታይ ነገ የሚፈፀም ድላዊ ኩነት ነው። እስከዚያ የቅርብ ወገኖቹንና ሰላዮቹን ከአለም ዙሪያ እየሰበሰበ "ሰስእኦ! ሰስእኦ – ሰይፍን ዋልታን ኩኦ – አንት ዘአድና...." እያለ ያፋሽክ!!!!!!

እንግዶቼ የሚሉት –"....በቆየ የየሃገሩ ልምድና የተዘወተረ ባህል፣ አንድ በሃገር መሪነት ሉአላዊ መአርግ ላይ የተሰየመ ግለሰብ፣ቢያንስ ቢያንስ ያለበትን ማእርጋዊ ክብር ለመጠበቅ ሲል፣ በግላዊ የሰብአዊነት አካላዊና ገፃዊ አካሉ ( Personality )መፍርሀ ወመ ደንግፅ የሚንፀባረቅበት ግርማ ሞገስ የተጎናፀፈ ፣ ሌላው ቢቀር ፣ የአነር የፋደት ያህል መድምምነት( Charismatic & Magnanimous)የሰው መሆን አለበት። እኛ ሰው የሚታይባቸው ምልአተ ገፅ፣ እንደ ሀገር መሪነታቸው፣ ይህን ቅድመ ሁኔታ አያከትትም። በቀደመው ታሪካችን ውስጥ ፣ እነአይዙር ይሉ አነናአድ አለያም ሚናስ፣ ያን መሰሉን ቅድመ ሁኔታ ያሟሉ ባይሆንም ፣ በጨዋ ባህርያቸው አማካይነት ያስተካክሉት ነበር ። እኛ ዲስኩረኛ ሰውዬ ግን ፣ በረጨት ሃሳብ አንፃር ፣ ግልብነትና ቀላልነት ይታይባቸው ስለነበረ፣ ከሁሉ ቱ መስፈርቶች አንዱን እንኳ ያላሟሉ በመሆናቸው፣ እንግዶቼን አበሳጭቶ፣ ለአነጋገራቸው መከረር ምክንያት ሊሆናቸው ችሏል። ያም ብቻ ሳይሆን ፣ ሰውየው እንኳንስ ለባታሪካዊቱ ታላቅ ሀገር (ኢትዮጵያ) ቀርቶ ፣ ለተገኙበት የአድዋ መንደር የወረዳ ገዥ መሆን አይችሉም !!!"...... የሚል አጠቃላይ ድምዳሜ ነበር የሰጡት ።

ይህን ፅሁፍ ወደ እሚመለከተው የዲስኩረኛው ተረብ ላቅና። "የፖለቲካ እስረኛ ብሎ ነገር የለም !......እስረኞች ምህረት ይጠይቁኝ !......."። ይኸ እንግዲህ ቅዠት ካልተባለ፣ሌላ ምን ነገር ሊባል እንደሚችል ከቶ አይገባኝም። ባጭሩ መተቸት ይቻላል።ፀጋዬ እና ብዙሃን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ቆፍጣኖች ኢትዮጵያን የታሰሩት –"የጠ.ሚ.ሚስት ቀሚስ ሲገልቡ እጅ ከፍንጅ ተይዘው" አለያም "የፕሬዚደንቱን ባለቤት ሙታንታ ሲቀዱ" እጅ ከፍንጅ ተይዘው ነውን ፣ ለዘመናት በእስር ቤት ያለፍርድ ፍዳ ፈጠቃቸውን ሲበሉ የኖሩት ? ኢትዮጵያዊ ባልሰራው ወንጀል ቀርቶ በፈፀመው ወንጀል እንኳ፣እስከላመነበት ድረስ፣ ጥፋቱን ተቀብሎ –"ምህረት የሚጠይቅበት ባህሉም ሆነ ልምዱ እንደሌለው" ስ

ለምናውቅ፣እስር ለማኖር የተዘየደ ቅርሻት እንጅ "ይቅርታ አድርግልኝ"የሚለው — ሰ ው ከቶ አንድም እንደማይኖር፣ከወዲሁ ህሊና ካለው ሊያውቀው ይገባል።

"ነገረ አመፅ" አለያም "ንፍረተ ትግብርት" – እንዲሁ በዘፈቀደ እንደዳጉሜ የደመና ሽንት ጭርቅታ ፀንሶ የሚወልደው ፣ አለያም በጠራራ ፀሃይ ላይ ጋኔል ለማባረር ድንገት የሚበርቅ የወርሃ ሰኔ "ብራቅ" እንዳይደለ ቀደም ባለው አንቀፅ ላይ ገረፍ አድር ጌ አልፌው ነበር። የደደቢትን ሰራዊተ ደናቁርት ለማስተማር ሲባል፣መልሶ ቀልሶ፣ሰልሶ ቾላልሶ መናገር ግድ ይላልና – የብዙ ኩነታዊ ፍጭትና እርስበርስ ፍትጊያ፣ የአጠቃላይ ድምር ውጤት መሆኑን ማስተማር ያስፈልጋል – አቶ አምበርብር አመፅ !!!– ምስጢራዊ ኩነቱ "የሞልቶ መፍሰስ" አለያም "የፈልቶ መገንፈል" አለያም"የተሰባብሮ መደርመስ" ድርጊታዊ ውጤት ነው።ልኩን ሲስት፣መጠኑ ሲበዛ የሚከሰት ኩነት ነው።የአፈንቀቃል ባህርዩ "ቁጠኛ" (ቯይኦለንት) ክስተት ነው። በተራ ኩነታዊ ስሪቶች ውስጥ እንኳ፣በጉልህ ይታያል። ለምሳሌ – ጭነት የበዛበት ማንኛውም ነገር መገልበጥ ብቻ ሳይሆን ይወላልቃ ል።ንፊት በዝቶበት የጦዘ ፊኛ (ባሉን) ይፈነዳል።እጅግ ጦዛ የከረረች ክር፣ስበት ሲበዛ ባት፣ቷ ብላ ትበጠሳለች። እሳት ላይ የተጣደ ውሃ፣ነዲድ በዝቶበት ፣ከንፍረት ደረጃው ሲደርስ ገንፍሎ ይፈሳል። መፍሰስ ብቻም ሳይሆን፣ሲጠብሰው የነበረውን ነዲድ እሳት፣ በቅፅበት ያጠፋል ። እነዚህን የመሳሰሉ የአመፅ ኩነታዊ ተምሳሊቶች፣ በሺ መደርደር ይቻላል። "ዘምር በመጠን!" ይላል ያገሬ ካህን።አለቅጥ ቢጨህ፣ጉረሮው እንደሚበጠስ ሲመክር ነው። በማህበራዊው እንስሳ የህብረተ ሰብ ህይወት ውስጥ፣አመፅን የሚመለከቱ ብዙሣን ህጋውያን ኩነቶች አሉ። "አመፅ" ከሰዎች ዘንድ ሊከሰም የሚችለው፣ጨቋኝ የ ሆኑ ግፈኞች፣ ለአንዴም ለምንጊዜም ተደምስሰው ሲጠፉ ብቻ እንደሆነ "የህጉ አንቀፅ ቁጥር አንድ ይደነግጋል!"።አመፅ እስኪፈነዳ ድረስ መለገሙ ግን፣መጠሪያውን የድጅ ኖ ጡንቻውን እስኪያደራጅ ድረስ ብቻ ነው።እነ ፀጋዬ ባልፈፀሙት ወንጀል፣በገዛ ምድ ራቸውና በግለኛ ሀገራቸው ውስጥ፣ለአመታት ታስረው የሚማቅቁትም "ፅዋው እስኪሞላ ድረስ"እንጅ፣አንድ ቀን አመፅ በራቸውን አንኳኩታ "ኑ ውጡ! የነፃነትን አየር ተንፍሱ!" ለማለት ከቶች ማለቷ የማይቀር ነው።...........

በቅርባችን ከምናያቸው አንዳንድ የአመፅ ምሳሌዎችም መጠቃቀስ ይቻላል።በየብሱ

ላይ የሚሽከረከሩትን ማናቸውም አይነት መንገኒቃዊ (ሞተራዊ) አካላት ፣ ሰንጎ ሳይወዱ በግድ የሚያንቀሳቅሳቸው -"ሞገደኛው አመፅ"- ነው።የባለጎማውን መኪናና የባለሃዲዱን ባቡር እንኳ ብንጠቅስ፣ነዲድ እሳት ተጭሮበት በመቀጣጠልና በመንደድ ላይ የሚገኝ፣በ ሞተር ጋን ውስጥ የሚገኝ ነዳጅ ቤንዚን፣ ከተጫረበት ቃጠሎ ለመሸሽ ሲል፣በገዘ ራሱ ትግል ያካሄዳል።በጋኑ ውስጥ ታፍኖና ታምቆ እንዳለ፣እሳት የተጫረበት ቤንዚን መፈና ፈኛ ሲያጣ፣ ለህልውናው ድህነት ሲል፣ የሞት ሽረት ትግል ያካሂዳል።ከታፈነበት የነዲ ድ እመቃ ውስጥ እንዳለ ሲወጣጠር፣ የውጥረቱ ሃይላዊ ግፊት፣ መንኮራኩሩ የቆመበትን ጎማ ሲያንፈራፍር፣ ካለበት ቦታ መንቀሳቀስ ይጀምርና፣ግፊቱ በጠነከረ መጠን፣የጎማውን የመሽከርከር ፍጥነት እንዲጨምር ያደርገዋል። አንዳንዴ መኪናም ሆነ ባቡር ሲቃጠል የምናየው፣የቤንዚኑ አመፅ አሸንፎ ድል በመምታት፣በሃይል በጥርቆ ሲወጣ ነው።ይህ አ ጠቃላይ ንባበ ቃል (ቲኦሪ) በአየራት ላይ ለሚከንፈው ነፋሪት (አውሮፕላን)፣ በባህር ላይ ተንሳፎ ለሚንሸራሸረው ጀልባና መርከብ ሁሉ ይሰራል ። በሶሻላዊው ማህበረ ሰባዊ ኑሮ ውስጥ የምናየውም አመፅ፣ የአፈናና የእመቃ ርቱአዊ ውጤት ነው።እነወዲ እንቶኔ አመ ፅን ያን ያህል የፈሩትና "ከጨዋታው ህግ ውጭ ነው"የሚሉት፣ወደው አይደለም፣የኢት ዮጵያን ህዝብ ለአመታት፣ምን ያህል አፍነውና አምቀው እንዳሰቃዩት ያውቃሉና።..........

እንደተጠቀሰው፣የሚቃጠለው የሞተር ውስጥ ነዳጅ፣ከቃጠሎው ለማምለጥ ሲንፈ ራፈር አየሩን (ለነፋሪት)፣ውሃውን (ለመርከብ) በነዛሪት (ፕሮፔለር) ሲቀዝፍ፣አውሮፕላኑ ም ሆነ መርከቡ ከመንሳፈፍ አልፎ ይንቀሳቀሳል።ዞሮ ዞሮ ያ የታፈነ ቤንዚን፣ ከቃጠሎ ው ለመተንፈስ ሲወራጭ የመንኮራኩሮቹን አካላት እንዳንቀሳቀሰ መረዳት አያዳግትም። ነፋሪውን በአየር ላይ፥መረከቡን ደግሞ በውሃ (ባህር) ላይ ተንሳፈው እንዲምዘገዘጉ ያስቻ ለው፣ውስጣዊ የቤንዚን አመፅ መሆኑ፣በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ለሚከናወኑ ድርጊቶች ሁሉ በአርአያነት የሚያገለግል ቋሚ የተፈጥሮ ህግ መሆኑን ማመን ይኖርብናል ። ይህን ነባር የተፈጥሮ ህግ፣ቢገባቸውም ባይገባቸውም፣ከደደቢት አምባ ለተፈለፈሉ ደናቁርት መላልሶ ማስተማር፣ ግድ ይላል። በርግጥ ባይገባቸው ነው እንጅ፣እነሱን ራሳቸውን፣ከስ ድስት አመታት በፊት፣ ጭው ካለው የሃውዜን በረሃማ ምድረ በዳ ፣ ሳያስቡት አምጥቶ ድንገት ከምኒልክ ፀአዳ ቤተመንግስት ያስቀመጣቸው "አመፅ" መሆኑን ማመን አለባቸው። ቀላሉ መግለጫ "ወ - ሻ"ን "የፈጠረ አመፅ ነው" የሚለው ቋንቋ ይገልፀዋል።

እኔ "አባ ፈንቅል አመፅን" የማየው፣እንደ "አቃቤ ሰአት ፈንጂ"( Time Bomb )ነው። እነ ወዲ ደደቢት ስለፈሩት ብቻ፡ሟሸሾ የሚጠፉ ምትሃት አይደለም።ጊዜው ሲደርስ፣የ ጊዜው ጊዜ፣ ድምብቅ ተምጧ ብሎ ይገለባብጣል።የሚጨቁኑ ሁሉ፣ የማያልፉት ፍትሃዊ መቅሰፍት ነው።ይህ ማለት ሲያልፉ የሚችሉበት መንገድ፣ ጨርሶ የለም ማለት አይደለ ም።ከተጨቆኑ ወገኖች ጋር አሁንም በእኩልት እርከን ላይ ተቀምጦ፣ ሃቅና ሎጂክን መ ሰረት ባደረገ እርቃዊ ውይይት አማካይነት መደራደር ይቻላል።የእኩልነት መድረክ የሚ ባለው ደግሞ፣የጠፈጠፉትን ግለ ወጥ ህገ መንግስት አቅሮ፣ለዲሞክራሳዊ አሰራር አጣማ ጅ የሚሆኑትን ሚዛን፣ጠባቂ ባላዊ የተቃዋሚዎች ዋልታ አስወግዶ፣ያለወንጀል ማስረጃ በሺ የሚቆጠ ሩ ንፁሃን ወገኖችን አስሮ፣የሃገሪቱን ሀብትና ንብረት በግል ውጦና ሚሊታሪውም ሆነ ፖ ሊሱ የግል ጠባቂ ዋርድያ....በሆነበት ጨለምተኛ ሁኔታ ውስጥ ሳይሆን፣እነዚህ ሁሉ ህዝ ባውያን እሴቶች ሁሉ በጋራ አገልግሎት ተቀይረው፣ተግብራዊነቱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

ከበስተላይ እንደተተረከው፣የየብሱ ተንቀሳቃሽ መንገኚቅ (ሞቶር)፣ከቤንዚናዊ ቃጠሎ የተከሰተው ሃይል፣ ወደ ጎማዎች ማንፈራፈር ስራት ተለውጦ፣ የመጓጓዣን እንቅስ ቃሴያዊ ተአምር እንደፈጠረ ሁሉ፣ በለስላሳው ሶሻላዊ የማህበረ ሰብ ህይወትም ውስጥ፣ በነወዲ ወያኔ-ሻቢያ የሚፈጠር፣ የአፈናና የእመቃ ሰብአዊ ቃጠሎ፣ የማይቀረውን አመፅ ፈጥሮ፣ለዓኅነት፣ለፍትህ፣ለርትእና ለመብት የሚደረገውን ፍትጊያ በማፋፋም፣አንድ ቀን የድል ደመራ ተክሎ የችቦ ብርሃን እንደሚያበራ የሚያረጋግጥ፣ ሳይንሳዊ ሃቅ ነው።

የህዋውና (የአየር) የባህሩ (የውሃው) ምልአተ ሃይል፣ በነፈረና በተቃጠለ፣በታፈነና በታመቀ የነዳጅ መተራመስ፣የሰማያትን ባለአክናፋት መንኮራኩሮችና(አሮፕላን ሆነ ሳታላ ይት) የአለመ ማያትን ተንቀሳቃሽ አካላት (መርከብ ይሉ ጀልባ) በፍፁማዊ ትግብርታዊ ሃ ይል፣ያለውድ በግድ ሰንጎ ማሽከርከር የቻለ፣በተፈጥሮ ህግ የሚመራ"አመፅ"የደቃውቁን ኢምንቶች፣ የነ 'ወ -ሻ' ን፣አፈናና እመቃ፣አገሩና ጭቆና ብትንትኑን ሊያወጣ አይችልም ብሎ የሚያምን ግለሰብና ቡድን ቢኖር፣ከነውሼ ዋርዴ በአምሳላዊ ቅርፅ እንጅ በአስተሳ ሰብ በምንም የማይለይ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

ከምድሩ ወደ ላይ ከፍ ብለን፣ስለሰማያት አሳቤ የተፃፉ መዛግብትን የመረመርን እን ደሆነ -"አጅሬ አመፅ"በብዙ መልክ ሲገለፅ መኖሩን እንረዳለን።አንዳንድ መረጃ ልጥቀስ! በድህረ ክርስቶስ 33ኛው ዘመን ላይ፣ ሰውን ለማዳን የመጣ አምላክ በራሱ ፍጡራን ሰዎ

ች ተይዞ ያለወንጀሉ ከተቀጠቀጠ በሂላ፣በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሲሞት፣ አካላተ ሰማያት በሙሉ (ፀሃይ፣ጨረቃ፣ከዋክብት....) አምፀው፣የተዘወተረ የወትሮ ተግባራቸውን አቁመው ነበር።ማለትም – ሰማያዊት ፀሃይ፣ ፀዳለ ብርሃኗን በመንፈግ፣ ቀኑ እንዲጨልም አድርጋ ነበር። ሌላይቱ የሌሊት ፀሃይ ጨረቃም (ወርህ)፣ፍፁም ደም በመምሰል የበቀል አመፃዊ እርምጃ ወሰዳ ነበር።ቁጥራቸው ይህ ነው የማይባል እልፍ አእላፋት ከዋክብትም ከነባሩ ሰማያዊ መካናቸው ረግፈዋል (እንደ ኮሜት)።

እንደገና በሰዎች መዝገበ ታሪክ ውስጥ፣ በየዘመኑ የተከሰተውን "ታሪክ አመፅ" የመረመርን እንደሆነ፣በየታሪካዊው አዝማናተ እርከን ላይ – ማለትም በዘመነ አበው፣በዘመነ ነቢያት፣በዘመነ ነገስት፣በዘመነ መሳፍንት....ወዘተ.በዘመነ ሃዲስም ከጥንታውያኑ ሄሮድስ፣እስክንድር፣ናቡከደነፆር....እንስቶ እስከትኩሶቹ ሃያላን አነናፖሊዎን እነሂትለር ሙሶሊኒ ድረስ.............በነበሩት ገናናዎች ኣ[illegible] የተደረገ የአፈናና የእመቃ አምባገነናዊ ግፌትና ጭቆና፣ "እጅሬ አመፅ"ን ወልዶ፣ሁሉንም ዶጋመድ አድርጎ እንዳነጠፋቸው እናውቃለን! በተለይም የመከራውና የግፉ የቅርብ ተካፋይ የሆነው እንጋፋው የኢትዮጵያ ትውልድ፣ ፋሽስቱ ሙሶሊኒ የሀገሩ ቤት ወይዛዝርት ሳይቀሩ፤በኢትዮጵያ ለሚያደርገው ወረራ የስንቅና የትጥቅ መርጃ እንዲሆን፣ ያንገታቸውን የወርቅ ሀብልና፣ የጆሮዎቻቸውን የአልማዝ ሎቱ እያወለቁ ሰጡ [illegible]፣ከጥቂት አመታት በሂላ፣አፈናውንና እመቃውን በነሱው ላይ በማድረሱ፣በድንገት አምፀው ከቤተ መንግስት አውጥተው የዝቅዝቅ ሰቅለው እንደገደሉት የታሪክ ሃቅ ነው።የ"አመፅ ነገር አታንሱ!" እያሉ የሚለፋደዱብን የኛው ዘመናይ ሙሶሊኒዎች፣እነሱ ወደዱትም ጠሉትም፣ የፈሩት አመፅ፣ ህጋዊ ኪደቱን ጠብቆ፣አንድ ቀን ከቀና አጣና ላይ ሳይሆን፣ከወልጋዳ ግንድ ላይ እንደ ባንዳ አባታቸው፣የዝቅዝቅ ቸንክሮ እንደሚሰቅላቸው፣ከወዲሁ በስርአት ሊያውቁት ይገባል።

በባህር ላይ ማእበልና ሞገድ፣ በየብስ ላይም አውሎ ነፋስ ቢያምፁ፣ በዘፈቀደ የሆነ ኩነት አይደለም።ምድሪቱ በአቶምና በኒውክለር ቦምቦች ስትነሽም፣መንቀጥቀጧ፣የውዴታ አይደለም።የማመፅ ቀጥተኛ ውጤት ነው።የደቡብ አፍሪቃውያንን የዘረኞች አገዛዝ ሞያሌ፣ከነሰንኮፉ የነቀለ፣ የጥቁሮች አመፅ ትንሳኤ ነው።የኢትዮጵያን የዘመናት የፊውዳል ስርአታዊ ብጉንጅ፣ያፈረጠ፣የኢትዮጵያውያን ተማሪዎች፣ያላሰለሰ ትግል ነው።

የትላንትናውን የምርጥ መኮንኖች አምባገነናዊ ስርአታዊ ውርዴ የኮላ፣የኢትዮጵያ ህዝብ

የተባበረ ሃይላዊ አመፅ ነው ።ይህን ትንተናዊ ላስቲክ፣ በግራም በቀኝም፣በራስጌም በግርጌ ም እንደስፈላጊነቱ ቢለጥጡት፣ እስከ ላይ እስከ አርያም፣አለያም እስከታች እስከ በርባ ሮስ ሊደርስ ይችላልና፣ የነገረ "አመፅን" ታሪካዊ ይዘት ላንባቢዎቼ ልተውና፣አሁን ወደ ተነሳሁበት የፀጋዬ ደብዳቤዎች ትንተናዬ ልመለስ።

24/11/79

ተናፋቂ ለሆንከው ወንድማችን
ኃይሉ ገ/ዮሐንስ ፣

በአይሌው ፡ እንደምን ፡ አለህ ፤ እኛ ፡ ስሙን ፡ ክረምትን ፡ "ደምፀ ፡ እገሪሁ"
በማለት ፡ እያጋፈርነው ፡ ነው ፡፡ — ዶርግ ፡ ደጋሞ ፡ " ደምፀ ፡ እገሪሁ ፤ ደምፀ ፡
እገሪሁ " ሲሉበት ፡ ዛሬ ፡ ይነሣብትና ፡ ያስገዝፈዋል ፡ ይሉናል ፡፡ —
ይገርምሃል ፤ በዚህች ፡ ለአሳሽ ፡ መዝሙር ፡ ዓሊናውን ፡ የሳተ ፤
" ወአሮ ምዕራፍ ---- ይትከወስ ፡ ኩሉ ፡ ኀይለ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡
አሜሃ ፡ ይበክዩ ፡ ኩሉሙ ----- " የሚለውን ፡ አርዕድ ፡ እንቀጥቅጥ ፡
የሚለውን ፡ ዘይት ፡ መዝሙር ፡ እንዲልትሰጡ ፡ ምን ፡ እንዲሚውለው ፡
አንረሳት ፡፡ —

ፀሃፍት ምሁራን ፣ እንደዝሆማ የሚፍለቀለቅ ድረሰታቸውን ሲያጎርፉት፣ ከተፈጥሮ ኩነት ጋር አለያም ከነገረ ፍልስፍና ጋር አጣምረው እንጅ፣ሃሳባቸውን እርቃኑን ብቻ በደ ረቁ አራቁተው የማቅረብ ልምድም ሆነ ባህል የላቸውም ። የዚህ አይነቱ የአፃፃፍ ስልት የማይለየው ፀጋዬም፣በሚፅፋቸው ድርሰቶች ሁሉ፣ ሃሳቡን ከአንድ ሌላ የተፈጥሮ ኩነት ጋር እያዛመደ እንደሆነ ፣ ቀደም ብለው በቀረቡት ጦማራዊ ሰነዶቹ አማካይነት መረዳት ይቻላል ።በዚህኛውም ደብዳቤው ላይ – የነበረበትን የወርሃ ክረምቱን ወቅት አስመልክቶ "....ደምፀ እገሪሁ (ለዝናም)" የሚለውን የወርሃ ክረምት ዜማዊ መዝሙር አመላክቶ፣የተ ፈጥሮን የተለያዩ ወቅቶች ይገልፃል ።የሃምሌና የነሃሴ ማእበላዊ ዝናምና ነጎድጓዳዊ ህዋ ሲያስገመግም ላየው፣ሰማይ ምድሩ ተገለባብጦ ሊደመሰስ የሚዘጋጅ ይመስላል ። ፀሊም ደመና በሰማያዊ አፉ ጎርሶ፣ ያፈጠጠ ደራጎን የሚመስለው የክረምት እስታዊ ገፅታ፣እጅ ግ የሚያስፈራ፣ግርማ ሞገስና መፈርህ ወመደንግፅ ያለው ይመስላል ። ያ አይነቱ አስፈሪ ክረምት፣ ከቶ የሚበጋ (ክረምትነቱ የሚያልፍ) አይመስልም ። በቀላል የማያዋዛ ትርጉም ፀጋዬ "ደምፀ እገሪሁ...." ብሎ የጠቀሰው፣ ሰማዩን መርገጥ ብቻ ሳይሆን፣በመብረቅ ግረ ሻው እየደረመሰ የሚገሰግሰውን ዝናባማና ጎርፋማ ክረምት መምጣቱን ሲገልፅ ነው ።

በአዲስ አበቦችማ ቅይር ብሂል፣ቆሻሻውንና ጥርህርሁን ጠራርጎ ከአቃቂው የአባ ሳሙኤል ባሕር ወስዶ ስለሚጨምርና ከተማይቱንም ስለሚያፀዳ –"ምክትል ከንቲባ" ተብሏል ። በንፅፅር ድርሰታዊ አቀራረቡ የበለፀገው ፀጋዬ "ደምፀ እገሪሁ! ደምፀ እገሪሁ !" ሲሉበት

ያ ጽርጽራው ደርግ ፣ ደርሰው የማጅራት ጋማውን የጨመደዱት ይመስል፣ በፍርሃትና በድንጋጤ "ዛሩ ይነሳበትና ያስገዝፈዋል!!" ሲሉን እንሰማለን" እያለ፣ ረቂቅ በሆነ አገላለፅ የምርጥ መኮንኖችን አምባገነናዊ የቦቅቧቃነት ስሜታዊ ባህርይ ያጋልጣል።ደርግ በስተኋላ ላይ ያረጋገጠውም፣ ይህንኑ የፈሪነት "ፍርጠጣ" ነበር።

"በዚች በትንሽቱ ለሰላሲት መዝሙር፣ ፈሪው ደርግ ያን ያህል ህሊናውን ከሳተ፣ እንደ እለተ ምፅአት፣ህዝብ ወአህዛብ በአንድነት ተምሞ ሲነሳበት የት ሊገባ ይሆን"እያለ አስፈሪውን የእለተ ደብረ ዘይት ቃለ ምእዳንና የመአት አዋጅ –"ወአመ ምፅአቱሰ....ይት ከወሰ ኩሉ ሃይለ ሰማያት ወምድር አሜሃ ይበክዩ ኩሎሙ.......የሚለውን አርእድ አንቀጥ ቅጥ የደብረ ዘይት መዝሙር ሰንደልቅለት ምን እንደሚውጠው እንጃለ●ት !!!" በማለት ጥሩ አድርጎ ገልብጦ አስጥቶታል። ፀጋዬ እንዳለውም አልቀረም ፣ ህዝብ በህብረት በተ ነሳበት ጊዜ፣ ፍርክስክሱ ወጥቶ እንደጢስ እንደተነነና እንደጉምም እንደበነነ ሁላችንም በአይናችን አይተናል።"ታጋዮች እንደ ሻማ ብርሃን ራሳቸውን እያቃጠሉ፣ነፃነት ብርሃንን ለህዝብ ያበራሉ"እንደሚባሉ፣ደርግን ካባረረ በሂላ፣ ራሱ ፀጋዬ እስረኛ ሆኖ ሲማቅቅ ይኖ ራል።

«... እውነቱን ለመናገር፦ "እውነቱን ተናግረህ የመሸበት እደር" ይባላልና፤ ዛሬ እንድጽፍልህ የቀሰቀሰኝ......በጸሐፊው ዲብዱብ ላይ ከሰዜደኝ በመዋዕድ ከለምትጊዘው "ነፍስ ነገሬት" ጠቅሰ ያደረግከው ነው። —ለብዙ ጊዜ የፊልምናት ፍቱን መድፍን ፀር አብነት ናት።— የሠጃሺውን ሁሉ ማድረግን እትርክ — ባገራችን ጀሮው የመገለው ብዙ ነውና ቸደን ጊዜ ፊውስ ያገኛል፣ እጥንቱም ይለመልማል።— ምኑን ልንገርህ ? ወዳጄ ስቤ? ... »

ፀገየ ወይን በሙያው አንፃር በደብተርነትና በስነ ፅሁፍ መስክ ብቻ እንደንጋት ጅራታም ኮከብ መጥቆ የሚወረወር፣ ልዩ ክሂልና ችሎታ ያካበተ ፣ ባለ "አርት" ሰብእና ብቻ አይደደለም።በዚያ ዜማ-ያሬድ ሞርዶ ባሾረው የሚስረቀረቅ ልዝብ ድምፁ ያዜመና ያነበበ እንደሆነ ፣ የሚፈነጥቀው ቃና እጅግ ሲበዛ ውብና ማራኪ ነው። በዚያ ለብዙሃን አመታት በተሰለፈበት ሀገርና ህዝብ የማዳኛ ትግላዊ ጎራ ላይ ፣ በይበልጥ ይሳተፍ የነበረ ው፣ እጅግ ያኮረተ ፍሬ በሰጠበት በሬዲዮ ስርጭት ተግባር ላይ ነበር።

ፀጋዬ በዚያ ነጎድጓዳዊ ድምፁ አየር ባየር ሲወረወርና ደመናትን ሰንጥቆ ለቆመለት ህዝብ ጆሮዎች ሲሰማ ፣ የብሩህ ተስፋ ብስራትና የሃዲስ ህይወት መራሄ ነፍስ እንደነበረ በጊዜው ያዳመጡት ሁሉ የሚመሰክሩት ነው ። በአንፃሩም የሚሰሙት የጠላት ጆሮዎች

በሚያስተላልፉቸው መብረቃዊ መልእክቶች፣እያበጡ የፈነዱ፣ እያዡ የቀሰሉ እንደነበሩ መጠራጠር አይቻልም ። ብዙዎቹም ከመርበድበዳቸው የተነሳ ፣ የአየሩን ቃላዊ ጦርነት ከሁሉ አስቀድመው ለማጥፋት ያልጣሩበት ጊዜ እንዳልነበር ታውቋል ። የአየር ለአየር ተምዘግዛጊ የትግል መሳሪያውን "ፍኖተ ዲሞክራሲ"(መንገደ ብዙሃን) ይለው ነበር ፀጋዬ! በዚህ ደብዳቤው፣ "በመዋግድ የምትጓዘው – ነፍስ ነባቢት" የሚላት ፣ ሌላይቱ የመሰል ትግብርት ታናሽ እህት ናት። በጎራው መዋደቅ ላይ የምታመረቅን "ፍቱን መድፍን ፀር አብነት ናት" ይላታል።

በዚህ የጦማር አንቀፁ ላይ ከባዱና ግዙፉ መልእክት "...ባገራችን ጆሮው የመገለ ብዙ ነው፣ያን ጊዜ ፈውስ ያገኛል፣አጥንቱም ይለመልማል..." የሚለው ነው። የህዝባችን ጆሮ ለምን አይመግል ? የሆነ ያልሆነ ጆርም-አዘል ዜናና፣ የጠባቦችና የፋሽስቶች መርዛዊ ፕሮፓጋንዳ ሲነሰነሰበትና ሲረጭበት ፣ እንዴት ብሎ አይመግል ? በአለማችን የፖለቲካ ስሪታዊ ጥቅንጥቅ ውስጥ ስልሳውን እጅ የሚሸፍነው ፕሮፓጋንዳ ነው።ያንን የተቆጣጠረ ለድል ዋዜማ ይደርሳል። በ "ዜና ስርጭት"(ሚዲያ) አማካይነት ባለጌን ማስተካከል ብቻ ሳይሆን መቅጣትም ይቻላል። ፀጋዬ በዚያ መስክ ሙያዊ አገልግሎቱ፣ ለብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ የመንፈስ አድገታዊ አስተዋፅኦ አበርክቷል። ግና ምን ይሆናል፣የዚያ ሁሉ ግልጋሎቱና የትግል መስዋእትነቱ ዋጋ – ይኸው እስከዛሬ በበረሃ እስር ቤት ውስጥ መማቀቅ ሆኗል !! የተፈፀመበት በደልና ሰቆቃ ፣ እጅግ አንጀት አይበላም ትላላችሁ ?

«... ደርግ "ሪፐብሊክ" የሚለውን እየመሠረተ ነው፤ እኛም
ሲናፋርስሰት ይበልጥ ጥርሳችንን ነክሰን እየተጸናናን ነው... –
የነርጭ ሰው ይበለንና እንተያያለን ... — to put it modestly ...»

ይህን አረፍተ ሃሳብ ብዙ የሚፅፉበት አይሆንም። "ደርግ ሪፐብሊክ" ብሎ የጠፈጠፈው ጭቃ፣ብዙም ሳይቆይ ውልቅልቁ እንደወጣ ሁላችንም አይተናል። በርግጥ እንደ ብረት ሆኖ በጥንካሬ የተሰራና የተመሰረተ ቢሆን ኖሮ፣ እንዴት እንዲያ ፈጥኖ ውልቅልቁ ይወጣ ነበር?። "በትህትና ቃና ለመናገር!" ይላል ፀጋዬ በልሳነ እንግሊጣር ፣ በጊዜው "ሪፐብሊኩን አወላልቆ ለመጣል" የነበረውን ዝግጅት በመጥቀስ ። ለነገሩማ ያሁኖቹም ተንባላት የቅፅል ድሪቶ ሲደርቱ ቆይተው "ዲሞክራሳዊ – ፌዴራላዊ – ሪፐብሊክ –ምንትስ ምንትስ.."እያሉ በባዶ ስም ብቻ ይመፃደቁ የለ ? እንደአባታቸው ደርግ ባፍጢማቸው እስኪደፉ ድረስ ነው!! ጊዜው አንድ ደመራ እስኪቃጠል ድረስ የሚዘገይ አይደለም።

«...... እንዲንዲቻችን ፡ "ነባሕነ ፡ ነባሕነ ፡ ከመ ፡ ዘኢነባሕነ ኮነ"
ብለን ፡ ደምድመናል ፡ — ይህች ፡ ዲሞክራሲ ፡ የምትገለፅ ፡ በሰው ሐሣብ ፡
በዚህች ፡ የለሰለሰ ፡ መሬት ፡ ካገኘች ፡ በቀላሉ ፡ ሥር ፡ እንድትሰድ ያገራችን ፡ መሬት
ዳግም ፡ እርግጫው ፡ በዝቶበት ፡ ደንድኗል ፡ — ልዩ ልዩ ፡ ጠባይና ፡ ባሕርይ ፡
ያላቸውን ፡ አዝርዕት ፡ እንደጠባያቸውና ፡ እንደ ፍላጎታቸው ፡ አቻችሎና ፡
አገናኝቶ ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ንጥረ ፡ ነገር ፡ በዕኩልነት ፡ ሰጥቶ ፡ አብሮ
ማሳደግ ማሳበብና ማስፈራት ፡ የሚችል ፡ አልመሰለም ፡ — እስቲ ፡ ...
በዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሐሣብ ፡ እንለዋወጥበት ፡ ...
— ፀጋዬ ፡ እደራቀን ፡ —

ቻር ፡ ወር ፡ ይሰጣን ፡ —
ደንታው ፡
የገለህ
/ ... »

እያችሁልኝ እንዴት አድርጎ የዲሞክራሲን እድገታዊ ኪደት፣ልዩ በሆነ በሰምና ወርቅ ቅኔያዊ አገላለፅ እንዳብራራው !! አዎን! እንኳንስ የመንፈሱ ስሪታዊ መዋቅር ቀርቶ ትንሽቱ ተክለ ሽንኩርት እንኳ፣ ተተክላ መብቀል የምትችለው፣ በቅድሚያ የመብቀያዋ መደብ ተቆፍሮ፣ ተኮትኩቶ ተኳትኩቶ ፣ አፈሩ ለስልሶ ፣ ውሃ ጠጥቶ ከተዘጋጀ በሗላ፣ የማያሰልስ እንክብካቤ ሲደረግላት ብቻ ነው ። ዲሞክራሲ በዘመናት ሁሉ መሃል በእድገታዊ ለውጥ የሚደረጅና የሚጎለብት ማህበረ ሰባዊ ሁለገብ ሂደት ነው ። እንደኛ ባለው ማህበረ ሰብ ውስጥ እድገታዊ ኪደቱ እጅግ አዝጋሚ ነው ። ቢሆንም በስርአትና በተግባር በምልአተ ህዝብ አጠቃላይ ፍላጎት፣ አንድ ቀን በሃቅና በቅንነት መጀመር አለበት ። ለዚህ ሁሉ ዋና ጥርጊያ መንገዱ ፣ በየጎዳናው ላይ ቅርቅፍትና ቅርቃር፣ እንቅፋትና ሰከ እሜከላ...የሆኑ፣ እንደጠባብነት ፣ እንደአፍቅሮ ርእስ ፣ እንደአጉል ትምክህት.........ያሉት ደካማ ባህርያት ተወግደው ፣ በምትካቸው እርስ በርስ መደማመጥና መወያየት፣ አንዱ የሌላውን ምክንያታዊ ሃቅ መቀበል፣ እርስ በርሳችን መቻቻል፣የህግ ልእልናን ማክበርና ለምግባረ ሰናያት መሰለፍን ይጠይቃል ።

ፀጋዬ".....ያገራችን መሬት እርግጫው በዝቶበት ደንድኗል !!......" ይልና "ልዩ ልዩ ጠባይና ባህርይ ያላቸውን አዝርእት እንደጠባያቸውና እንደግእዛቸው አቻችሎና አገናኝቶ የሚያስፈልጋቸውን ንጥረ ነገር በእኩልነት ሰጥቶ አብሮ ማሳደግ ፣ ማሳበብና ማስፈራት የሚችል አልመሰለም......" ይልና ከዚህም የተነሳ "...ነባህነ ነባህነ ከመ ዘኢነባህነ ኮነ!.."' በማለት ያጠቃልላል ።ኢትዮጵያን "ህገረ ሞዛይክ" ይሏት የለ ? ህብረ ቀለማትን በስምረት አዋህዶ ውስጣዊና ውጫዊ ውበቱን በድምቀት እንዲያንፀባርቅ ማድረግ ቀላል እንዳልሆነ የሚያጠይቅ ነው ።"እርግጫው በዝቶበት ደንድኗል!!" የሚለው – ፀጋዬ !! ታዲያ ለእንደዚህ ያለ ወጣሪ ችግር ፣ የፀጋዬ ጥንታዊ ግጥም በመፍትሄነት ጭላንጭል ይጠቁማልና

ይህንኑ ግጥም በመሰናበቻነት አቀርባለሁ። እነሆኝ !! (ለምን – በህይወት ለሚገኙ የፀጋዬ ወዳጆችና ቅኔውን አድናቂዎች፣ያችን ዝነኛ ቅኔውን አስታውሰው በጋዜጣ እንዲፅፉ– በ ጠራ መልክ አላቀርብም ? ስለቅኔዋ ፍንጭ ለመስጠት ያህል፣ የተመሰረተችው በአንድ ጨዋታ አይነት ላይ ነው ።)

ማስታወሻ – የፀጋዬን አጠቃላይ ደብዳቤዎቹንና መላ ይዘታቸውን እንዳላቀረብኩ ታውቃላችሁ ብዬ እገምታለሁ። ዋናውም ምክንያቱ "መድሃኒተ ህዝብ" እንደፀገየ ወይን ያሉ ወገኖች፣ከታሰሩበት ቢፈቱ፣ እንደቅመምነታቸው፣ የፈጥኖ ማዳን አብነትነታቸውን ስለማውቅ፣ በህይወት እንዲቆዩልን ስለ እምፈልግ ነው። ስለዚህም በጠቅላላው አንባብያን ተራዳኢነትና ተሳትፎ አንድ ሰላማዊ ዘመቻ መጀመር እፈልጋለሁ ። ሰብአዊ መብት ጠባቂ ድርጅቶች የተዘጋጁ ካርዶችን ፀጋዬና በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን እንዲያስፈቱ ማሰራጨት ብቻ ነው።በዚህ ዘመቻ ወገኖች እንደሚረዱኝ ተስፋዬም እምነቴም ነው። ቸር ይግጠመን ።

***********************************

# ከደብተራ ጸገየ ወይን ቅኔዎች

## ለአብነት የቀረቡ !

1ኛ – ".....ቁማር ተጨውቼ !
ጎፈሩን መትቼ !
ቀረሁ ተጭቼ ።
ምነው ዕድሌ – ተሰበረ (ባማረ) !
ዘውዱን ገልብጨው – በነበረ !......."

2ኛ – " አዎ ጠፍቷል አሉ – ምንድር ነው ነገሩ !
ለፍስጋ እንዲያመች – ይገልበጥ መንበሩ !

3ኛ – ከለበሱ አይቀር – ሱሪ !
የዚያን ሰው ነበር – የተፈሪ !
ግን ምን ይሆናል – አለው መከራ
ወጥሮ ይዞ – ከቀኝ ከግራ !
አያፈናፍንም – በውጠራ !!!........"ወዘተ.



ምን ይላል መጣፉ ?
- ወነሦቶሙ ለኃያላን እመናብርቲሆሙ !
- ወዘርዎሙ ለእለ የአብዩ ኀሊና ልቦሙ !
- አድከመ ቀስተ ኃያላን !
- ወአውረዶሙ ውስተ መድር ታህቲተ !
- ኢይትመካሕ ኃያል በኃይሉ !
- አይትመካህ ባዕል በብዕሉ..................ወዘተ.